የከተማ አመራርና ያልተማከለ አስተዳደር ፕሮግራም



የካፒታል መዋዕለ-ንዋይ ዕቅድ መመርያ ለኢትዮጵያ ከተሞች

ከተሞችን በአገልግሎት አቅርቦት ውጤታማ ማድረግ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

የካፒታል መዋዕለ-ንዋይ ዕቅድ መመርያ ለኢትዮጵያ ከተሞች

በአገልግሎት አሠጣጥ ከተሞችን ውጤታማ ማድረግ

መሠረተ ልማት በማደግ ላይ ላሉ ከተሞች የጀርባ አጥንት ነው፡፡

መቅድም

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2025 መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር ትሆናለች፡፡ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (እ.ቴ.አ) ይኼን እንዴት እንደምናሳካ ይዘረዝራል፡፡ የከተማ አካባቢዎች የእድገት ሞተሮችና የትምህርት ምጥቀት ማዕከላት ስለሆኑ ከተሞች በእ.ቴ.አ ከፍተኛ ሚና ይወጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ የዜጎችን ሙሉ አቅም የሚገልጹት በደንብ ከተያዙና መሰረተ ልማትና አገልግሎት ከሰጡ ነው፡፡ ስለዚህ መሠረተ ልማት ለሰዎችና ምጣኔ ሀብት እድገት ቅድመ ሁኔታ ነው& ትምህርት ቤቶች ከሌሉ ትምህርት የለም፡፡ ያለጤና ተቋማት፣ ንጹህ ውሃ፣ የተስተካከለ ጠጣርና ፈሳሽ አያያዝ ከሌለ ጤናማ ዜጎች አይኖሩም መንገድ ከሌለም እንቅስቃሴ የለም፡፡ ጤናማ፣ የተማሩና ተንቀሳቃሽ ዜጎች የውስብስብ ማህበረሰብ እና ምጣኔ ሀብት እድገት መሠረቶች ናቸው፡፡ ለዜጎች አገልግሎት የሚሰጡ ኢንቨስትመቶችን ስለሚያቅድ ካፒታል ኢንቨስትመንት እድቅ የሕዝብ አስተዳደግ ቁልፍ ተግባር ነው፡፡

ካፒታል ኢንቨስትመን እቅድ የዲሞክራሲ ደም ስር ነው፡፡ የካፒታል በጀት ሕዝቦች በምን ላይ ገንዘባቸውን እንዳዋሉ ይገልፃል፡፡ ይህ ገንዘብ አገልግሎት እንዲያቀርብ ለአስተዳደሩ ኃላፊነት እንደሰጡ ያሳያል፡፡ ስለዚህ የካፒታል ኢንቨስትመንት እቅድ በጣም አስፈላጊው ክፍል በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ አሳታፊ መሆኑ ነው፡፡

ካፒታል ኢንቨስትመት እቅድ በተፈጥሮ የሕብረተሰቡን ድምጽ አካቶ የሚያሰማ አሳታፊ እና አወያይ ነው፡፡ ሕዝቦች በሚፈልጓቸው እና ቅድሚያ በሚሰጧቸው ጉዳዮች አቅም ያጎለብታል፡፡ ከማቀድ ፣አቅምን ከማጎልበት፣ ከትግበራ፣ ከአፈፃፀምና ከጥገና በተጨማሪ ሕብረተሰቡን በአጠቃላይ፣ ሴቶችንና ወጣቶችን በተለይ በከተማ እድገትና አስተዳደር ሂደት የተሳትፎ እድል ይሰጣል፡፡ ያለውን ሀብት ጠብቆ ማቆየትና ተጨማሪ ሀብትን ለማፍራት ለከተማ አመራሮች የአስተዳደር መሣርያ ነው፡፡

እንደተጠቀሰው ዜጎች የመገልገል መብት አላቸው፡፡ ግዴታም አለባቸው፡፡ በሌላም በኩል አስተዳደሩ ለዚያ መገልገያ የሚሆነውን ገንዘብ የመሰብሰብ መብትና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ እናም ካፒታል በጀቱ፣ ውጤታማ አፈፃፀሙና በላዩ ላይ በዜጎች ቁጥጥር መደረጉ እና ምክር ቤቱ ለጋራ ኃላፊነት ዋስትና ለመስጠት በጣም አስፈላጊ ተግባራት ናቸው፡፡

ይህ መመሪያ የከተማ አስተዳደር ኃላፊነቱን እንዲያሟላ በሕግ ማዕቀፍነት ያገለግላል፡፡ በኢትዮጵያ ከተሞች የካፒታል ኢንቨስትመንት እቅድን ለማሳደግ ቀጥተኛ አማራጭ ያቀርባል፡፡ ለልጆቻችን ጤናማ አካባቢ ለማውረስና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የከተማውን ባለድርሻ አካላት ለማሳተፍ የከተማ አስተዳደሮችን ይደግፋል፡፡

በመጨረሻ ይህን ሕትመት ለማዘጋጀት በቀና መንፈስ የተባበሩትን እና ሁሉንም አጋሮቻችንን በተለይም የጀርመን የልማት ተቋም (GIZ)ን ይህ ሚኑዋል እንዲዘጋጅ ለአደረጉት አስተዋጽኦና ድጋፍ አመሠግናለሁ፡፡

መኩርያ ኃይሌ

በኢትዮጵያ ፌዴራል ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስትር

የካፒታል መዋዕለ ንዋይ ዕቅድ መመሪያ ለኢትዮጵያ ከተሞች
© 2011 የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስትር

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይህ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 410/1997 የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ጥቅም ላይ ስለሚውልበት፣ ስለሚሠራጭበት፣ ስለሚተረጐምበትና በድጋሚ ስለሚካተትበት ወዘተ አኳኋን ሊወስን ይችላል፡፡

ከሌሎች መብቶች በተጨማሪ የመመሪያውን የህትመት ሥራ በተለይም ለግል አገልግሎት በነጠላ ቅጅ፣ በግለሰብ ደረጃ በግል ማባዛት፣ የመመሪያውን የተወሰነ ክፍል (ማጣቀሻ) የማባዛት፣ ተገቢና ተዛማጅ በሆነ አኳኋን ምንጩንና አዘጋጁን ጠቅሶ ለማስተማር አገልግሎት እንዲሁም በቤተመፃሕፍትና መሰል ተቋማት የማባዛት፣ ለሕዝብ መረጃ አገልግሎት የማባዛት፣ በተፈጥሮ ሰው ለቤተሰቡ ወይም በትምሕርት ቤት ከክፍያ ነፃ በሆነ አግባብ በሕጉ በተሰጡት የተወሠኑ ሁኔታዎች መሠረት ለግል አፈፃፀም ማዋል ተፈቅዷል፡:

ይህ ሰነድ በጂ.አይ.ዜድ በኩል በጀርመን መንግሥት ተደግፏል፡፡

ሰኔ 2003
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

ምሥጋና

ይህ ሰነድ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚንስቴር የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ቡድን ከፍተኛ ድጋፍ በተለይም በአቶ አቡየ አንለይ፣ አቶ ደስታ፣ አቶ ጥዑመእግዚና አቶ ዓለማየሁ ተዘጋጅቷል፡፡

በተጨማሪም አዘጋጁ ወሳኝ አስተዋፅኦ ላበረከተው የጂ.አይ.ዜድ ቡድን በተለይም አቶ ሞላ፣ አቶ ኃይሌ፣ አቶ ፈቃዱ፣ አቶ ዳምጤ፣ አቶ ታፈሰ፣ አቶ ላእከ፣ ሚስተር ግሮስና ሚስተር ሽሚት ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

በመጨረሻም ለሰነዱ መዳበር ላደረጉት አስተዋጽኦ የከተሞች ከባቢያዊ አስተዳደርና ልማት ፕሮጀክት (ULGDP) የአለም ባንክ ቡድንን ሊያመሰግን ይወዳል፡፡

ይዘት

የማኑዋሉ አጠቃቀም ገፅ 2

ጠቅላላ

1. ደኪውመንቴሽን ሲዲ
2. የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ ቴምፕሌትን መጠቀም

ክፍል 1 የካፒታል ሙዋለ ንዋይ ዕቅድ ገፅ 6

1. 1. የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ አስፈላጊነት
2. ገቢን ማሣደግና የመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅዶች
3. አሳታፊ ሂደት
4. የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ ('ካሙዕ') ክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ
5. የ" የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ" ዝግጅት የቴክኒክ ኰሚቴ
6. የ" የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ
7. " ሂደት ዑደት

ክፍል 2 የካፒታል ሙዋለንዋይ በጀት ገፅ 12

ደረጃ 1- መጭውን ለመተንበይ ያለፈው ላይ
ዳሰሳ (ቅኝት) አድርግ

ደረጃ 2- ገቢን፣ የሥራ ማስኬጃ ወጭንና ከሥራ
የሚገኝ ትርፍን ተንብይ

ደረጃ 3- የካፒታል ገቢ

ክፍል 3- የፕሮጀክት ጥናት ሐሳቦችን ማመንጨት ገፅ 16

ደረጃ 1- የከተማውን ዓላማዎች ቃኝ

ደረጃ 2- የፕሮጀክት ጥናት ሐሳቦችን ግለጽ

ደረጃ 3- የፕሮጀክት ዝርዝር

ክፍል 4 - የአዋጭነት ምልከታ የመሠረተ ልማት አመራር ገፅ 20

ደረጃ 1- የፕሮጀክቱ ዑደት የሚያስከትለውን ወጭ አስላ

ደረጃ 2- የጥገና በጀትን አመላክት

ደረጃ 3- አጠቃላይ አዋጭኝ ምልከታ (ዳሰሳ)

ደረጃ 4፡ የማጣራት፣ የተፈጥሮ አካባቢው ተፅዕኖ ዳሰሳና የመልሶ
ማቋቋም ማዕቀፍ ፣

ክፍል 5፡ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ገፅ 26

የአጋር አካል የውሳኔ አሠጣጥ

የተለመደው አሠራር

አዲሱ አሠራር

ደረጃ 1- የዕቅድ ተሣትፎ

ደረጃ 2- ልማዳዊው የምክክር ሂደት

ደረጃ 3- አሣታፊ የበጀት አመዳደብ ሂደት

ደረጃ 4 - ሂደቱን የሚያሣይ ዘገባ

ክፍል 6፡ የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድን አቀናጅ ገፅ 36

"የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ አዘጋጅ

ደረጃ 1- የከተማዋ የተጠቃለለ መግለጫ (ቅኝት)

ደረጃ 2- የፋይናንስ ድርጅታዊ ቁመና መረጃ

ደረጃ 3- የ" የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ" ዕዝሎች

ክፍል 7፡ የግዥና የገንዘብ ፍሰት ዕቅድ ገፅ 42

ደረጃ 1- የግዥ ሁኔታዎችን ስለመግለጽ

ደረጃ 2- የግዥ ዘዴዎች (ሥራዎች)

ደረጃ 3- የግዥ ዕቅድን አዘጋጅ

ደረጃ 4 - የገንዘብ ፍሰት ዕቅድ

ክፍል 8፡ ማጽደቅ፣ ማሠራጨትና ቁጥጥር ገፅ 52

ደረጃ 1- የ"የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ"ን አጽድቅ

ደረጃ 2- ዘገባና ሪፖርት

ደረጃ 3- የመረጃ ፍሰት

ደረጃ 4 - ቁጥጥርና የሂደት ክትትል

ዶኪዉመንቴሽን ሲዲ

የማኑዋሉ አጠቃቀም

የዚህ ማኑዋል ዓላማ የከተማ አስተዳደሮችን የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድን እንዲያዘጋጁ ማስቻል ነው፡፡

የ"የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ" ዝግጅት በከተማ አስተዳደሮች የቴክኒክና ፋይናንስ ክፍሎች መካከል የቅርብ ትብብርንና ከአጋር አካላትና ከነዋሪው ሕዝብ ጋር ምክክርን የሚጠይቅ አሣታፊ ሂደት ነው፡፡

ስለማኑዋሉ ጠቅላላ

ክፍል 1- ስለካፒታል መዋዕለንዋይ ጠቃሚና መሠረታዊ መረጃን ይሠጣል፡፡ የ' የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ'ን ክፍሎችና ዓላማ ይገልፃል፣ በከተማዋ አጠቃላይ የዕቅድ ሥርዓት ውስጥ 'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ'ን ያንፀባርቃል፣ ኃላፊነት ያለባቸው ባለሙያዎችንም ይለያል፡፡ በተጨማሪም የድርጊቶችን አስፈላጊ ቅደም ተከተልና በምን አግባብም መፈፀም እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡

ክፍል 2- የፋይናንስ ዝግጅትን ይገልፃል፡፡ ለመዋዕለንዋይ ምን ያል ገንዘብ እንዳለ በግልፅ የሚያሣይ የሀብት አመዳደብን ቀላልና ግልፅ በሆነ አቀራረብ ያስቀምጣል፡፡

ክፍል 3- ካሙዕን ከከተማዋ ስትራቴጅካዊ ዓላማዎች ጋር በማስተሣሠር የሚነደፍ የፕሮጀክት ጥናት ሀሣብን አስመልክቶ ያትታል፡፡
አንድን ፕሮጀክት ከማራመድ በፊት ከተሞች የልማት ዓላማዎቻቸውን መገንዘብና የካፒታል መዋዕለንዋይ ፍሰቱ በረጅም ጊዜ ይዞታ የሚመጣውን የወጭ አሉታዊ ውጤት ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ክፍል 4- ካፒታል መዋዕለንዋይ አዋጭነት ላይ ያተኩራል፡፡ የፕሮጀክት ጥናቶች የቴክኒክና ፋይናንስ አዋጭነትን መፈተሽ (መዳሰስ) አለባቸው፡፡ እያንዳንዱ ፕሮጀክትም በማህበራዊና የተፈጥሮ አካባቢው ላይ ከሚኖራቸው የወደፊት ጫናና የከተማዋን ዓላማዎች ለማሣካት ካለው አስተዋጽኦ አንፃር ሊመዘን ይገባል፡፡

ክፍል 5- አጋር አካላት ከከተማዋ የሀብት መዋዕለንዋይ ፍሰት አንፃር ቅድሚያ የሚሠጧቸውን ተግባራት ስለሚገልፁበት አሣታፊ ሂደት ይገልፃል፡፡ ዓላማው የመዋዕለንዋይ ፍሰቶችን ከተጠቃሚው ሕዝብ ፍላጎት ጋር ለማጣጣም ነው፡፡

ክፍል 6- ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ፕሮጀክቶች እንዴት ወደአንድ የተጠቃለለ የበጀት ዕቅድ እንደሚገቡ ያብራራል፡፡ በተጨማሪም ይህ ክፍል የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድን መግለጫና ተጓዳኝ ዕዝሎች እንዴት እንደሚዘጋጁ ይገልፃል፡፡ በዚህ ክፍል የተገለፁት ዕዝሎች በክፍል 7 ከተገለፁት ሁለቱ ጋር ተዳምሮ ከዋናው ሰነድ ጋር የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡ እነዚህም ምንም እንኳ መመሳሰል ቢኖርም ከደኪውመንቴሽን ሲዲ የዕዝል ሰነዶች ጋር መምታታት የለባቸውም (ገፅ 8 እና 9 ተመልከት)

ክፍል 7- ሁለት የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ አተገባበር ቀሪ ክፍሎችን ያስተዋውቃል፡፡ እነዚህም የግዥ ዕቅድ (ዕዝል 8-የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ) እና የገንዘብ ፍሰት ዕቅድ (የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ዕዝል 9) ናቸው፡፡ እነዚህ ዕቅዶች ግዥ እንዴትና መቼ እንደሚከናወን እና ቀጥሎም የገንዘብ ፍሰት ፍላጐቶች መቼ እንደሚሆኑ መሠረት ይጥላሉ፡፡

ክፍል 8- የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድን የማፅደቅ ሂደት ይገልፃል፡፡ የበጀት ውሳኔ ስርጭትን ይገልፃል፡፡ በተጨማሪም ይህ ክፍል በቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ አጭር መረጃን ይሠጣል፡፡

በማኑዋሉ ውስጥ በጠቅላላው የተለዩ አርዕስቶችን ለማብራራትና ምሣሌዎችንና ተምሳሌታዊ ጥናቶችን ለማገናዘብ መጻሕፍት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በሰማያዊ የተቀመጡት ቃላት ከሌሎች ተጨማሪ ጉዳዮች ጋር በግራጫ ቀለም በተቀመጠዉ የጎን መግለጫ ተገልፀዋል፡፡



ስዕል 1፡- የሲዲ መክፈቻ ስክሪን ቴምፕሌቶች



ስዕል 2፡- የሲዲ ቴምፕሌት ስክሪን ዶክመንቶች



ስዕል3፡- የሲዲ ዶኪመንት ስክሪን

1. ዶኪውመንቴሺን ሲዲ (Resource CD)

ይህ ማኑዋል የማኑዋሉን የአማርኛና እንግሊዝኛ ትርጉሞች ከአውቶማቲክ የካፒታል መዋዕለ ንዋይ ዕቅድ ቴምፕሌቶችና በርካታ ሌሎች ጠቃሚ ዶኪመንቶች ከያዘ ሲዲ ጋር ቀርቧል፡፡ ሲዲው ወደ ኮምፒዩተር ሲገባ ወዲያውኑ በራሱ ይጀምራል፡፡ ሲዲውን ለማንቀሣቀስ የሚያስችሉ መምረጫዎችን የመክፈቻ ስክሪን ይመራቸዋል፡፡ ተጠቃሚው ለዚህ ተግባር የሚያስፈልጉ ፕሮ ግራሞችን ለመጫን አማራጭ ተሠጥቶታል፡፡ ሁሉም ከሲዲው ላይ ያሉ ዶኪመንቶች እንዳልተተረጐሙ ይወቁ፡፡

የሲዲ መክፈቻው ስክሪን ከቴምፕሌቶች ማኑዋሎችና ዕዝል ዶኪመንቶች መካከል ምረጥ፣ ሲዲ ቴምፕሌትና ማኑዋል ስክሪኖች ለቴምፕሌቶችና ማኑዋሎች ከተለያዩ ቋንቋዎች ምረጥ ፣ ሲዲ ዶኪመንት ስክሪን የዋናውና የዕዝሎች ዶኪመንቶችን ምረጥ፣ በጽሁፉ ውስጥ የሲዲው ዶኪመንቶች ማጣቀሻዎች "ሲዲ ዕዝሎች" ተብለውና በዕዝል ቁጥራቸው ተለይተው ተጠቅሰዋል፡፡

ስለሲዲ ዕዝሎች ዶኪመንቶች በጠቅላላው

1. የፋይናንስ አመራርና ሒሣብ
1.1 ማዘጋጃ ቤታዊ የፋይናንስ ማስታወቂያ ማኑዋል
1.2 የፋይናንስ አመራር መመሪያ
1.3 የሂሳብ አርዕስት
1.4 የካፒታል በጀት ፎርሞች

2 ሕጐችና ደንቦች
2.1 መሬትና የይዞታ ሕጐች
2.2 የአካባቢ (ጥበቃ) ሕጐች
2.3 የፋይናንስ አስተዳደር ሕጐች
2.4 የከተማ ፕላን ሕጐች
2.5 የሕዝብና ቤት ቆጠራ (Census - 2007)
2.6 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ

3 ማኑዋሎች
3.1 የበጀት ማሣደግ ዕቅድ
3.2 የመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ
3.3 የማዘጋጃ ቤት የመሠረተ ልማት ሙዋለንዋይ ዕቅድ መመሪያ

4 ግዥና ጨረታ
4.1 የግዥ ደንቦች
4.2 የጨረታ ሰነዶች
4.3 የኮብልስቶን መንገድ ግንባታ
4.4 ዝርዝር የዋጋ መግለጫ

5 ቁጥጥርና ክትትል
5.1 የቁጥጥር ማኑዋሎችና ቴምፕሌቶች
5.2 የሪፖርት ቴምፕሌቶች
5.3 የመረጃ ፍሰት

6 አካባቢና መልሶ ማቋቋም
6.1 የአካባቢ ተፅዕኖ ዳሰሳ
6.2 የመልሶ ማቋቋም ፖሊሲ ማዕቀፍ
6.3 የአካባቢ ሕጐች (Environmental laws)

7 ተሣትፎ
7.1 የሕዝብ ምክክር
7.2 አሣታፊ የበጀት ዕቅድ
7.3 የሕዝብ ስሚ
7.4 መሠረታዊ ጥናት (Baseline survey)

8 የ'ULGDP' ልዩ ዶኪመንቶች
8.1 ተሣትፎና የሥራ ውል ስምምነት ቴምፕሌት
8.2 'ULGDP' የተግባር ማኑዋል
8.3 ለ'ULGDP' ተጠሪ ወኪሎች ዝክረ ተግባር
8.4 የቁጥጥር ማኑዋል

2. የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ ቴምፕሌትን መጠቀም

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ቴምፕሌት የዚህ ማኑዋል ዓይነተኛ ክፍል ነው፡፡ ይህም የመጨረሻውን የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ዶክመንት የያዘ ማይክሮሶፍት ወርድ ፋይልና ሠንጠረዦችን ለማሳካት የሚረዳ አንድ የMicrosoft Excel ፋይልን ያካትታል፡፡ እነዚህ ዶክመንቶች እርስ በርስ የተገናኙና አስቀድሞ ፕሮግራም የተደረጉ ናቸው፡፡

Microsoft Excel ፋይሉ በተጠቃሚው እንዲተገበር የተደረጉ አኃዞችን በራሱ እና ወዲያውኑ ያሠላል፡፡ ከዚያም ሠንጠረዦቹ ወደ Microsoft Word ፋይል በቀጥታ ይተላለፋሉ፡፡ ማናቸውም በExcel ፋይል ላይ የሚደረግ ለውጥ ወዲያውኑ ወርድ ዶክመንት ላይ ይንፀባረቃል፡፡ ቴምፕሌቶቹ በሁሉም የኢትዮጵያ ዋና- ዋና ቋንቋዎች ይገኛሉ፡፡

በተጨማሪም እነዚህ ፋይሎች አውቶማቲክ ባልሆነ ትርጉም ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን አስቀድመው ፕሮግራም የተደረጉ ትርጉሞች በእጅጉ ሥራን ያፋጥናሉ፡፡ ለሁሉም የከተማ አስተዳደር ከተሞች ቴምፕሌቱን መጠቀም የግድ ነው፡፡

! ማስታወሻ፡- ሁለቱም MS Excel እና MS Word ቴምፕሌቶች በተመሣሣይ ፎልደር (አቃፊ) ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡ ስለዚህ እባክዎን ሁሉንም ፋይሎች ከCDው ወደ ኮምፒዩተርዎት በተመሣሣይ አቃፊ ይገልብጡ፡፡ ፋይሎቹን ሌላ የፋይል ስም አይስጧቸው፡፡

2.1 የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ ቴምፕሌት

የMS Word ቴምፕሌት የመጀመሪያ ክፍል ጠቃሚ መረጃን የሚያመላክት መግለጫን ያጠቃልላል፡፡ የከተማውን መሠረታዊ መረጃ ማለትም ስም፣ ሕዝብ፣ የእድገት ምጣኔ፣ የአየር ሁኔታ ---ወዘተ እና የከተማዋን ዓላማዎችና ግቦች አጭር ማጠቃለያ የያዘ ነው፡፡ መግለጫው በተጨማሪም በአሣታፊ ሂደት እና በሕዝቡ ፍላጎቶች፣ ግቦችና ዓላማዎች ምላሾች ውጤት ላይ አጭር ዳሰሳን ያስቃኛል፡፡

ሁለተኛው ክፍል በፋይናንስ አስተዳደር ቁልፍ ዝርዝሮችን የያዙ ሠንጠረገሮች ስብስብን የያዘ ነው፡፡ ይህ ክፍል በአጠቃላይ ከMS Excel ፋይል የወጣ ነው፡፡ ስለዚህም በMS Word ፋይል ውስጥ መታተም የለበትም፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሠንጠረገሮች በሥራ ማስኬጃ (በመደበኛ)ና ካፒታል ወጪዎችና በገቢ ዙሪያ አጠቃላይ ግንዛቤን ያስጨብጣሉ፡፡ ሠንጠረዥ 4 የጥገና በጀትን ያዘጋጃል፡፡ ሠንጠረዥ 5 እና 6 የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ ዋና ክፍሎች ናቸው፡፡ ከዚህም የካፒታል መዋዕለንዋይ በጀት ያዘጋጃል፡፡ ሠንጠረዥ 7 የሰው ኃይል ፍላጎትን ያሣያል፡፡ ሠንጠረዥ 8 እና 9 የግዢና የገንዘብ ፍሰት ዕቅድን ለማዘጋጀት መሣሪያዎች ናቸው፡፡ በዚህ ማኑዋል ሁሉም ሠንጠረገሮች በዝርዝር ይብራራሉ፡፡

የቴምፕሌቱ ሶስተኛው ክፍል ዘጠኝ የ"የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ" ዕዝሎችን ይይዛል፡፡ የመጀመሪያዎቹ 7 ዕዝሎች በዚህ ማኑዋል ክፍል 6 በዝርዝር ተገልፀዋል፡፡ የመጨረሻዎቹ ሁለት የግዥና የገንዘብ ፍሰት ዕቅዶች በክፍል 7 ተብራርተዋል፡

ቁልፍ ክፍሎች "MS Excel" እና "MS Word"ን በቁጥጥር ሥራ ማዋል፣

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድን ማዘጋጀት፣ የኮምፒዩተር ክህሎቶችን በተለይም በ"MS Excel" ማሣደግን ይጠይቃል፡፡ "MS Excel" ማለት የመረጃ ሰሌዳ ሽትን ሥራ ላይ ማዋል ማለት ነው፡፡ ወደ መረጃ ሺት የሚገባ መረጃ አኃዞችን ወይም ጽሑፍን ሊይዝ ይችላል፡፡ ሁለቱም በስሌት ሊገለፁ ይችላሉ፡፡ የ'Excel' ስሌት ከትንሿ የድምር ሥራ እስከ ውስብስብ ፎርሙላዎች (ቀመሮች) ሊዘልቅ ይችላል፡፡ ትክክለኛ ዓረፍተ ነገሮችን በማመሣከር አኃዛዊ መረጃዎች በትዕዛዝ መስመሩ ላይ ወደሴል ይገባሉ፡፡ ቱልባሩ ለናቢጌሽን መሣሪያዎቹ ፈጣን ተደራሽነትን ያመቻቻል፡፡

እጅግ አስፈላጊ ባይባልም 'MS Excel' ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ በCDው ላይ ያለው የ'Excel' ቴምፕሌት የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ አኃዛዊ ስብስቦች ስሌት በፍጥነት ያከናውናል፡፡ በተጨማሪም ስህተትን ለማስቀረት በከፊል የተጠበቀ ነው፡፡ አስቀድሞ የተዘጋጁ ቀመሮች በተዘጉ ሴሎች ውስጥ ለውጥን ሊቀበሉ አይችሉም፡፡ ሊገቡ የሚችሉ ቁጥሮች ብቻ በተከፈቱ ሴሎች ውስጥ ወደ ስሌት ይሄዳሉ፡፡ የ'MS Excel' ሲዲን ተመልከቱ፡፡



ስዕል 4፡ የ Excel አዉቶማቲክ ሰንጠረዥ አጠቃቀም

ክፍል 1

የካፒታል ሙዋለንዋይ ዕቅድ

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ የከተማዋን ስትራቴጀካዊ አላማዎች ለማሣካትና ለማጠናከር የከተማ አስተዳደር ዋና መሣሪያ ነው፡፡ ተግባራዊነቱም የከንቲባው ኃላፊነት ነው፡፡

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ማዘጋጃ ቤቶች የረጅም ጊዜ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ለማቀድ ሊጠቀሙበት የሚችል ተለዋዋጭ መሣሪያ ነው፡፡ የካፒታል መዋዕለንዋይ እንደደመወዝ ያሉ መደበኛ ወጭዎችን አያካትትም፡፡ ነገር ግን የፊስካልና ማህበራዊ የመሠረተ ልማት (መንገዶች፣ ት/ቤቶች) መሣሪያዎች (መኪናዎች) እና የማማከር ሥራ (ፕሮጀክት ዲዛይን) -- ያሉትን ያካትታል፡፡

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ዝግጅት መዋዕለንዋይ ፍላጐቶችን ካለው የሀብት መሠረትና አጋር አካላት ቅድሚያ ከሚሠጧቸው የተለዩ ተግባራት ጋር የሚያስተሳስር ሂደት ነው፡፡ የነዋሪዎችን ፍላጐት በመመለስና በዳሰሳ ጥናት ተገቢ የካፒታል ፕሮጀክቶችን ለመምረጥ አጠቃላይ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሥራ ላይ ይውላል፡፡ የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ በሕግ ደረጃ በከተማ ምክር ቤት የሚፀድቅ ገዥ ዕቅድ ነው፡፡

1. የካፒታል መዋዕለንዋይ አስፈላጊነት?

የከተማ አገልግሎቶች ከሌሎች ተግባራት መካከል የመብራት ተደራሽነት፣ ኮሚኒኬሽን፣ የመጠጥ ውሃ፣ የተፋሰስ፣ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ መንገዶችና ድልድዮችን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ አገልግሎቶች በሺዎች የሚቆጠሩ የከተማ ነዋሪዎችን የጤና፣ የዕንቅስቃሴና አጠቃላይ ደህንነት ለማስጠበቅ ይረዳሉ፡፡ በተጨማሪም አገልግሎቶች ሥራን በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ላለው ከተማ ሕዝብ ይፈጥራሉ፣ ለግል ዘርፉም ዕድሎችን ይከፍታሉ፡፡

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ለከተማዋ ነዋሪዎች አገልግሎቶችን በሚስፋፋው መሠረተ ልማትና ሌሎች አማራጮች ታግዞ የማቅረብ ብቃትን ለማሣደግ ስልታዊ አሠራር ነው፡፡

እንደመልካም አስተዳደር ማረጋገጫ ዘዴ የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ የሕይወት ዑደት ቋሚ ንብረት አስተዳደርና ውጤታማ የግዥ ሥርዓትን ጨምሮ ለመሠረተ ልማት አመራርና አገልግሎት አቅርቦት ሁልአቀፍ የአሠራር ስልት አካል ነው፡፡ ይኸውም በግዥ የአሣታፊ ውሳኔ አሠጣጥ መርህ የሚመራ ነው፡፡

በትይዩ ግልፅ፣ ውጤታማና ቀልጣፋ የሀብት አጠቃቀምን ለማሣደግና በመጨረሻም በተሻሻለ የአገልግሎት አቅርቦት ምክንያት የሚገኘውን ገቢ ለማጐልበት አዲስ የፋይናንስ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ አዳዲስ የአሠራር ማሻሻያ ሥራ ላይ መዋል ካለበት የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ እና የፋይናንስ አመራር ተቀናጅተው መሥራት አለባቸው፡፡



ስዕል 5፡- በካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ የሚተገበሩ የመልካም አስተዳደር መርሆዎች

የሕይወት ዑደት የመሠረተልማት አስተደደር (አመራር) የንብረቱን የአገልግሎት ዘመን ለማራዘም ሲባል የጥገና ዕቅድን ለማዘጋጀት መሣሪያ ነው፡፡

የሥልጣን ተዋረድ (Subsidiarity) ዝቅተኛው የአስተዳደር ዕርከን የሥራ ኃላፊነት ሊኖረው የሚችልበት አሠራር ሲሆን ይህም በዝቅተኛው ዕርከን የአካባቢ የመንገድ ግንባታና በፌደራል ደረጃ ደግሞ የብሔራዊ መከላከያን ማየት ይቻላል፡፡

ውጤታማነት (Efficiency) ጊዜን/ጥረትን በተገቢው መጠቀም ለምሳሌ ከአስፖ'ልት ይልቅ የኰብልስቶን መንገድ ሥራን ማጠናከር በወጪ ደረጃ አዋጭ ሲሆን በአገልግሎት ዘመንም የላቀ ነው፡፡

ተፈላጊ ውጤት ላይ መድረስ (Effectiveness) ማለት አንድ ሀብት የተፈለገውን ዓላማ ለማሣካት የማስቻል ደረጃው ነው፡፡

የሕግ የበላይነት ማለት ማንም ከሕግ በላይ አለመሆኑና ሌላውም ከሕግ ጥሰት ውጭ (ሕግን ሳይጥስ) የማይቀጣበት ሕጋዊ መሠረት ነው፡፡

ዘላቂነት ለረጅም ጊዜ የደህንነት አጠባበቅ ዕድል (ተስፋ) ሆኖ ይህም ከባቢያዊ፣ ኢኰኖሚያዊና ማህበራዊ ገፅታዎች አሉት፡፡

ፍትሃዊነት የምክንያታዊነት (ሚዛናዊነት) አስተሳሰብ ሲሆን በተለይም በኢኰኖሚክስ በታክስ አጣጣልና ደህንነት ኢኰኖሚክስ ይገለፃል፡፡

ተሣትፎ ሕዝቦች በፖ'ለቲካ፣ በኢኰኖሚ፣ በአመራር ወይም ሌላ ማህበራዊ ውሳኔዎች ጫና ማሣደር የሚችሉባቸውን ልዩ - ልዩ መንገዶች ያካትታል፡፡

ግልፅነት ከተማው በሚሠራቸው ተግባራት ዙሪያ የዜጐችን የመረጃ ተደራሽነት የሚፈቅድ አሠራር ነው፡፡

ተጠያቂነት ኃላፊነትን መሠረት ያደረገ ተጠያቂነትንና መልስ ሰጭነትን ያጠቃለለ ነው፡፡

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ከየትኛው የከተማዋ የዕቅድ ሥርዓት ውስጥ ይዋሐዳል?

ሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች ስትራቴጅካዊ የልማት ዓላማዎችና መዋቅራዊ ፕላንን ያካተተ የልማት ዕቅድ አላቸው፡፡ የከተማ ዕድገት ፕላኖች ፊዚካላዊና ስፖሻል ዓላማዎች አሏቸው፡፡

ከዚሁ ጋር ደግሞ የከተሞችን መሪ ዓላማዎች ለምሳሌ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ልማትን ያመላከተ የፌደራል መንግስት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አለ፡፡

እያንዳንዱ ከተማ ከባቢያዊና ሀገራዊ ዓላማዎችን ያዋሀደ የ5 ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲያዘጋጅ ይፈለጋል፡፡ ይህ ፕላን ደግሞ ወደየከተማዋ ሴክተር ጽ/ቤቶች ዓመታዊ የድርጊት መርሃግብር ይለወጣል፡፡



ስዕል. 6፡- ከስትራቴጅ ወደ ትግበራ የከተማ ዕቅድ ሥርዓት

ቁልፍ፡-'ዕትዕ' ማለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ነው፡፡

2. ገቢን የማሣደግ ዕቅድ (ገማዕ)ና የመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ (መሠ/ል/አ/ዕ)

የገቢ ማሣደግ ዕቅድ (ገማዕ) ከተማዋ ከ3-5 ባሉት ዓመታት ከሀብት ምንጮቿ ምን ያህል ገቢን ማመንጨት እንደምትችል ያሣያል፡፡ ቁልፉ ውጤት የቀጣይ 3 ዓመታት የካፒታል መዋዕለንዋይ በጀት እንዲሁም ከተማዋ እንዴት ገቢን እንደምትሰበስብ የሚያመላክተው የገቢ አሰባሰብ ዕቅድ ነው (ክፍል 2ን ተመልከት)፡፡

ይሁን እንጅ ሌሎች ምንጮች ማለትም ድጎማ፣ የሕዝብ አስተዋጽኦና ብድር ያሉት ለካፒታል በጀት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ ከንቲባው፣ የገቢዎች ባለሥልጣንና የገንዘብና ኢኮ/ል/ጽ/ቤት በከተማዋ የገቢ ምንጮች ላይ የተሻለ ዕውቅና አላቸው፡፡ እናም የካፒታል በጀትን ለማዘጋጀት መካተት አለባቸው፡፡

የመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ (መሠ/ል/አ/ዕ) ስትራቴጅካዊ ዓላማዎችን ወደተጨባጭ የፕሮጀክት ሐሳቦች ማለትም ወደ መሠረተ ልማት ማስፋፋት፣ ወይም የአንድ ጊዜ መዋዕለንዋይ (የመኪና ግዥ) ይለውጣል (ክፍል 3ን ተመልከት)፡፡

የ'መሠ/ል/አ/ዕ' ሁለተኛ ሥራ ከጥገና በጀት ጋር የሚጠቃለለውን የጥገና ፍላጎቶችንና ወጪዎችን በመወሰን ያለውን መሠረተልማት ማስተዳደር ነው (ክፍል 4)፡፡

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ከነዚህ ሁለቱ ፕላኖች ይመነጫል፡፡ ቁልፍ ተግባራቸውም የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድን ከከተማዋ የፊዚካልና ፋይናንስ ዓላማዎች ጋር ማስተሳሰር ነው (ሁሉም ዕቅዶች በሁሉም ከተሞች ገና አልተጀመሩም)፡፡

3. አሣታፊ ሂደት

ከ'ገቢ ማሣደግ ዕቅድ' እና ከ'መሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ' የሚገኘው ውጤት የነዋሪው ሕዝብ ቀዳሚ ፍላጎቶች ወደሚወሰኑበት ሂደት ውስጥ ይጠቃለላል (ይገባል)፡፡ ይህም በነዋሪው ሕዝብ ተሣትፎ (ክፍል 5) የሚመራ አሣታፊ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የመጨረሻው ዶኪመንት ተጠናቆ (አልቆለት) ከመቅረቡ በፊት መከናወን አለበት ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ የመሠረተልማት ፍላጎት ካለው ሀብት ጋር ስለማይጣጣም ነው፡፡ በገቢ ማሣደግ ዕቅድ ከተገለፀው የፕሮጀክት ጥናት በተጨማሪ ስለካፒታል በጀት አጠቃቀም ሌሎች ሐሳቦችም ከአካባቢ የፖለቲካ ሰዎች፣ አግባብ ያላቸው መምሪያዎችና ሌሎች አጋር አካላት በተለይም ከነዋሪዎች ሊመነጩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ሶስቱ ዕቅዶች ማለትም የ'ገቢ ማሣደግ ዕቅድና'፣ የ'መሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ' እና የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' መተሣሠርና ተመሳሳይ ውጤትን መስጠት አለባቸው፡፡



ስዕል 7፡-'የገቢ ማሰባሰብ ዕቅድ'ንና 'የመሠረተልማት አስተዳደር ዐቅድ'ን ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደትና ከ' ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' ጋር እንዴት ማሥተሣሠር እንደሚቻል

'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' ፈርጀ - ብዙ ሂደት

የካፒታል መዋዕለንዋይ ውሳኔ አሰጣጥ ፈርጀብዙ ሂደት ነው፡፡ ከእያንዳንዱ ተጨማሪ ሂደት ጋር ፕሮጀክቱ በጣም ተጨባጭ እየሆነ ይመጣል፡፡ በሂደቱ መጀመሪያ ላይ ከተማው የፕሮጀክት ፍላጐት መግለጫ ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡ በመጨረሻም አዋጭ የሆኑ የፀደቁ ፕሮጀክቶች ይገኛሉ፡፡ ከመነሻ እስከ መድረሻ ባለው አጠቃላይ የውሳኔ አሠጣጥ ሂደት ቀጣይነት ያለው የአጋር አካላት ተሣትፎ መጠበቅ አለበት፡፡



ስዕል 8፡ የካሙዕ ፈርጀ ብዙ ሂደት

አስተባባሪ ኮሚቴው የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉት፡-

- ያለውን ሀብት መረጃ መሰብሰብና ከፋይናንስ/ገቢዎች ባለሥልጣን የወደፊት ትንበያን መያዝ ፣
- የጽ/ቤቶችን የመዋዕለንዋይ ፍላጐቶች መረጃ ከካቢኔው መሰብሰብ ፣
- ቅድሚያ የሚሰጣቸዉን ፕሮጀክቶችን ከከተማው ስትራቴጅካዊ ግቦችና ካለው ሀብት አንፃር በማመሳከር መከለስ፡፡
- የውጭ አጋሮችን ማማከርና የነዋሪውን አሣታፊ ሂደት አቅጣጫ ማስያዝ ፣
- የ" የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ" ዝግጅትን፣ አተገባበርና የቢሮ ሪፖርት አቀራረብን መከታተል ፣
- "የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ" ከ'መሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ ' እና 'የገቢ ማሠባሰብ ዕቅድ' ጋር በዘላቂነት መቀናጀቱን የሚያረጋግጡ ዕቅዶችን ማስተሣሠር፣
- የ" የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ"ን በከተማ ም/ቤቱ ማፀደቅ ፣

የቴክኒክ ኮሚቴው ኃላፊነት የሚከተሉት ናቸው

- "የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ"ንና ሌሎች ለፕሮጀክት ትግበራ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ንደፍ፣
- ለፕሮጀክት ትግበራ የሚረዱ ሌሎች ሰነዶችንና የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድን ንደፍ፣
- ዝርዝር ዲዛይኖችንና ቴክኒካል ስፔስፊኬሺኖችን እንዲሁም የጨረታ ሰነዶችን ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት አዘጋጅ፣
- የገንዘብ ፍሰትና የግዥ ዕቅዶችን ተከትሎ የዕቃዎችን ግዥ አዘጋጅና ተግብር ፣
- ሂደቱን፣ ጥራቱንና ከዲዛይንና ከግንባታው የገንዘብ ፍሰት ጋር መጣጣሙን ተከታተል ፣
- የሁሉንም ጠቃሚ ሰነዶች የሚጠብቅ የመዝገብ ቤት ሥርዓት ይኑርህ፣
- የቁጥጥርና ግምገማ ሥርዓትን ዘርጋ፣ ተከታተል፣ ሪፖርቶችንም አዘጋጅ፣
- የአቅም ክፍተቶችንና የሥልጠና ፍላጐቶችን ለይ፣ እጥረቶችንም ለመሙላት ርምጃዎችን ውሰድ፣
- ተገቢ የመረጃ ፍሰትን ለማረጋገጥ ፈጣን የሆነ የላይና ታችና የጐንዮሽ ግንኙቶችን ዘርጋ፣

4. "የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ " ክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ

የ" የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ" ዝግጅትና ትግበራ የነዋሪዎችን ፍላጐት ከከተማው ዓላማዎች ጋር የሚያቀናጀው የከንቲባው ቀጥታ ኃላፊነት ነው፡፡

ካቢኔው የመዋዕለንዋይ ፍላጐቶችን አካቶ የየራሱን ጽ/ቤቶች በጀትና የድርጊት መርሀግብሮች ያዘጋጃል፡፡ የካቢኔ አባል የሆነው የከተማ ሥራ አስኪያጅ ከ90% በላይ ለሚሆነው የከተማዋ መዋዕለንዋይ ኃላፊ ነው፡፡ እናም በ" ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ" ሂደት ውስጥ ዘልቆ መግባት ይጠበቅበታል፡፡ የፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (ፋኢልድ) ኃላፊ ታሣቢ (የተገመተውን) የመዋዕለንዋይ በጀት ለ' ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ'ያቀርባል፡፡ በዝግጅቱም ላይ ወሳኝ ድርሻ ይወስዳል፡፡

ከንቲባው፣ የከተማ ሥ/አስኪያጅና የፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ኃላፊ ቁልፍ የ"ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ" አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፡፡ አስተባባሪ ኮሚቴው የ"ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ"ን ቴክኒካዊ ዝግጅት ለመከታተል በዝግጅቱ ጊዜ መደበኛ ስብሰባዎችን ማካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ አስተባባሪ ኮሚቴው በሂደቱ መጀመሪያ ላይ መገኘትና ከመሠረተልማት አስተባባሪው ተመክሮ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

5. የ "የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ " ዝግጅት የቴክኒክ ኮሚቴ

የመሠረተልማት አስተባባሪው ስትሪንግ ኮሚቴውን በቴክኒክ ምክር መደገፍ አለበት፡፡ አስተባባሪው ከከተማ አስተዳደሩ የተውጣጡ ልዩ- ልዩ ባለሙያዎች እንደ የመሠረተልማት አስተዳደር ባለሙያ፣ የክትትልና ቁጥጥር ባለሙያ፣ የአካባቢ (Environment) ግዥ ባለሙያዎች፣ የፋይናንስ አመራር (ሥ/አስኪያጅ)፣ የውስጥ ኦዲተርና የፕሮጀክት ኢንጅነር የሚገኙበትን ኮሚቴ ይመራል፡፡ በዶኩመንት ሲዲው በትይዩ የተቀረፀ ዝክረተግባራት ይገኛሉ፡፡

6. የ "የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ" ሂደት ዑደት

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድን ለማዘጋጀት ዋና- ዋና ደረጃዎች፡-

አንደኛ - የፕሮጀክት ጥናቶችን ዝርዝር አዘጋጅ ፣
ሁለተኛ - የነዋሪዎችን ፍላጐት ለመወሰን የመጀመሪያ አሣታፊ ምክክር አካሂድ ፣
ሶስተኛ - ፕሮጀክቶችንከታቀደውጤታቸው አንፃር ገምግም፣ አዋህድ (አስተሣሥር)
አራተኛ - ከነዋሪ አጋር አካላት ጋር ሁለተኛ አሣታፊ ምክክር አካሂድ ፣
አምስተኛ - "የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ"ን አቀናጅ፣ ሁሉንም ዕዝሎችም አዘጋጅ፣
ስድስተኛ - በከተማ ም/ቤቱ ለማፀደቅና ለሕዝብ ሥርጭት የተቀናጁ ዶኪመንቶችን አቅርብ፣

"የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ" = የኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ከማለቁ በፊት (ሰኔ 30) በከተማ ም/ቤቱ መጽደቅ አለበት፡፡ ስለዚህም የበጀት ጥሪ እንደ 'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' የመጀመሪያ ሂደት በበጀት ዓመቱ አስቀድሞ መታወጅ አለበት፡፡ ከዚያ በኋላ የከተማ አስተዳደሩ የመጨረሻ ውጤቱን ለም/ቤቱ በወቅቱ ለማቅረብ የድርጊት መርሀግብሩን በጥብቅ መከተል አለበት፡፡ ስዕላዊ መግለጫ - 9 ሂደቱን ያብራራዋል፡፡

የከሙዕ ኡደት



ስዕል 9 የከሙዕ ኡደት

የየከተማ አካባቢ አስተዳደር የልማት ፕሮጀክት

የከተማ አካባቢ አስተዳደር የልማት ፕሮጀክት (ULGDP) በGIZ (የቀድሞው ጅቲዜድ) የሚደገፍ የከተማ ል/ኮን/ሚንስትርና የዓለም ባንክ የጋራ ፕሮጀክት ነው፡፡ 'ULGDP' 'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ'ን፣ የ'መሠረ/ልማ/አስ/ዕቅድ' እና 'የገቢ ማሣደጊያ ዕቅድ'ን በኢትዮጵያ ለሙከራ በተመረጡ 19 ከተሞች አስዋውቋል፡፡ ፕሮጀክቱ አሃዛዊ የሂሳብ አያያዝና 'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ' ያሉ የአጭር ጊዜ ዓላማዎችን አሣክቷል፡፡ በተጨማሪም 'ULGDP' የለውጡን ሂደት ለመዳሰስ የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ ጐን ለጐንም 'GIZ' የተሻሻለ የፋይናንስ አመራር ሥርዓት አስተዋውቋል፡፡ 5 ዋና- ዋና ክፍሎቹም፡-

1. ለከተማ አስተዳደሩ የከተማ ፋይናንስ አስተዳደር ደንቦችን፣ የታሪፍ ደንቦችን፣ የገቢ ማሣደግ መመሪያዎችን እና የግዥ መመሪያዎችን የሕግ መሠረቶች ማዘጋጀት፣
2. ለከተማ አስተዳደሩ አንድ በጀት የማዘጋጀት ክህሎትን ጨምሮ የተሻሻለ ካሽን መሠረት ያደረገ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት በወጭ ማዕከላት ተንትኖ ለከተማ አስተዳደሩ ማስተዋወቅ፣
3. ውዝፍን በማስወገድ ሂሳብ መዝጋትን፣ ወቅታዊ የፋይናንስ መግለጫዎችን፣ የውጭና የውስጥ ኦዲትን የማስረፅ (የማስኬድ)
4. ለካሽ፣ ለመምሪያዎችና ለመዋዕለንዋይ የንብረት ግዢን ጨምሮ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣
5. ዓመታዊ ወቅታዊ የገቢ ማሣደግ ዕቅድን ማዘጋጀት፣

ክፍል 2

የካፒታል መዋዕለንዋይ በጀት

የከተማ የካፒታል መዋዕለንዋይ በጀት ለመዋዕለንዋይ ምን ያህል ገንዘብ እንዳለ ለመግለፅ ይረዳል፡፡

የበጀት ስሌቱን ለመስራት ከተሞች የራሳቸውን ገቢ፣ መደበኛ ወጭና የውጭና የወጭ ምንጮችን መተንበይ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህም ባብዛኛው ያለፈ አፈፃፀምን በመቃኘት የሚከናወን ነው፡፡ የካፒታል በጀት ዝግጅት በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የገቢ ማሣደግ ዕቅድን በኃላፊነት ከሚመራው የገቢዎች ባስልጣን ጋር በመተባበር ያቀናጃል (ያቀናብራል)፡፡ ይሁንና በተወሰኑ ከተሞች የገቢ ማሣደግ ዕቅድ ገና አልታወቀም (አልተለመደም)፡፡ ስለዚህ ይህ ክፍል ካፒታል በጀትን ያለገቢ ማሣደግ ዕቅድ እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል ጠቅለል ያለ መነሻ ይሠጣል፡፡

ደረጃ 1- መጭውን ለመተንበይ ያለፈውን ፈትሽ

የገቢ አሰባሰብን ወይም ወጭን ለመተንበይ ከተማዋ ያለፈ ተሞክሮዋን መቀመር ይኖርባታል፡፡ መጭውን ለመተንበይ የመጀመሪያው ደረጃ ካለፉት 3 ዓመታት ትክክለኛ መረጃ መውሰድና ከዚያ ተነስቶ ምክንያታዊ መደምደሚያ ላይ መድረስ ነው፡፡ የከተማዋን አፈፃፀም ለመገምገም ያለፉት ዓመታት 3 ዓይነት የፋይናንስ መረጃዎች ጠቃሚ ናቸው፡-

1. የተሰበሰበ የራስ ገቢ መጠን (የማዘጋጃ ቤት ገቢ)
2. የመደበኛ ወጭ መጠን (የሥራ ማስኬጃ ወጭ)
3. የካፒታል ወጭዎች (ልዩ- ልዩ የመዋዕለንዋይ ፍሰቶች)

ለቁጥጥር ሥራና ትክክለኛ መረጃን ለማግኘት ሲባል ያለፈ ጊዜ ገቢና ወጭዎችን ለማመልከት አዲሱን የሒሳብ አርዕስት ተመልከት (ሲዲ ዕዝል 1.3)

በመጀመሪያ ያለፈውን የራስ ገቢዎች የሂሳብ አርዕስቱን ቁጥሮች በቅደም ተከተል በማየት አስላ፡፡ እናም የማዘጋጃ ቤት ግብሮችና ክፍያዎች ብቻ አግባብ አላቸው፡፡ ይህም፡-

- ከአገልግሎት የሚሰበሰቡ የግብር ገቢዎች
- (ቁ. 1701 - 1719)
- ኪራይና ሙዋለንዋይ (ቁ. 1720 - 1730)
- የአገልግሎት ክፍያዎች (ቁ. 1740 - 1749)
- ሽያጭ (ቁ. 1750 - 1789)
- የከተማ መሬት ሊዝ ገቢ (ቁ. 1731)

ሁለተኛ - ያለፈውን ጊዜ መደበኛ ወጭዎች ዝርዝር ይህም ማዘጋጃ ቤታዊ ወጭዎችን (500 ተከታታይ) ሆኖ፡-

- የሠራተኛ ደመወዝ (6100 ተከታታይ)
- ሸቀጦችና አገልግሎቶች (6200 ተከታታይ)
- የካፒታል መዋዕለንዋይን ሳይጨምር ከንብረት አስተዳደር ዕቅድ (ቋሚ ዕቃና ግንባታ) የመነጨው የጥገና በጀት (6245 ተከታታይ)
- ድጐማ፣ ስጦታና ክፍያዎች (6400 ተከታታይ)

ስዕል 10፡- መጭውን ለመተንበይ ያለፈውን ቃኝ

ገምት (ምክንያታዊ ትንታኔ ስጥ)

የአንድን ተለዋዋጭ ዋጋ (ሀ) ከሚታወቅ መነሻ ተነስተህ በምክንያታዊ ትንተና (ሀ) ከሚታወቀው ዕውነታ ባሻገር የት ሊደርስ እንደሚችል መገመት፣

የራስ ገቢዎች ከግብር፣ ኪራይና ከማ/ቤት አገልግሎት የሚሰበሰቡ ገቢዎች፣ ከከተማ መሬት ሊዝና ንብረት ወይም አገልግሎት ሺያጭ የሚገኙት ናቸው፡፡ እነዚህ ገቢዎች ለክልሉ የገንዘብና/ኢ ከነማ/ልማት/ቢሮ ፈሰስ እንደሚደረጉት የመንግስት ገቢዎች ሳይሆኑ በከተማው ግምጃ ቤት የሚቀሩ ናቸው፡፡

መደበኛ ወጭዎች የሚባሉት የማስፈፀሚያ ወጭዎች ናቸው፡፡ እነዚህ በአጠቃላይ በራስ ገቢ ይሸፈናሉ፡፡ የመንግስታዊ ተግባራት ወጭዎች (የመምሕራን ደሞዝ --- ወዘተ) ከክልሉ በሚገኝ ጥቅል ፈንድ ይሸፈናሉ እናም የመደበኛ ወጭዎች አካል አይደሉም፡፡

አዲሱ የሂሳብ አርዕስት የአመዘጋገብ ሥራን መልክ የሚያስይዝና ገላጭ የሆነ ባለኮድ የሂሳብ አያያዝ መስመሮች ስብስብ ነው፡፡ የታቀደና ትክክለኛ የወጭዎችና የገቢዎችን ደረጃ ከሁሉም መንግስታዊ ተቋማት ይለያል፡፡ ለከተሞች የሚከተሉት መስመሮች ብቻ ጠቃሚ ናቸው፡- የራስ (የማዘጋጃ ቤቱ) ገቢዎች በ1700 ተከታታይ ሥር ይመዘገባሉ፡፡ መደበኛ ወጭዎች ግን ከ6100 - 6400 ባሉት የ500 ተከታታዮች የበጀት መስመሮች ሥር ይመዘገባል፡፡ የ6300 ተከታታዮች መዋዕለንዋይ ይባላሉ፡፡ እኒህም የቋሚ ንብረት፣ የመሠረተልማት ግንባታ፣ የዕቃዎችና የምክር አገልግሎቶች ወጭዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የመሬት ሊዝ ገቢ (ቁ.1731) ፡- የኢትዮጵያ የከተሞች አዋጅ 90% የመሬት ሊዝ ገቢ ለካፒታል መዋዕለንዋይና 10% ብቻ ለመደበኛ ወጭዎች መዋል እንዳለበት ይገልፃል፡፡

የጥገና ወጭ በጀት፡-የመሠረተልማት ጥገና ወጭዎች መጠነኛ የንብረት ጥገናና ማሻሻያ ወጭዎችን ጨምሮ በሂሳብ መስመር 6245 ሥር እንደመደበኛ ወጭ ይመዘገባሉ፡፡ ይህም ከመሠረተልማት መልሶ የማሻሻል፣ ዕድሳትና የደረጃ ለውጥ ማለትም በ'ካፒታል መዋዕለንዋይ' የካፒታል መዋዕለንዋይ ሥራ ከሚገልፀው ይለያል፡፡

ጥቅልና የተጣራ መረጃ

ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የሚገኝ እና ወደ ‘Excel’ሠንጠረዥ የሚገቡ የገቢ መረጃዎች ትክክለኛ አኃዞችና ጥቅል አኃዞች ተብለው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ነገር ግን አኃዞች በወቅታዊ የኢትዮጵያ ብር የግሽበት ምጣኔና ዓመታዊ የከተማ ሕዝብ ዕድገት ምጣኔ አንፃር መፈተሽ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም የተጣሩ አኃዞች የከተማውን ዓመታዊ አፈፃፀም የተሻለ ገጽታ ስለሚያሣዩ ነው፡፡

ለምሣሌ አንድ ከተማ አጠቃላይ ገቢዋን በ15% በዓመት ጨመረች እንበል፡፡ ዓመታዊ የግሽበት ምጣኔ (5% በዓመት) እና የከተማውን ሕዝብ የዕድገት ምጣኔ (5% በዓመት) ስናይ የተጣራ የገቢ ጭማሪ 5% ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ነው ከተማዋ ዓመታዊ የግሽበት ምጣኔንና የሕዝብ ዕድገትን በአውቶማቲክ ቴምፕሌቱ እንድትገልፅ የምትጠየቀው፡፡ የቁጥጥር ቴምፕሌቱ ግራፎች ጥቅል ገቢንና የተጣራ ለውጥን ያሣያሉ (ክፍል ‘8’ን ተመልከት)፡፡



ስዕል 11፡- ጥቅልና የተጣራ መረጃን የሚያወዳድር የቁጥጥር ቴምፕሌት ምሣሌ

ሶስተኛ- የጥገና ወጭን ሳይጨምር በ”መሠረተልማት ግንባታዎች” ሥራ በ6300 ተከታታይ (ቅደም - ተከተል) ያለፈ ጊዜ መዋዕለንዋዮችን አመልከት፡፡

በ’MS Excel’ ቴምፕሌት ሠንጠረዥ የተጠቀሱ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን፣ ዕቃዎችንና የምክር አገልግሎቶችን በማካተት ሁሉንም የካፒታል መዋዕለንዋዮች ዘርዝር፡፡ (ሲዲ ዕዝሎችንና ቴምፕሌት ስክሪን ተመልከት)

የተወሰኑ ቁጥሮች ለስሌት ያስቸግሩ ይሆናል በተለይም ከተሞቹ ገና “ካመኢ”ን ሊጀምሩ ሲነሱ፡፡ ይሁንና የገንዘብና ኢኮነሚ ልማት /ጽ/ቤት በተከታታይ የፋይናንስ ሪፖርት ለክልሉ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡ አዲሱን በኮምፒዩተር ቴክኖሎጅ የታገዘ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት (IBEX) በመጠቀም ላይ ያሉ ከተሞች ሁሉም መረጃ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ አንዳንዴ ይህ መረጃ ያሉፉትን ለገንዘብና ኢኰኖሚ ልማት ቢሮ የተላለፉ ዓመታዊ የፋይናንስ ሪፖርቶች በመፈተሽ ሊገኝ ይችላል፡፡

ደረጃ 2 - ገቢን፣ መደበኛ ወጭንና ሥራ ላይ የሚውል ትርፍን (Operating Surplus) ተንብይ፡፡

በጀትን ለመተንበይ 3 መንገዶች አሉ፤ አቅምን መተንተን፣ ፍላጐትን መተንተንና አፈፃፀምን መተንተን ናቸው፡፡ የነዚህ ሶስት አስተሳሰቦች ቅንጅት የገቢና ወጭዎች ትንበያ መሠረት ነው፡፡

የአቅም ትንተና ትክክለኛ አፈፃፀም ባለፈ ጊዜ ትንተና ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ወጭው የታቀደ ገቢና ወጭን ያሣያል፡፡ የወደፊት ውጤቶችን ለመገመት ካለፈው አፈፃፀም ግኝት በመነሣት በጀቶችን ተንብይ፡፡ ነገር ግን በጀቶች ተለዋዋጭ ናቸው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱን ሁኔታ በሂሳብ አርዕስቱ ላይ በተናጠል ፈትሽ

ስዕል 12፡- የካፒታል መዋዕለንዋይ በጀት ዝግጅት ምክንያታዊነት

የፍላጐት ትንተና፡- በማደግ ላይ ያሉ ከተሞች በገንዘብ መልክ ሊሰሉ የሚችሉ መሠረተልማትና ሌሎች መዋዕለንዋዮች ይፈልጋሉ፡፡ የከተማ ፋይናንስ ፍላጐት ከንብረት አስተዳደር ዕቅድ ይመነጫል (ዕዝሎች 3.2 ተመልከት)፡፡ የገቢ ማሣደግ ዕቅድ የገቢ ፍላጐቶችን ለማስላት 'ካመዕ'ን ተጠቀም፡፡

የአፈፃፀም ትንተና፡- መንግሥት የከተሞችን የወደፊት መደበኛና ካፒታል ወጭዎች ለመሸፈን ከተሞች ቢያንስ ዓመታዊ ገቢያቸውን በ30% እንዲያሳድጉ ይፈልጋል፡፡ ይህን መመሪያ ሥራ ላይ ለማዋል ያለፈ አፈፃፀምና የአሁኑን አቅም ፈትሺ፡፡ በራስ ገቢና ወጭ መካከል ያለው ልዩነት የሥራ ማስፈፀሚያ ትርፍ (የተጣራ የከተማ ገቢ) ይባላል፡፡

ይህም ከተማዋ የካፒታል ገቢ ያደረገችው የራስ አስተዋጽኦ ነው፡፡ የካፒታል መዋዕለንዋይ በጀት በአብዛኛው በከተማዋ የገቢ አሰባሰብ ችሎታና መደበኛ ወጭዎች ከፍተኛ ጥቅምን በሚያስገኙበት ሁኔታ የመጠቀም ብቃት ላይ ይመሠረታል፡፡ ስለበጀት ጉዳይ ከፈርጀ - ብዙ የበጀት ትንበያ ሠንጠረዥ (ሠንጠረዥ 3 'MS Excel' ቴምፕሌት) ጋር ተይዞ ዝርዝር ጉዳዮች በሂሳብ አርዕስቱ (ዕዝሎች 1.3) ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ይሁንና የጥገና በጀት (ቋሚ ንብረቶችና ግንባታዎች ቁ. 6245 ከ500 ውስጥ) ከንብረት አስተዳደር ዕቅድ ይመነጫል፡፡ እናም ለብቻው መዘጋጀት አለበት(ክፍል 4)፡፡

ደረጃ 3 - የካፒታል ገቢዎች

የካፒታል በጀት ከሥራ ማስፈፀሚያ ትርፍ በተጨማሪ ሌሎች የካፒታል ገቢዎችን ያካትታል፡፡ ይኸውም፡-

- 90% የከተማ መሬት የሊዝ ገቢ (የሂሳብ አርዕስት መስመር ቁ.1731)
- መያድና የግል አስተዋጽኦ (ሂሣ/አ/መ/ቁ 1732 እና 1733)
- የአንድ ጊዜ ንብረት ሽያጭ (መስመር 1791)
- የማህበረሰብ አስተዋፅኦና ሌላ የካፒታል ገቢ (መስመር 1792 - 1799)
- ለካፒታል መዋዕለንዋይ የክልል ጥቅል ድጐማ (መ. 1622)
- የረጅ ድርጅቶች ድጐማ/ተዛማጅ ፈንድን ሣያካትት (መ 2000 - 2999)
- የመንገድ ፈንድ (መ 1604)
- ሌሎች የካፒታል ገቢዎችና ባለፈው ዓመት ጥቅም ላይ ያልዋለ ሀብት (የሂ/አርዕስት/መስመር ቁጥር የሌለው) በመጭው ቅርብ ጊዜ ውስጥ ከተሞች ግዙፍና በራሳቸው የካፒታል በጀት ሊሸፈን የማይችል መዋዕለንዋይ ይፈልጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ከተሞች በባንክ ብድር መልክ ሀብቶችን መበደር አለባቸው፡፡ በደንብ ለማብራራት ከተሞች "ብድርን የመመለስ አቅም ያላቸው" ይሆናሉ ማለትም ዓመታዊ የገቢ አፈፃፀማቸውንና በመያዣነት ሊያገለግል የሚችል ንብረት መሠረተ ልማትና ተንቀሳቃሽ ንብረትን በምሣሌነት ሊያሣዩ ይችላሉ፡፡

የገቢ ማሣደግ ዕቅድ

- የከተማዋ የራስ ገቢ የካፒታል መዋዕለንዋዩን ትልቅ ድርሻ ይወስዳል፡፡ ስለዚህ ከተሞች የገቢ አሰባሰብ አቅማቸውን የገቢ ማሣደግ ዕቅድን (ሲዲ ዕዝል 3.1) በመተግበር እንዲያሣድጉ ይጠየቃሉ፡፡ የ'ገቢ ማሣደግ ዕቅድ' ቁልፍ ተግባር ፈርጀ ብዙ የበጀት ትንበያን በሚከተለው አኳኋን ማዘጋጀት ነው፡-
- ያሉትን የራስ ገቢዎች ለመለየትና ለሕዝቡ አገልግሎቶችን በብቃት ለማቅረብ የከተማዋን ነባራዊ መደበኛ ወጭዎች መዳሰስ ፣
- የከተማዋ የገቢ አሰባሰብ ተፈላጊ የመሠረተልማትና የአገልግሎት ወጭዎችን እንዴት እንደሚሸፍን መቀመር፣
- የገቢ አሰባሰብዎን በማሣደግ ላይ አትኩሮ ለመጭዎቹ 3 ዓመታት ገቢና ወጭን ማቀድ፡ - የገቢ መሠረትን የማሣደግ ምክንያቶች አዲስ የታሪፍ ደንቦችን፣ የአሰባሰብ ብቃትንና የደሞዝና የአገልግሎት ወጭዎችን መቀነስን ያካትታሉ፡፡ ሁለም ይህ መረጃ ወደ 'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' ይገባል፡፡ ዓላማው የሕዝብ መዋዕለንዋዮችን አወንታዊ ዑደት ለመፍጠር፣ የግሉን መዋዕለንዋይና የመሬት ዋጋ ለማሣደግና በተራው የከተማዋን የገቢ መሠረት ለመጨመር ነው ይህ ያደገው ገቢም እያደገ ለሚሄድ መዋዕለንዋይ አቅም ይሆናል፡፡

ክፍል 3

የፕሮጀክት ጥናቶችን መቅረጽ

ይህ ክፍል የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ የፕሮጀክት ጥናት ዝርዝር እንዴት እንደሚዘጋጅ ያስረዳል፡፡ የዚህ ዝርዝር ዋና ዓላማ የመሠረተልማት ፕሮጀክቶችን ወይም ሌሎች በ" ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ " የካፒታል መዋዕለንዋዮችን ከከተማዋ ስትራቴጅካዊ ግቦች ጋር ማስተሳሰር ነው፡፡

ምሣሌ:-

1. ለመስፋፊያ አካባቢዎች የመንገድ ግንባታ
2. የተማሪ ቅበላ አቅምን ለማሣደግ የሚደረግ የአዳዲስ ት/ቤቶች ግንባታ ወይም ተጨማሪ ክፍሎች ለነባር ት/ቤቶች ግንባታ

ደረጃ 1- የከተማዋን ዓላማዎች መዳሰስ

ሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች አንድ ወይም ሌላ የዕድገት ፕላን አላቸው (መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላን (LDP) ወይም አልፎ - አልፎ የተቀናጀ የዕድገት ፕላን)፡፡ እነዚህ ፕላኖች ስፓሻል ዓላማዎች (እንደ የመስፋፊያ አካባቢ) እና ስትራቴጂካዊ ዓላማዎች (እንደ የድህነት ቅነሣ) አሏቸው፡፡

መዋቅራዊ ፕላን፣ የአካባቢ ልማት ፕላንና ለትንንሽ ከተሞች ደግሞ መሠረታዊ ፕላን የመሳሰሉት ስፓሻል ፕላኖች የከተማ ደረጃ ማሻሻል፣ ማስፋፊያና የመልሶ ማልማት አካባቢዎችን ለይተው ያመላክታሉ፡፡ ሌሎች ፕላኖች የመንገድ መረብና የተፋሰስ ፕላኖች ናቸው፡፡ ስፓሻል ፕላኖች የመሬት አስተዳደር፣ የግንባታ ቁጥጥርና ኮንስትራክሽን ዲዛይን ይወስናሉ፡፡

እነዚህ ጽ/ቤቶች በሕግ ገገርነት ያላቸውን የመዋቅራዊ ፕላንና የአካባቢ ልማት ፕላን አፈፃፀም መቆጣጠርና ማስተባበር አለባቸው፡፡ ሌሎች መምሪያዎች፣ ከንቲባና የከተማ ሥ/ አስኪያጅ እኩል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ስትራቴጂካዊ ፕላኖች እና የዕድገት ፕላኖች የከተማዋን የማህበረ-ኢኮኖሚ ስትራቴጅካዊ ዓላማዎች ለምሣሌ ገቢን ማሣደግ፣ የመሬት ገበያ ልማት ወይም የወጣት ሥራ ፈጠራ የመሣሠሉትን በግልፅ ለይተው ያስቀምጣሉ፡፡ ከተሞች እነዚህን ዓላማዎች ከመንግስት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር በክልልና በፌደራል ደረጃ ማስተሣሠር አለባቸው፡፡

የከተማ አስተዳደሩ ጽ/ቤቶች ስፓሻል ወይም ስትራቴጅካዊ ፕላን የካፒታል መዋዕለንዋይ ፍላጐትን ለመግለፅ መጠቀም አለባቸው፡፡ ጽ/ቤቶች አንዴ የካፒታል ፍላጐታቸውን ከወሰኑ ለክትትል ከከተማ ካቢኔው ሊከፈላቸው ይገባል፡፡



ስዕል 13፡- ስፓሻልና ስትራቴጅክ ዕቅዶችን ከካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ጋር ማስተሳሰር

መዋቅራዊ ፕላኖች በከተማ ፕላን አዋጅ ቁ.574/2001 በሕግ አግባብ ገዥ ዕቅዶች ሲሆኑ የሚከተለውን ያካትታሉ፡-

1. የዕድገትን አቅጣጫና መጠንን
2. ዋና- ዋና የመሬት አጠቃቀም ፈርጆችን
3. የመጠለያ ልማትን
4. ዋና- ዋና የፊስካልና ማህበራዊ መሠረተልማት አደረጃጀትን (በቦታ)
5. የመሀል ከተማ የመልሶ ማልማት ጣልቃ ገብነትን
6. የአካባቢ ደህንነት ጉዳዮችን
7. የኢንዱስትሪ ቀጣናዎችን

የአካባቢ ልማት ፕላን ትግበራን ለማሣለጥ በስትራቴጅካዊ ቦታዎች ላይ በማተኮር ተግባራትን፣ የልማቱን ዓላማዎች፣ የትግበራ ስትራቴጅዎችን፣ የአካባቢ ልማትን፣ የከተማ ዲዛይን መመሪያዎችን፣ ስታንዳርዶችን፣ በጀትንና ወቅታዊነትን ይገልፃል፡፡

የከተማ ደረጃ ማሻሻል፣ ዕድሳትና ማስፋፊያ፡ - ለምሣሌ ጠጠር መንገድን አስመልክቶ የደረጃ ማሻሻል ስንል የጠጠር መንገድን ወደ ኮብልስቶን መለወጥ ማለት ነው፡፡ ማስፋፊያ ማለትም ለመንገድ የተፋሰስ መሥመርን መጨመር ወይም መንገዱን ማስረዘም ማለት ነው፡፡ ዕድሣት ደግሞ እጅግ የተጐዱ ሙሉ የመንገድ ክፍሎችን እንደገና መገንባት ማለት ነው፡፡ ሁሉም የካፒታል መዋዕለንዋይ ክፍሎች ናቸው፡፡

የመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ

- የ’መሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ’ ዓላማ ‘የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ’ን ከከተማዋ ስትራቴጅካዊ ዓላማዎችና የረጅም ጊዜ ሥራና ጥገና ጋር ለማያያዝ ነው፡፡ ስለዚህ የ’መሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ’ ከተማዋ ለእያንዳንዱ መሠረተልማት የጥገና በጀት በመመደብ ነባራዊ የመሠረተልማት ጥገናን እንድታስተዳድር ይረዳታል፡፡ በተጨማሪም የመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ የመልሶ ማሣደግን፣ ማሻሻልና አዲስ የካፒታል መዋዕለንዋይ ፕሮጀክቶችን አስመልክቶ ቀዳሚ የልማት ፍላጎቶችን ያቀርባል፡፡ ለጊዜው ‘የመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ’ ዋናዋና መሠረተልማቶችና የአገልግሎት ሥራዎች ማለትም የከተማዋ የመሠረተልማት (መንገድና የተፋሰስ መረቦች፣ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ሥርዓትና የመንገድ መብራት) ላይ ይወስናል፡፡

- የመሠረተልማት አስተዳደር ዕድቅ ሰነዶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የመሠረተልማት ቆጠራ፣ የሁሉም መሠረተልማቶች ሠንጠረዥና ስፓሻል የመረጃ መረብ ከስፔስፊኬሺንና ከልዩ ባሕርያታቸው ጋር፣
- የመሠረተልማቱን ብልሽት መንሥዔና አሁን ያለበትን ደረጃ የሚገልፅ የመሠረተልማት ሁኔታ፣
- ቀሪውን የመሠረተልማት ዋጋ የሚያሠላ የመሠረተልማት ዋጋና ኪሣራ፣ ጥገናና ዕድሳት ጉድለት በዓመታዊ ሕልቀት ስሌት መሠረት፣
- ተጓዳኝ የመሠረተልማት ጥገና በጀት (ዕድሣትና አዲስ መሠረተልማት የከተማዋን ሁሉንም የመሠረተልማት ዕድገት በሚገልፅ ሁኔታ)
- የመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ ትግበራ ስትራቴጅ ዝርዝር ተግባራትንና በዓመቱ የሚያስፈልግ የበጀት መጠን ጨምሮ

ደረጃ 2 - የፕሮጀክት ጥናቶችን መግለፅ (ይፋ ማድረግ)

ስፓሻል የዕድገት ፕላኖችን ከ’ ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ’ ጋር የሚያቀናጁ ልዩ- ልዩ መንገዶች አሉ፡፡ የፕሮጀክት ጥናት ዝርዝር ሐሳቦችን ለማፍለቅ ከተማው የሚከተለውን ዘዴ ሊጠቀም ይችላል፡፡

ሀ. የበጀት ጥሪ

በጀት የማቅረብ ሥልጣን የፋይናንስና ኢ.ኮ/ል/ጽ/ቤት ሆኖ መጋቢት መጀመሪያ አካባቢ ይታወጃል፡፡ የገ/ኢ./ል/ጽ/ቤት የጽ/ቤት ኃላፊዎችን (የካቢኔ አባላትን) የየመምሪያቸውን ግምታዊ በጀት እንዲያዘጋጁ ለማገዝ ወርክሺት ያዘጋጃል (CD ዕዝል 1 KA/BEMA)፡፡ የበጀት ጥያቄዎች ከተዘጋጁና ከፀደቁ እንዲሁም የበጀት ማስታወቂያ ወጥ በሆነ ፎርማት ከተሠራጨ በኋላ ብቻ ነው ጥያቄዎቹ በኮምፒዩተር ወደተደገፈ የገ/ኢ./ል/መምሪያ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የሚቀናጁት (IBEX)፡፡ በመርህ ደረጃ የሴክተር ጽ/ቤቶች ለገ/ኢ./ል/ጽ/ቤት የመደበኛና ካፒታል በጀት ፍላጎታቸውን በዓመታዊ የድርጊትና ስፓሻል ፕላን አስደግፈው ማቅረብ አለባቸው፡፡ በሌላ አገላለፅ ለመዋዕለንዋይ የፕሮጀክት ጥናቶችን ማቅረብ አለባቸው፡፡ ይሁንና በተግባር የገን/ኢ./ል/ጽ/ቤትና የሴክተር ጽ/ቤቶች ይህንን የአሠራር መስመር ለመከተል የዓቅም ችግር ይታይባቸዋል፡፡

ለ. የመሠረተልማትት አስተዳደር ዕቅድ

የከተማ መሠረተልማት ግንባታ አስተዳደር ዘርፉ እንደመንገድ፣ ተፋሰስ፣ ቄራና የመሳሰሉት አካባቢዎች ያሉት ሁሉም የፊዚካል መሠረተልማት ግንባታ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ ስለሆነም ይህ መምሪያ ከ90% በላይ ለሚሆነው የከተማዋ የካፒታል መዋዕለንዋይ ኃላፊ ነው፡፡ እነዚህ የመዋዕለንዋይ ወይም የልማት ፍላጐቶች በመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ ላይ በግልፅ ተቀምጠዋል፡፡ ስለዚህ በ’መሠረተልማተ አስተዳደር ዕቅድ’ የተፈላጊ ፕሮጀክቶችን ዝርዝር የመልሶ ማቋቋም፣ የደከሙ አካባቢዎችን የደረጃ ማሻሻልና የመስፋፊያ ፕሮጀክቶችን አካትት፡፡

ሐ. የሴክተር ዕቅዶች

በእርግጥ ሁሉም ከተሞች የ’መሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ’ ላይኖራቸው ይችላል፡፡ የፕሮጀክት ጥናቶችን ለማዘጋጀት ሌላው አማራጭ መንገድ ሴክተር ፕላን ከሚባለው ስፓሻል ፕላን መነሣት ነው፡፡ በአገላለጽ ደረጃ እነዚህ ዕቅዶች ከላይ በተጠቀሱት ዕቅዶች ውስጥ መካተት አለባቸው፡፡ የሴክተር ዕቅዶችን ለተለያዩ ዓላማዎች አዘጋጅ፡፡ በአንዳንድ ከተሞች የሚከተሉት ፕላኖች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

- የመንገድ፣ የእግረኛና የሳይክል መንገዶች፣ የሚኒባስ መስመሮችና አልፎም የደረቅ ወደቦች ወይም እንደ አውሮፕላን ማረፊያ ያሉ የብሔራዊ ትራንስፖርት መሠረተልማት የመሣሠሉ የትራንስፖርት ፕላኖች፣
- የተፋሰስ መረቦችና የአፈር ክለት መቆጣጠሪያ መሠረተልማቶች እንዲሁም የደን ልማት ጥብቅ

አካባቢዎች ፕላኖችን የሚያጠቃልሉ የጐርፍ ቁጥጥር ፕላኖች ፤

- የደረቅ/ፍሳሽ ቆሻሻ አስተዳደር ዕቅዶች (የማከማቻ ቦታዎች፣ የገንዳ ማስቀመጫ አካባቢዎች፣ የትራንስፖርት ፍላጐቶችና የመሬት ሙሊትና ተረፈ-ንብረቶችን አዙሮ ለመጠቀም የመምረጫ ቦታዎች እይታን ያካተቱ ፕላኖች)፡፡

እነዘህ ዕቅዶች ሊኖሩ ከሚገቡ ዕቅዶች መካከል ጥቂቶቹን የሚወክሉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ እያንዳንዱ በ" ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ " የፕሮጀክት ጥናት ሊስት ውስጥ የሚካተቱ የካፒታል መዋዕለንዋዮችን ይጨምራል፡፡

መ. የሕዝብ ተሣትፎ

በፅንሰሀሳብ ደረጃ ስፓሻል ዕቅዶች የዜጐችን ፍላጐቶች ማንፀባረቅ ይገባቸዋል፡፡ የዜጐች ተሣትፎ ከስፓሻል ዕቅድ ጀምሮ ከተማ አስተዳደሩ ላይ ቁጥጥር እስከማድረግ ይዘልቃል፡፡ ተሣትፎ ተአማኒነትን ያስገኛል፡፡ በመጨረሻም የተረጋጋ ማህበረሰብን ይፈጥራል፡፡ በዚህ ደረጃ በ" ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ "የዝግጅት ሂደት አሳታፊ ተግባቦትን (የመረጃ ልውውጥን) አካሂድ ይህም፡- እንደቀበሌ ስብሰባዎች፣ መጠይቆችና የአጋር አካላት ቃለመጠይቅ በመሣሰሉት በልዩ ልዩ መንገድ ይፈፀማል (ክፍል 5ን ተመልከት)፡፡

ደረጃ 3 - የፕሮጀክት ዝርዝር

ማናቸውንም ዓይነት ዘዴ ቢቀይስም የከተማ አስተዳደሩ በዚህ ይረዳ የፕሮጀክት ጥናት ዝርዝሩን ሊያጠቃልል የግድ ይላል፡፡የፕሮጀክት ዝርዝሩን ለማጠቃለል ቀጥሎ የተመለከተውን ሠንጠረዥ 1 ፎርማት ተጠቀም፡፡

የተጠናው ፕሮጀክት	ዝርዝር መግለጫ	አስተዋፅኦ	ምንጭ	ግምት
ኮብልስቶን መንገድ	የከተማ ማዕከሉን ከመስፋፊያ አካባቢው ጋር ለማገናኘት ነባሩን የጠጠር መንገድ ማሻሻልና ማስፋፋት	በማስፋፊያ አካባቢውና በከተማ ማዕከሉ መካከል የመኪና ተደራሽነትን መፍጠር	የመሠረ/ል/አ/ዕ እና የከተማዋ መዋቅራዊ ፕላን	2.3ሚ የኢትዮጵያ ብር
የሕዝብ መፀዳጃ ቤት	በአረጀው የከተማ ክፍል መፀዳጃ ቤቶችን መሥራት	የነዋሪዎችን የጤና ጠንቆች መቀነስ	የሕዝብ ተሳትፎ	200,000.00 የኢትዮጵያ ብር
የአካባቢ ልማት ዕቅድ	የአሮጌውን የከተማ ክፍል የአካባቢ ልማት ፕላን በአማካሪ ማሠራት (የመሬት አጠቃቀምና የመንገድ መረብ ፕላንን ጨምሮ)	የይዞታና የፕላን መብትን ማረጋገጥና የግል መዋዕለ ንዋይ ፍሰትንና የኢኮኖሚ ልማትን ማበረታታት	የከተማዋ መዋቅራዊ ፕላን	3.3 ሚ.የኢትዮጵያ ብር
የቆሻሻ ገንዳ መኪና	የከተማ አስተዳደሩ ቆሻሻን ወደመጣያ ቦታ ለማጓጓዝ የገንዳ መኪናን ይፈልጋል፡፡	ጤናማ አካባቢ	የተቀናጀ የቆሻሻ አወጋገድ ዕቅድ	3 ሚ የኢትዮጵያ ብር

ሠንጠረዥ 1፡-የፕሮጀክቶች ዝርዝር ምሣሌ

ክፍል 4

አዋጭነትን ማረጋገጥና የመሠረተልማት አስተዳደር

ይህ ክፍል የተጠኑ ፕሮጀክቶችን እንዴት በአፈፃፀም ቅደም ተከተል እንደሚተነተኑ ይገልፃል፡፡ የፕሮጀክት ዝርዝሮች በአብዛኛው የፍላጐቶች ዝርዝር ናቸው፡፡ ምክንያቱም አንድ ፕሮጀክት ስለተፈለገ ብቻ በተፈለገው ሰዓትና ሁኔታ ሊተገበር አይችልም፡፡ በሌላ አገላለጽ ተፈላጊነት አዋጭነትን አያመላክትም፡፡

ሁሉም የተጠኑ ፕሮጀክቶች የቴክኒክና የፋይናንስ አዋጭነት መሥፈርትን ማሟላት አለባቸው፡፡ ይህ ዳሰሳ (ቅኝት) የመጀመሪያ መነሻ መዋዕለንዋይን፣ የማስፈፀሚያና የጥገና ወጭዎችንና መዋዕለንዋዩ የሚመልሰውን ትርፍ ስሌት ያካትታል፡፡

ዳሰሳው ግምገማንም ያጠቃልላል፡፡ እያንዳንዱ ፕሮጀክት ሊያመጣ ከሚችለው የታቀደ ውጤት፣ ለከተማዋ ዓላማዎች ስኬት ባለው አስተዋፅኦ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖ አንፃር ይገመገማል፡፡

አንዳንድ ፕሮጀክቶች በተለይም ከፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ጋር የተያያዙት ከባቢያዊ እና ማህበራዊ እንድምታ ጥናቶችን ይፈልጋሉ፡፡

ደረጃ 1- የአገልግሎት ዘመን ወጭን አስላ

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ከተሞች የመሠረተልማት ልማትን እንደ "የአንድ ጊዜ" መዋዕለንዋይ ይመለከቱታል፡- የግንባታ ወጭውን ብቻ በማሰብ፡፡ ይሁን እንጅ የመሠረተልማት አውታሮች የተወሰኑ ዓመታት ዕድሜ ነው ያላቸው፡፡ ይህ ዕድሜ ሲጠናቀቅ ንብረቶቹ ሊታደሱ ይገባል፡፡ ከዚህም በላይ የመሠረተልማት መዋዕለንዋዮች የተለያየ መጠን የጥገና ወጭዎችን ያስከትላሉ፡፡ በመጨረሻም ከተሞች ውዝፍ የጥገና ፍላጎቶችን ያስተናግዳሉ፡፡ አንድን ንብረት ወደትክክለኛው የህልቀት ምጣኔ ለመመለስ ከተሞች በጥገና ላይ ብዙ መዋዕለንዋይ ማፍሰስ አለባቸው፡፡ የአገልግሎት ዘመን ወጭ ስሌትን ቀጥሎ ተመልከት፡፡



ስዕል 14፡- የንብረት ሕልቀት፣ የጥገና እጥረትና ቀሪ ዋጋ

ለምሣሌ:- የመሠረተልማት ዋጋዎችን ማስላት - የዕድሜ ልክ የመሠረተልማት አስተዳደር የአዲግራትን ከተማ ማዕከላዊ ክፍሏን ከመሥፋፊያ አካባቢው ጋር ለማገናኘት ትፈልጋለች፡፡ በግምት የ20 ዓመት የአገ/ዘመን ያለው አዲስ የአስፓልት መንገድ ለመሥራት 1 ሚሊዮን የኢ.ት/ብር ይጠይቃል፡፡ ከዚያም በኋላ ደግሞ መንገዱ ዕድሳት ይጠይቃል፡፡ መንገዱ በአገልግሎት ዘመኑ ሁሉ 5% ማለትም 50,000 የኢ.ት/ብር ዋጋውን እያጣ ነው የሚሄደው፡፡ ይህም የንብረት ሕልቀት ተብሎ ይጠራል፡፡

እስኪ በዝናብ ወቅት የላይኛው የመንገዱ ሽፋን ተጐዳ ብለን እናስብ፡፡ ከተማው በዓመት 2,000 የኢ.ት/ብር በመመደብ ለጥገናው ኃላፊነት አለበት፡፡ ጥገና ባይከናወን ደግሞ የአስፓልቱ የላይኛው ሺፋን በበለጠ ይጐዳል፡፡ ያለጥገና በሚፈጠረው የተፋጠነ ሕልቀትና ጥገና እየተካሄደለት በሚመጣው ጤናማ ሕልቀት መካከል ያለው ልዩነት የጥገና ኪሣራ ተብሎ ይጠራል፡፡ መደበኛ ጥገና ከተፋጠነ የሕልቀት ዋጋ በእጅጉ ያነሰ ዋጋ እንደሚያስከፍል መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡

እንደተጠቀሰው የኛ አስፓልት መንገድ የ20 ዓመት ግምታዊ የአገልግሎት ዘመን አለው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኰብልስቶን መንገዶች ከ40 ዓመት በላይ የአገልግሎት ዘመን አላቸው በዚያም ላይ አነስተኛ የጥገና ወጭን ይጠይቃሉ፡፡ በሌላ አገላለፅ ኮብልስቶን አነስተኛ የግንባታ ወጭን መጠየቅ ብቻ አይደለም የሕልቀት ምጣኔውም ቢሆን ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሠረተልማት ዘርፍ የሚወጣው ከፍተኛ የጥገናና ግንባታ ዋጋ መፍትሔ ለመሥጠትና የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድን ወጭ ቆጣቢና ዘላቂነት ያለው በማድረግ የሕዝቡን ፍላጎት መመለስን አስፈላጊ አድርጎታል፡፡

ለምሣሌ የጥገና በጀት እንዴት እንደሚዘጋጅ እንመልከት

ከተማዋ በቅርቡ ማዕከላዊ ክፍሏን ከቀለበት መንገዱ ጋር ለማገናኘት የ1 ኪ.ሜ ኮንክሪት የተፋሰስ ቦይን ጨምሮ አዲስ 1 ኪ.ሜ አስፓልት መንገድ ገንብታለች፡፡ በተጨማሪም ከተማዋ የኰብልስቶን ፕሮጀክት ጀምራ 500 ሜትር ያህል አንጥፋለች፡፡ በተጨማሪም ከተማዋ ከ4ኪ.ሜ በላይ የጠጠር መንገድ እና ከዝናም ወቅት በኋላ በየዓመቱ ጥገና የሚጠይቅ 10 ኪ.ሜ የአፈር መንገድ አላት፡፡ በመጨረሻም በከተማዋ ዙሪያ የዝናም ውሀን ለማፋሰስ የሚረዳ በድንጋይ የተገነባ 1ኪ.ሜ ተፋሰስ አለ፡፡ እንግዲህ የጥገና በጀትን ለማዘጋጀት እያንዳንዱ መሠረተልማት በመሰረተልማት አውታር ቆጠራ የነጠላ ዋጋ መቶኛ ከሚሆን የነጠላ ጥገና ዋጋ ተነፃፅሮ ይዘረዘራል፡፡ በመጨረሻም የጥቃቅን ወጭዎች ይጠቃለላሉ፡፡ በዚህም ምሣሌ አጠቃላይ ዓመታዊ የጥገና ወጭ ከ1ሚ የኢ.ት/ብር በላይ ይሆናል፡፡ የዚህ በጀት ግማሽ ከዝናብ ወቅት በኋላ ለሚደርስ የተጐዱ የአውራ መንገዶች ጥገና ያስፈልጋል፡፡

ዕቃ፣ አሐድና መጠን	የመሠረተ ልማት ዋጋ	ሥራ ላይ የዋለው ዋጋ በመቶኛ	የጥገና ወጭ/ በመሠረተ ልማት (የኢ.ት/ብር)
አስፓልት መንገድ (1 ኪ.ሜ)	4,500,000	5%	225,000
ኮብልስቶን መንገድ (0.5 ሜ)	1,400,000	3%	42,000
የጠጠር መንገድ (4 ኪ.ሜ)	10,000,000	3%	300,000
የአፈር መንገድ (10 ኪ.ሜ)	5,000,000	10%	500,000
ኮንክሪት የቱቦ ሥራ	400,000	3%	12,000
የግንብ ማፋሰሻ (1,000ሜ)	300,000	3%	9,000
ጠቅላላ ጥገና			1,088,000

ሠንጠረዥ 2፡- የጥገና በጀትን በመሠረተልማት አውታር ቆጠራ asset (inventory) መሠረት ማዘጋጀት

ደረጃ 2 - የጥገና በጀትን አዘጋጅ

የመዋዕለንዋይ አማራጮችን ለማወዳደር የቆይታ ዘመናቸውን፣ የማለቂያና የጥገና ወጫቸውን ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ ቀጥሎ ያለው ምሣሌ የአማራጮችን ግንባታ ዋጋ ማወዳደር የመዋዕለንዋዩን የፋይናንስ አዋጭነት (ደህንነት) እንደማይገልፅ ያሣያል፡፡ ይልቁንስ የመሠረተልማት አውታሮችን የአገልግሎት ዘመን ወጭዎች ማወዳደር የተሻለ ነው፡፡

የጥገና ወጭዎች የከተማዋ መደበኛ ወጭዎች አካል ናቸው፡፡ የጥገና ሥራዎች የመሠረተልማቱን ዕድሜ እስካራዘሙ ድረስ ምድባቸው ከካፒታል መዋዕለንዋይ ነው፡፡ ለምሳሌ የአረጀ አስፓልት መንገድ ዕድሳት ሥራ፡፡

በለውጥ ከተሞች የጥገና በጀት የመሠረተልማት ኪሣራና የጥገና ፍላጐቶችን ከሚያስረዳው የመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ ይመነጫል፡፡ የመሠረተልማት አውታር ቆጠራ የማይደረግባቸው ከተሞች ከ5 - 10 የሚደርስ የካፒታል በጀታቸውን ለጥገና መመደብ አለባቸው፡፡ ሆኖም ከተማዋ መሠረተልማትን በዝርዝር የሚያሳይ የመሠረተልማት አውታር ቆጠራ ካላት ይህ ዝርዝር ለእያንዳንዱ መሰረተልማት የጥገና ወጭ አመዳደብ ሊያገለግል ይችላል፡፡ የአመዳደብ መጠኑ የመሠረተልማቱ የግንባታ ዋጋ መቶኛ መሆን አለበት፡፡ ሠንጠረዥ 3 የከተማ የጥገና በጀት እንዴት እንደሚዘጋጅ ያሣያል፡፡

ርዝመት ኪ.ሜ፣ ስፋት 10 ሜትር	አስፓልት	ኮብልስቶን	ጠጠር
1. የግንባታ ዋጋ የኢ.ትዮ.ብር	4,500,000	2,800,000	2,500,000
2. የተገመተ የአገልግሎት ዘመን	15 ዓመታት	40 ዓመታት	5 ዓመታት
3. አመታዊ የመሠተ ልማት ማለቂያ	300,000	70,000	500,000
4. አመታዊ ጥገና	225,000	84,000	75,000
የአገልግሎት ዘመን ወጭ (3 + 4 የኢ.ት.ብር)	525,000	154,000	575,000

ሠንጠረዥ 3፡-የተለያዩ የመንገድ ዓይነቶች የአገልግሎት ዘመን ምሣሌ

ደረጃ 3 - አጠቃላይ የአዋጭነት ቅኝት

የእያንዳንዱን ፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት አካሂድ፡- በጥናቱ እያንዳንዱን የተጠና ፕሮጀክት ከተለያዩ መነሻዎች ማለትም ከውጤት፣ ከቴክኒክና ከፋይናንስ አዋጭነት አንፃር ፈትሽ፡፡ ከዚህ የሚገኘውን መረጃ በመጨረሻው የ'ካመፅ'ጥራዝ ዕዝሎች አካትት፡፡

የቴክኒክና ፋይናንስ አዋጭነት ጥናት የቴክኒክ ችግሮች እንደየመሬት ካሣ ክፍያና የቦታ ዝግጅት (ጠረጋ) ያሉት የሚከናወኑበትን አግባብ ለመወሰን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ቀላል የወጭና ትርፍ ትንተና፣ አማራጭ የሥርጭት ዘዴ ጥናትና የመዋዕለንዋዩን ምላሽ ማስሊያ ስልቶችን በመጠቀም የፕሮጀክቱን ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ለመዳሰስ ይረዳል፡፡

የውጤት ዳሰሳ የፕሮጀክቱን የታቀደ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ አንደምታዎችና ለከተማ አጠቃላይ ዓላማዎች ያላቸውን አስተዋፅኦ ይፈትሻል፡፡ ለሁለቱም ዳሰሳዎች የመጀመሪያው ደረጃ የፕሮጀክቱን መሠረታዊ መረጃ ማጠቃለል ነው፡፡ የሚከተለውን መረጃም አካትት፡-

- የፕሮጀክት መግለጫ፡- መረጃን በቦታ ምልከታ (ቀበሌ)፣ ስፋትና በቁሳዊ ሁኔታ (ስፋት፣ርዝመት፣ የድልድይ ዓይነት) እና ሌሎች ጉዳዮች (የጐን መንገዶች) ለይተህ አካትት፡፡ በመልሶ ማሻሻልና ዕድሳት ጊዜ የመሠረተልማቱን ሁኔታ ግለፅ፡፡ በተጨማሪም የሴክተር ዕቅዶችን፣ ዝርዝር የፕሮጀክት ዲዛይኖችን፣ ዝርዝር የዋጋ መግለጫና ግዢ ወይም የገንዘብ ፍሰት የድርጊት መርሀግብሮችን አመላክት፡፡
- የፕሮጀክቱ ምጣኔ ሀብታዊ ጥናትና ገንዘብ፡- የተገመቱ የመዋዕለንዋይና መደበኛ የሥራ ማስፈፀሚያና የጥገና ወጭዎችን፣ የአገልግሎት ዘመን፣ዓመታዊ የአላቂ ወጭዎችን፣የተመረጠውን የአቅርቦት ዘዴ (ምሣሌ የሀገር ውስጥ ጨረታ ግገር) እና አሉ የሚባሉ አማራጮችን ጥቅምና ጉዳት ሁሉ ታሳቢ አድርግ፡፡ በተጨማሪም የእያንዳንዱን ፕሮጀክት የፋይናንስ ምንጭ ወይም አማራጭ ምንጭና ተያያዥ የወጭ ቅነሳ ወይም ወጭን መልሶ የመሸፈን ስልቶችን (ምሣሌ የመሠረተልማት ክፍያዎች) አካትት፡፡
- የፕሮጀክቱ አስፈላጊነትና ውጤት፡- ፕሮጀክቱ ለከተማዋ ስትራቴጅካዊ ዓላማዎች ያለውን አስተዋጽኦ ካለፉ ሌሎች ተግባራት፣ ከታሪክና አመሠራረት ጋር ያላቸውን ትሥሥር ግለፅ፡፡ በተጨማሪም በትግበራ ጊዜ እና ከመነሻ እስከ መድረሻ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎችን፣ ፕሮጀክቱ ለነዋሪዎች የሚሰጠውን ምላሽ እና ማህበራዊና አካባቢያዊ ውጤቶች አጠቃልል፡፡ ይህን ሥራ ለማመቻቸት ከኮብልስቶን የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት (ሲዲ ዕዝል 4.3) ጋር ደረጃውን ጠብቆ የተቀረፀ የትንተና ሽት ተዘጋጅቷል፡፡ የዚህ ፈጣን ትንተና ውጤቶች ለሁሉም ኢጋር አካላት በሕዝብ ስሚ (ጉባኤ) ጊዜ ተደራሽ ሊሆኑ ይገባል፡፡

የዋና ጥቅም ትንተና አንድ ፕሮጀክት ከማህበራዊ ደህንነት አንፃር ሲመዘን ያለውን ተፈላጊነት የመወሰኛ መንገድ ነው፡፡ ይህም ቴክኒካዊ የምህንድስና ትንተናን፣ የፋይናንስ ትንተናንና ሁሉንም ገቢና ወጭዎች እንዲሁም አንፃራዊ የገበያ ዋጋቸውን ለመለየት የሚያገለግል ኢኮኖሚያዊ ትንተናን ያካትታል፡፡ ይህም መረጃ ከኦፕሬተሩ ዕይታ አንፃር ሊታዩ የሚገባቸውን ጉድለቶች ለተከታታይ እርምቶች ያመቻቻል፡፡ (የሰነድ ሲዲውን በተጨማሪ ተመልከት)፡፡

መዋዕለንዋዮች የሚያስገኙት መልስ (ጥቅም) የልማት፣ የማስፈፀሚያና የጥገና ወጭዎን የሚያካትት የፕሮጀክቱ የፋይናንስ ውጤት ስሌት ነው፡፡ በአጠቃላይ ከተሞች በትርፎች ላይ ብቻ ሳያነጣጥሩ ለዜጐች ቅድሚያ ለመስጠት ምርቶችንና አገልግሎቶችን ያቀርባሉ፡፡ ስለዚህ የመንግስት ሴክተሩ ለምርቱ ወይም አገልግሎቱ የፋይናንስ ምላሽን ያገኛል፡፡ ከዚህም በላይ ከፌደራል፣ ከበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ከባቢያዊ የመንግስት ምንጮች የገንዘብ ፍሰት ከሚቀርበው አገልግሎት ወይም ምርት ጋር የተገናኘ ነው፡ በዚህ ጊዜ ምርቱ ወይም አገልግሎቱ ቢጠፋ ኪሣራ ባጋጠመ ጊዜ ያንን ምርት ወይም አገልግሎት በማቅረብ የተለየ ገቢ ሊመነጭ አይችልም፡፡

የመሠረተልማት ክፍያዎች ('መልክ') ከአዲሱ እድገት የሚመነጨው የመሬት ዋጋ ማደግ ክፍያዎች ናቸው፡፡ 'የመሠረተልማት ክፍያዎች' ለመሠረተልማትና ሌሎች የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ለመክፈል ይረዳሉ፡፡ እንደንብረት ግብር ሳይሆን 'የመሠረተልማት ክፍያዎች' አገልግሎት ለመስጠት የወጡ የካፒታል ወጭዎች በተጠቃሚዎች መሸፈናቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

ደረጃ 4 - ማጣራት፣ ከባቢያዊ ዳሰሳና የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕቀፍ

ሁሉም የ' ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ 'ፕሮጀክቶች ማህበራዊና ከባቢያዊ ማጣሪያን ማከናወን አለባቸው፡፡ ማጣራት ማለት ፕሮጀክቱ ሙሉ በሙሉ የመልሶ ማቋቋም ድርጊት መርህ ግብር (መማድመ) ወይም ከባቢያዊ የውጤት ዳሰሳ (ከውዳ) የሚፈልግ ስለመሆኑ አስፈላጊ የዳሰሳ ደረጃን የመወሰን ሂደት ነው፡፡

የተጣሩ ፕሮጀክቶች በ3 ፈርጅ ይመደባሉ፡፡ የድርጊት መርህ 1 (መማዕ እና/ወይም ከውዳ)፣ የድርጊት መርህ 2 (ምህፃረ መማዕ ወይም/እና ከፊል ከውዳ እንዳስፈላጊነቱ) ወይም የድርጊት መርህ 3 (ቀጣይ ዳሰሳ አያስፈልግም፡፡)
ሂደቱ በከተማ አስተዳደሩ ዲዛይን ግንባታ (መሠረተልማት) ጽ/ቤት አነሣሽነት ይቀረፅና ጽ/ቤቱ ሥራውን በሌላ እንዲሠራ ይሰጣል ወይም የማጣሪያ ሪፖርቱንና ተያያዥ የዳሰሳ ጥናቶችን ለክልሉ ከተማ ልማት ቢሮና የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ ለማፀደቅ ያቀርባል፡፡

የማጠሪያ ሪፖርቱ የታቀዱ ተግባራትንና የሚያስገኙትን ውጤት፣ የተግባር አካባቢውን ባህሪያት፣ ስፋት ወይም መጠን፣ የሕዝብ ፍላጐት ደረጃ፣ ተቋማዊ ፍላጐቶችና የቁጥጥር አስፈላጊነትን በዝርዝር ይገልፃል (ለዝርዝሩ ሲዲ ዕዝል 6 ተመልከት)፡፡

የመልሶ ማቋቋም እንድምታዎች

አንዳንድ ፕሮጀክቶች ባይበልጥም የከተማ ደረጃ ማሻሻልና መልሶ ማደስ ፕሮጀክቶች የነዋሪዎችን መልሶ ማቋቋም ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ ከ200 በላይ ነዋሪዎች በዚህ የሚፈናቀሉ ከሆነ ከተማዋ የመልሶ ማቋቋም የድርጊት ዕቅድ የመልሶ ማቋቋም ፖሊሲ ማዕቀፎችን ተከትሎ ማቅረብ አለባት፡፡ (መማማ፣ ሲዲ ዕዝሎች 6.2) አጭር የመልሶ ማቋቋም የድርጊት መርህግብር ከ25 - 199 ለሚደርሱ ተፈናቃይ ነዋሪዎች ያስፈልጋል፡፡ ቁጥሩ አነስተኛ ከሆነ ዕቅዱ አያስፈልግም፡፡

ይህ ማዕቀፍ የሚያገለግለው የታቀደው የፕሮጀክት መዋዕለንዋይ ወደህዝባዊ ሁከት ወይም ጊዜያዊ መፈናቀል ያመራ እንደሆነ ነው፡፡ በቋሚ መኖሪያዎችና የንግድ ተቋማት ወይም ለግጦሽና ለእርሻ የዋለ መሬትን የመውረስ እንድምታዎች (የሚያስከትሉት ውጤት) በትኩረት መታየት አለባቸው፡፡ የማህበረሰቡ መፈናቀል ታላቅ ጫናን ያስከትላል፡፡ በጣም ተጐጅ ክፍሎች ሴቶች፣ ሕፃናት፣ የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን በተለይ በኢመደበኛ ማህበራዊ ትሥሥር በጥገኝነት ይኖራሉ፡፡ በተለይ እነዚህ ክፍሎች በመልሶ ማቋቋም ዕቅዱ ዝግጅት ጊዜ ሐሳባቸው ሊደመጥ ይገባል፡፡ በመጨረሻም ግዙፍ የመልሶ ማቋቋም ሂደቶች ሁልጊዜ ካልተፈለገ ዕርግዝና፣ የአባለዘር በሽታ ሥርጭትና የሴተኛ አዳሪነት መብዛት ጋር ቁርኝት አላቸው፡፡ ስለዚህ የመልሶ ማቋቋሙ ዋና ዓላማዎች፡-

1. ፈቃደኛ ያልሆነ መልሶ ማቋቋም የመሬት ግኝት አሉ የሚባሉ አማራጮችን ሁሉ በማየት መወገድ ወይም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ መቀነስ አለበት፡፡

2. ማንኛውንም ተፈናቃይ በተለይ በመሠረተ ልማት መዋዕለንዋዩ የተፈናቀሉ ተጐጅ ወገኖች ሥራን እንዲያገኙ በማድረግና በሌላ ዕርዳታ ደግፍ ፣

3. ያለፈቃደኝነት የመልሶ ማቋቋምና የመሬት ግኝት የግድ በሆነ ጊዜ የመልሶ ማቋቋምና የካሣ ተግባራት ይዘጋጁና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በቂ የመዋዕለንዋይ ሀብቶችን በመስጠት ይተገበራሉ፡-

- አዋጅ ቁ.455/------ የመሬት ይዞታዎችን ለሕዝብ አገልግሎትና ለካሣ ክፍያ ሲባል ስለመውረስ የወጣ አዋጅ ፣
- የሚንስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁ. 135/----- ለሕዝብ አገልግሎት በተወረሱ ይዞታዎች ላይ ስላሉ ንብረቶች ስለሚፈፀም የካሣ ክፍያ የወጣ ደንብ ፣

ከባቢያዊ አንደምታዎች

ጥቂት ፕሮጀክቶች በዜጐች ላይ ጉልህና አሉታዊ ማህበራዊና ከባቢያዊ ጉዳቶች ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ፕሮጀክቶች በውጭ አማካሪ ወሰናቸውንና ሙሉ የከባቢያዊ እንድምታቸውን ዳሰሳ ይሻሉ፡፡ የድርጊት መርህ 1ፕሮጀክቶች ታላቅ ግድቦችን፣ የውሃ ማከማቻዎችን (>100 ሄክታር)፣ የከርሠ ምድር ውሃ ልማት (>4000 ሜ3/ቀን) እና ግዙፍ የመስኖ ተፋሰስና የጐርፍ ፍሰት ቅነሣ ሥራዎችና ለውሃማ አካላት ቅርብ የሆኑ የተፋሰስ ፕላኖችን ያካትታል፡፡ ሌሎች ፕሮጀክቶች ለከተማ ቆሻሻ አወጋገድ የመሬት ሙሌት፣ የቆሻሻ አወጋገድ ኢንስታሌሺን (የኢንዱስትሪ ቆሻሻን ለማቃጠል፣ ኬሚካል ማስወገጃ ፕላንት፣ ጐጅ ቆሻሻን የመቅበር)፣ ግዙፍ የሆስፒታልና የትምህርት አገልግሎት፣ የቤት ልማት (>50 ሄክታር)፣ አዲስ ከተሞችና የመኖሪያ አካባቢዎች፣ አዲስ የኢንዱስትሪ ቦታዎች፣ የገበያ ማዕከላት፣ የከተማ ግልፅ ገበያዎች፣ የአውቶቡስና ባቡር ጣቢያዎች፣ ዋና-ዋና የከተማ መንገዶች፣ የባቡር መሠረተልማትና መንገዶች፣ ግዙፍ የኃይል ተሸካሚ መስመሮች፣ ታላላቅ ባዮማስኢነርጂ ተጠቃሚ ፕላንቶች፣ የተፈጥሮ ኃይል ጣቢያዎችና የማቀጣጠያ ኢንስታሌሺኖች (የሙቀት ውጤታቸው >100 ሜጋዎት) እና የተቀናጁ የኃይል ጣቢያዎች ያሉት ናቸው፡፡

አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች ከፊል የአካባቢ ተፅዕኖ ዳሰሳ ብቻ ይፈልጋሉ፡፡ ቢሆንም ግን አሉታዊ የአካባቢና ማህበራዊ ጫናን ያስከትላሉ፡፡ ስለዚህ በግልባጩ ስለሚያስከትሉት ጠቃሚ ውጤት መገምገም አለባቸው፡፡ ይህም በፕሮጀክት አካባቢዎች የመስክ ጉብኝት፣ ከተጐጅ ነዋሪዎች ጋር በሚደረግ አጭር ምክክርና በአካባቢና ማህበራዊ አስተዳደር ማዕቀፍ የአካባቢ ኮንትራት አንቀጾች (ሲዲ ዕዝሎች 6) አማካኝነት ይከናወናል፡፡ የድርጊት መርህ 2 ፕሮጀክቶች የከተማ ጤናና ውሃ አቅርቦትን፣ አነስተኛ ደረጃ የመሬት ተፋሰስን የፍሳሽ ስርዓትና መልሶ የመጠቀም ስልቶችን፣ የመኖሪያ ቤትና የንግድ ፕሮጀክቶችን፣ መካነ መቃብርና የሃይማኖት ተቋማትን፣ የዋና ዋና መንገዶችና ኤርፖርቶችን (የመሸከርከሪያ ርዝመት <2100 ሜ) የደረጃ ማሻሻልና ጥገና ሥራዎችን፣ የተፈጥሮ ኃይል ጣቢያዎችና ሌሎች የማቀጣጠያ ኢንስታሌሽኖች (የሙቀት ውጤት <300 ሜጋዋት) እና የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮችን ያጠቃልላሉ፡፡

አድማሳዊ ዕይታ የፕሮጀክቱን የዳሰሳ ፍላጐቶች ለመለየት ይረዳል፡፡ የአካባቢ ተፅዕኖ ዳሰሳን ለማከናወን በልምድ የተካነ አማካሪን ለማግኘትና ለመምራት የሚያስችል ዝክረ ተግባር ማዘጋጀትን ያካትታል፡፡

ክፍል 5

የውሳኔ አሠጣጥ ሂደት

የአጋር አካላት ውይይት ለመዋዕለንዋይ ስኬታማነት ጠቃሚ ነው፡፡ አሳታፊ የበጀት ዕቅድና የሕዝብ ምክክር የሂደቱ አስገዳጅ ክፍል ናቸው፡፡ ግቡም መዋዕለንዋዮች ከተጠቃሚዎች ፍላጎትና ምኞት ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ክፍል የካፒታል መዋዕለንዋዮች በሕዝብ ተሣትፎ እንዴት እንደሚወሰኑ ፍንጭ ይሠጣል፡፡ የውሣኔ አሠጣጡን ሂደት ማቀናጀት በአመዛኙ የከንቲባው ኃላፊነት ነው፡፡

አጋር አካላት በውሳኔ አሠጣጥ:-

በአንድ ከተማ የልማት ፍላጐቶች ዙሪያ በርካታ አመለካከቶች አሉ - የሕግ፣ የቴክኒክና የተጠቃሚዎች አመለካከቶች:: በነዚህ የተለያዩ ነጥቦች ዙሪያ መረጃ በከተማዋ የማስታወቂያ ጽ/ቤት ይመራል፣ ይገለፃል:: ጽ/ቤቱ የሚከተሉትን የፍላጐት መረጃ ይሰበስባል:-

- **የከተማ ም/ቤት:-** ም/ቤቱ ከፍተኛው ተመራጭ የከተማዋ አካል ነው:: የከተማውን ካቢኔ ይቆጣጠራል:: በበጀት ላይም የመጨረሻ ውሳኔ ያሣርፋል:: ከንቲባው የመጨረሻውን የ' ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ' ፕሮፓዛል ለማፀደቅ ለምክር ቤቱ ያቀርባል::

- **ነዋሪዎች:-** ነዋሪዎች የልማት ወኪሎች ናቸው:: እንደልማት ውክልና ከፍተኛ የፍላጐት አካላት ናቸው:: ቀዳሚ ፍላጐታቸውንም ወይ በፍላጐት ቡድኖች (የሃይማኖት ተቋማት፣ ዕድሮች፣ ወጣትና የሙያ ማህበራት) አልያም በቀጥታ አሣታፊ የበጀት ዕቅድ አማካኝነት ይገልፃሉ:: መያድ፣ ዩኒቨርሲቲዎችና የግል ዘርፉ ሌሎቹ ጠቃሚ አጋሮች ናቸው::

- **ከንቲባው:-** አሣታፊ ሂደትን ለማቀናጀት ኃላፊነት ይኖረዋል:: ነገር ግን የፖለቲካ አጀንዳ ይኖረዋል:: ለምሳሌ የሥራ ፈጠራ:: ስለዚህም ሁልጊዜ ለጉልበት ተኮርና ተጨባጭ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ይሰጣል:: ነገር ግን ከንቲባው በውሳኔ አሠጣጥ ሂደት ውስጥ ዘልቆ መግባት የለበትም:: የሱ ሚና በካፒታል መዋዕለንዋይ ውሳኔዎች ላይ ስምምነትን እንዲመጣ ማስቻል ነው::

- **የማዘጋጃ ቤት መሠረተ ልማት ባለሙያዎች:** - የነዚህ ባለሙያዎች ሚና የንብረት አስተዳደር ዕቅድን ማዘጋጀት ነው:: መሠረተ ልማት በምን ሁኔታ ላይ እንደሚፈለግ የተሻለ ዕውቀት አላቸው:: ይሁን እንጂ ብዙ ከተሞች በደንብ የተዘጋጀ የመሠረተልማት አስተዳደር ዕቅድ የላቸውም እናም በስፓሻል ወይም የዕድገት ፕላኖች ላይ ይመረኰዛሉ (ክፍል 2 ተመልከት)

- **ካቢኔ:-** የካቢኔ አባላት ሁልጊዜ የራሳቸው አጀንዳ አላቸው:: አንዳንዴ እንዲያውም በሁኔታ ላይ የተመሠረቱ ባለሃብቶች ማለትም ሴክተር ተኮር ፕሮጀክቶች ለምሣሌ ለትምህርት ዘርፉ ብቻ የሚተገበሩ ት/ቤቶች ሊኖሩት ይችላሉ::



ስዕል 15:- የፕሮጀክት ውሳኔ አሠጣጥ ዕይታዎች

በፊት



በኋላ

ስዕል 16:-ዜጐች ፍላጐቶቻቸውን እንዲገልፁ ሥልጣን ውስጠት የከተማ አስተዳደሩ ቁልፍ ኃላፊነት ነው::



ስዕል 17፡- የተሣትፎ መሰላል ካለመሣተፍ ወደተሟላ ሥልጣን

ቀጥተኛው የዲሞክራሲ ስልት ከውክልና ዲሞክራሲ ይለያል፡፡ በኋላኛው ሕዝብ ወኪሎቻቸውን ከመሪዎች (የከተማ ም/ቤት አካላት) ጋር እንዲወስኑ ሥልጣን በመስጠት በድምፅ ይመርጣሉ፡፡ በቀጥታ ዲሞክራሲ ደግሞ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣኑ የሕዝብ ነው፡፡ የሕዝቡ ፍላጐቶች በአሣታፊ ሂደት ይደመጣሉ፡፡

ልማዳዊው ስልት

በሕዝብ ሀብት አመዳደብ የውሳኔ አሠጣጥ ሂደት አጋር አካላትን የማሣተፊያ በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ በዓለም አካባቢ የሕዝብ ተሣትፎ ደረጃ የተሠጠው ሂደት (መሠላል) ሆኖ ይታያል (ስዕል 17 ተመልከት)

ዝቅተኛው ዕርከን የገንዘብ አመዳደብን በራሣቸው በሚወሰኑ አውቶክራቲክ መሪዎች የሚመሩ አገሮችን ይገልፃል፡፡ በከፍተኛው ዕርከን ደግሞ ዜጐች በበጀት ላይ ፍፁም የመወሰን ሥልጣን አላቸው፡፡

ውጤታማ የሕዝብ ተሣትፎ ማህበራዊ ውህደትን (አለማግለልን)፣ የግል ደህንነትን፣ የመናገርና የመሰብሰብ ነፃነትን ይጠይቃል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ዜጐችን ለማማከር ልማዳዊው ዘዴ ነው እየሠራ ያለው ይሁንና የተጐጂ ክፍሎች በሕዝባዊ መድረኮች የመሣተፍ አቅም መጠናከርን ይፈልጋል፡፡ የነዚህም ምክክሮች ቅርፅና ይዘት ስለከተማ ልማት ውይይቶችና ውሣኔዎች ከፍተኛና ንቁ የሕዝብ ተሣትፎን ለማመቻቸት መሻሻል አለባቸው፡፡

አዲሱ ስልት

የኢትዮጵያ ከተሞች በአሁኑ ጊዜ በመካከለኛው የተሣትፎ ዕርከን አካባቢ ይሠራሉ፡፡ ሆኖም ጠንካራ የፖለቲካ መመሪያ ወደላይኛው ዕርከን ለማደግና የውሳኔ አሠጣጥን በሕዝብ ንቅናቄ ለማስኬድ በሂደት ላይ ነው፡፡ እነዚህ ዓላማዎች በተለያዩ የሕግ መሠረቶች ተቀምጠዋል፡፡ (Sidebar 33 ተመልከት)፡፡

እነዚህን ዓላማዎች ለማሣካት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር በልማቱ የሕዝብ ባለቤትነትን ለማረጋገጥ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ዕትዕ) ሁለት ዓይነተኛ ዒላማዎችን ወስኗል፡-

1. የጠቅላላ ልማትና ፕሮጀክት ዋጋ 50% በዕውቀት፣ ጉልበት፣ ገንዘብና ማቴሪያል አስተዋፅኦ በሕዝብ ሊሸፈን ይገባል፡፡
2. 35 - 50% የሚደርሰው መዋጮ በሁሉም የልማት ፕሮግራሞች ሴቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ዕትዕ) የፌደራል መንግስት ልማቱን ለማሣደግ ሥራ ላይ ያልዋለውን የሴቶች ዕምቅ ሀብት ለመጠቀም አስፈላጊውን ዕውቅና ሠጥቷል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ የሕዝብ ስብሰባዎችንና የአጋር አካላት ምክክሮችን ለሚካፈሉ ሴቶችና እነሱ ቅድሚያ ለሚሰጧቸው የልማት አጀንዳዎች ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባዋል፡፡ ነገር ግን ፍላጐትና የሕግ ማዕቀፍ ቢኖሩም አሣታፊ ሂደት እንዴት እንደሚካሄድ ያለው ውስን ዕውቀትና ልምድ የሕዝብ ተሣትፎና በተፈለገው ደረጃ የሴቶች ድርሻ እንዳይጐለብት ይጐትተዋል፡፡

ይህንን እጥረት ለመመለስ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተጨማሪ አዲስ ስልት ዘርግቷል፡፡ ይህም በሕዝብ ንቅናቄና አሣታፊ የበጀት ዕቅድ ዝግጅት የውሳኔ አሠጣጥ ቀጥተኛ ዲሞክራሲያዊ ዘዴ (ስልት) ነው፡፡ ስልቱ ብራዚል በአሁኑ ስዓት የምትጠቀምበት ሞዴል ነው፡፡

ደረጃ 1 - ተሣትፎን ማቀድ

ስለተሣትፎ ስንናገር ብዙ ሰዎች ነዋሪዎችን እንደስብስብ ያስቧቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ የአጋር አካላት በአንድ በኩል እንደደሀ እና በሌላ በኩል እንደአለም አቀፍ የመዋዕለንዋይ ባለሀብት በእጅጉ ይለያያሉ፡፡ ሁሉም ድምፅ አላቸው፡፡ በእርግጥ ዋናው ትኩረት በጣም ተጐጅ ለሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ሊሆን ይገባል፡፡ ይልቁንም ለሴቶችና ሕፃናት ጠንካራው የአሣታፊ ሂደት ዕቅድ የሚከተሉትን ይይዛል፡-

በመጀመሪያ፡- ለየትኛው አሣታፊ ሂደት የትኛው የካፒታል በጀት ድርሻ መሠጠት እንዳለበት መወሰን፡፡ በዚህ ክፍል ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የሕዝብ ተሣትፎ ለማስኬድ ሁለት ዋና- ዋና ስልቶች አሉ፡- ልማዳዊ ምክክርና አሣታፊ የበጀት ዕቅድ ዝግጅት፡፡ ስዕል 18 (ገጽ 35) የሁለቱን የጊዜ መስመር ያብራራል፡፡ የስዕሉ የላይኛው ዕርከን ልማዳዊውን የምክክር ሂደት መስመር ያሣያል፡፡ ይህ ስልት ከ88% በታች ያለው በጀት ሥራ ላይ የሚውልበትን ይወስናል፡'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ የስዕሉ ዝቅተኛው እርከን የአሳታፊ የበጀት ዕቅድ የጊዜ መስመርን ያሣያል፡፡ ቢያንስ 20 የ"ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ " በነዋሪዎች አሣታፊ የበጀት ዕቅድ መወሰን አለበት (ይህ ድርሻ በዓመታት ውስጥ እያደገ ሊሄድ ይችላል)፡፡

ሁለተኛ፡- ልማዳዊውንና አዲሱን አሣታፊ ስልት በእያንዳንዱ ስልት የሚመደበውን የበጀት ድርሻ ጨምሮ በአንድ ጊዜ አቅድ፡፡ በክፍል 1 የተገለፀው የ" ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ "ሂደት ዑደት በየካቲት 15 ሁለቱም አሣታፊ ስልቶች መጀመር እንዳለባቸው ያስረዳል፡፡

ልማዳዊው ሂደት በዳሰሳ እና በከፊል የተደራጀ የአጋር አካላት ቃለምልልስ ይጀምራል፡፡ አሣታፊው የበጀት ዕቅድ ሂደት ጐን ለጐን እየተካሄደ ከቀበሌ ስብሰባዎች ጋር ይጀምርና ለፕሮጀክቶች የአፈፃፀም ቅደም ተከተል በአሣታፊ በጀት ዕቅድ ድምፅ በም/ቤት ይደማደማል፡፡ ሁለቱም ሂደቶች የሕዝብን ቀዳሚ የመዋዕለንዋይ ፍላጐቶች ለማወቅና ለከተማ ም/ቤቱ ከመተላለፉ በፊት "የካፒታል መዋዕለንዋይ"ን ለማቀናጀት ሚያዝያ 15 በሚካሄደው ዓይነተኛ የሕዝብ ስብሰባ (ስሚ) ላይ ይዋሀዳሉ፡፡

ሶስተኛ፡- ሁለቱንም ስልቶች ለተሣትፎ ለመጠቀም የሚረዱ ዶክመንቶችን አዘጋጅ፣ ግልፅ የዶክመንቶችን ቅጅም አስቀምጥ፡፡

ለልማዳዊው ዘዴ ሂደት የአጋር አካላትን ዝርዝር፣ ለምክክር የተጠሩባቸውን ደብዳቤዎች፣ የቃለምልልስ መጠይቆች የነዋሪዎች ፍላጐት መግለጫ ጥናትና የሕዝብ ስብሰባ ተሣታፊዎች የጥሪ ደብዳቤዎች አዘጋጅ፡፡

ለአሣታፊ የበጀት እቅድ ሂደት አጋር አካላትን ለቀበሌ ስብሰባ የሚጋብዙ ደብዳቤዎችና የድምፅ አሠጣጥ ክፍለ ጊዜዎች የመሳሰሉት ተጨማሪ ዶኪመንቶች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት፡-

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘላቂ ልማትንና የኑሮ ደረጃቸውን ለማሻሻል መብት አላቸው፡፡ እናም በሀገራዊ ልማት በተለይም ሕብረተሰቡ ላይ እንደምታ ባላቸው ፓሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ የማማከርና የመሣተፍ መብት አላቸው (አንቀጽ 43.1 - 43.4)፡፡ ሴቶችም በብሔራዊ የልማት ፓሊሲዎች አቀራረጽ፣ በፕሮጀክት ቀረፃና ትግበራ በተለይም ይህ ሴቶች ላይ አንድምታ ያለው ከሆነ ሙሉ የማማከር መብቶች አላቸው (አንቀጽ 35)፡፡

የከተማ ልማት ፓሊሲው የሚከተለውን ያስቀምጣል፡- "ሕዝቡ በልማት ጉዳዮችና በመልካም አስተዳደር ዙሪያ በወኪሎች (የምክር ቤት አባላት) ብቻ ሳይሆን በሚመለከቷቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ሁሉ በቀጥታ መሣተፍና ማማከር አለባቸው" በተመሣሣይ የም/ቤት አባላት የፕሮሲጀር ማኑዋል እንዲህ ይላል፡- " [----------] የም/ቤት አባላት በበጀት ዝግጅትና በውሳኔ አሠጣጥ ቀጥታ ተሣትፎን ለማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

በመጨረሻ የዕድገትና ትራንስፎርሜሺን ዕቅዱ እንዲህ ያትታል፡- "የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች ተግባራት ለመደገፍ የአካባቢ መልካም አስተደደርን ጨምሮ በዕቅድ ዝግጅት ወቅት የሕዝብ ተሣትፎን አረጋግጥ፡፡ ሕዝቡን በአካባቢ የመሠረልማት ግንባታ በማነቃነቅና በማሠማራት፣ ምቹ ሕጋዊና ተቋማዊ አሣታፊ ስልቶችን በመፍጠርና በሁሉም የመንግስት የየተዋረዱ መዋቅሮች ተግባራዊ በማድረግ ሕዝቡ የመንግስት ፓሊሲዎችን፣ ስትራቴጅዎችንና የልማት ዕቅዶችን ለመቅረጽና ለመገምገም እንዲሣተፍ ለማስቻል የሴቶችን ተሣትፎ በወረዳና ቀበሌ ደረጃ ለማሣደግ ገንቢ ርምጃዎችን ውሰድ፡፡

በፓርቶ አሌግሬ አሣታፊ የበጀት ዝግጅት፡ - በፓርቶ አሌግሬ (ብራዚል) ከ20 ዓመታት በላይ ዜጐች (ነዋሪዎች) የከተማዋን ወጭዎች በቀጥታ ይወስናሉ፡፡ አሣታፊ የበጀት ዝግጅት ተብሎ በሚታወቀው ሂደት ተራ ነዋሪዎች የከተማ አስተዳደሩን የዓመታዊ በጀት ክፍል ይወስናሉ፡፡ ዛሬ 160ሚ የአሜሪካ ዶላር ያህል መዋዕለንዋዮች ላይ ጫና ማሣደር በሚችል አቅም በግልፅ ክልላዊ ስብሰባዎች ከተመራጭ ወኪሎች ጋር ከ20000 በላይ የሚሆኑ ነዋሪዎች በንቃት ይሣተፋሉ፡፡ በአጠቃላይ አሣታፊ የበጀት ዝግጅት 3 መሠረታዊ ደረጃዎችን ያካትታል፡-

መጀመሪያ፡- ሕዝባዊ ስብሰባዎች የኅብረተሰብ አባላት ቀዳሚ የወጭ መስኮችን ይለያሉ፣ የበጀት ልዑካንንም (ወኪሎችን) ይመርጣሉ፡፡

ሁለተኛ፡- የበጀት ወኪሎች በባለሙያዎች ድጋፍ ልዩ የወጭ ጥናቶችን ያዘጋጃሉ፡፡

ሶስተኛ፡- የህብረተሰብ አባላት የሠፈር ቀዳሚ ፍላጐቶችን፣ የመሠረተልማት መዋዕለንዋዮችንና ማህበራዊ ፕሮጀክቶችን በድምፅ ይለያሉ፡፡ በፓርቶ አሌግሬ የከተማዋን የተለያዩ ክፍሎች በሚወክሉ 16 የሕዝብ ስብሰባዎች ዜጐች ለክልሉ የበጀት ፎረምና ለአሣታፊ በጀት ም/ቤቱ (አበም) ይመርጣሉ፡፡ ለበጀት ፎረሙ የሚመረጡ የበጀት ልዑካን ቁጥር ከድምጽ ካርዶች ቁጥር ጋር የተያያዘ ነው (ማለትም ወኪሎች ቁጥር ባደገ ቁጥር ሠፈሩ ሠፊ ውክልናን እያገኘ ይሄዳል)፡፡ ከእያንዳንዱ ስብሰባ ለአሣታፊ በጀት ም/ቤቱ (አበም) 2 የም/ቤት አባላት ብቻ ይመረጣሉ፡፡

የተሣትፎ ዝርዝሮችና በፕሮጀክቶች ቅደም ተከተል ላይ የተሠጡ ድምፆች አስቀድሞ መከናወን አለባቸው፡፡ የከተማ ልማትና ኮንስትክሽን ሚ/ር ለወደፊቱ አሣታፊ የበጀት ዕቅድ ዝግጅትን ለማገዝ የሚረዳ ማኑዋል በማዘጋጀት ላይ ነው፡፡

ደረጃ 2 - ልማዳዊው የምክክር ሂደት

ከ80% የሚያንሰው የካፒታል በጀት በልማዳዊው ምክክር መወሰን አለበት፡፡ ጠቅላላ ሕዝቡ ከመጠየቁ አስቀድሞ የሁሉም አጋር አካላት የልማት ፍላጐቶች መታወቅ አለባቸው፡፡ ስለዚህ አጋሮችን በቡድን - በቡድን በሚወክላቸው ግለሰቦች አደራጅ፡፡ ዋናዎቹ አጋሮች፡-

- **የማህበረሰብ ምሥርት ተቋማት** እንደ ሴቶችና ወጣቶች፣ ያረጁ የከተማዋ ክፍሎች ነዋሪዎች ማህበራት እና ዕድሮች ፣
- **የሙያ ተቋማት፣** የንግድ፣ የባለሱቆች ማህበራት፣ የንግድ ም/ቤት ፣
- **መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች** (መያድ)፣ በድጋፍ ሠጭነት ላይ የሚሠሩ ብሔራዊ ቡድኖችና ዓለም አቀፍ የዕርዳታ ተቋማት (GIZ/GTZ)
- **የሃይማኖት ተቋማት፣** ኦርቶዶክስ፣ ሙስሊምና ፕሮቴስታንት ፣
- **የከተማና ቀበሌ ም/ቤት አባላት፣**- የቀበሌ ተመራጮች መደበኛ የቀ/ም/ቤት በሌለበት ያገለግላሉ፣
- **የከፍተኛ ትምህርት ተቋምና ሆስፒታል ተወካዮች** የአጋር አካላት ፍላጐቶችና ቀዳሚ የልማት ጥያቄዎች በሚከተለው ሁኔታ ይወሰናሉ፡፡

በመጀመሪያ፡- መጠይቆችን ለአባወራዎችና አጋር ድርጅቶች አዘጋጅተህ አሠራጭ ለከተማ አስተዳደሮች ጥናትና ምርምር በመጠይቅ ማካሄድና ለክልል ባለሥልጣናት ሪፖርት ማድረግ የግድ እንዳልሆነ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

በእርግጥ ጥቅሞቹ በርካታ አስተያየቶችንና ልዩነትን ሊያስገኙ ይችላሉ፡፡ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ጉዳቶች የተዛባ የመጠይቆች ሥርጭትና በውጤት ግምገማ ጊዜ የግልፅነት መጓደል ናቸው፡፡ መጠይቆች ሲዲ ላይ ያለውን ቴምፕሌት በመጠቀም ሊዘጋጁ ይገባል (ሲዲ ዕዝል 7)፡፡

ሁለተኛ፡- የአጋር አካላት ጋር የቡድን ውይይት አካሂድ፡፡ በዚህም የተለያዩ የአጋር ቡድኖች የመዋዕለንዋይ ቅደም ተከተሎችን እንዲያወጡ ይጠየቃሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ ምክክር የመዋዕለንዋይ ፍላጐቶችን በሚመለከት ስምምነት ላይ ለመድረስ ይረዳል እናም እንደ ሴቶች፣ ወጣትና ድሀ ያሉ ተጐጅ ቡድኖችን ፍላጐት የመግለፅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለሂደቱ ስኬት የትኩረት ቡድንን በጥንቃቄ መምረጥ ጠቃሚ ነው፡፡ የትኩረት ቡድኖች ጉዳት ምንድነው "የተፈጥሮ መሪዎች" የመሪነት ቦታውን ሲወስዱ አፋራም የሆኑት ተሰሚነትን ያጣሉ፡፡ ዶኪመንቴሽን ሲዲ የቃለመጠይቁን ሂደት ለመምራት ይረዳል፡፡ የትኩረት ቡድን ውይይቶችን፣ ዶኪመንቴሽንና ሪፖርት ማቅረብ ግዴታዎች ናቸው፡፡

ሶስተኛ፡- ከሁሉም አጋር ቡድኖች ተወካዮች ጋር የሕዝብ ስሚን አካሂድ አስገዳጅ የሕዝብ ሰሚ የፕሮጀክት ቅደም ተከተልን ለማውጣት ሚያዝያ 15 አካባቢ ይካሄዳል፡፡ በዚህ ስብሰባ ጊዜ ነው ሁለቱ የበጀት ዓይነቶች የሚቀናጁት፡፡

ይህም በቀጣይ በስፋት ይታያል፡፡ በስብሰባው ጊዜ አስቀድሞ ከልዩ ልዩ አጋር ቡድኖችና ከተማ አስተዳደር ጋር በጋራ የተጠኑ የፕሮጀክት ቅደም ተከተሎችን አቅርብ፡፡ ቀጥሎም ታሳቢ ፕሮጀክቶችን በዝርዝር ግለፅ ከዚህም ጋር የፊስካልና ፋይናንስ መሥፈርቶችና የፋይናንስ ሀብቶችን እንዲሁም የሚገመቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ተንትን፤ ከዚያም ቀዳሚ ተግባራትንና ታሳቢ ፕሮጀክት ሐሳቦችን መሠንዘር አለባቸው፡፡ በመጨረሻም በምሥጢር ወይም በሕዝብ ድምጽ የፕሮጀክቶችን ቅደም ተከተል ተንትን ውጤቱንም በሕዝብ ፊት ይፋ አድርግ፣ ለሥርጭትም ዶኪመንቴሺን ሊኖር ይገባል፡፡

ስዕል 18፡- ተጓዳኝ የሕዝብ ተሣትፎ ሂደት

ስዕል 19፡- ቁልፍ ችግር የሴቶችን ፍላጎት ማንፀባረቅ

ደረጃ 3 - አሳታፊ የበጀት ዕቅድ ሂደት

በብራዚል አገልግሎት ላይ ያለው ሞዴል (ገጽ 34 እና 35 ተመልከት) ለኢትዮጵያ ተወስዷል፡፡ የኢትዮጵያ ሞዴሎች 5 ደረጃዎች አሉት፡-

አንደኛ፡- በቀበሌ ደረጃ ሕዝባዊ ስብሰባን አካሂድ፡፡ ይህም ከመድረክ መሪው ጋር በየካቲት አጋማሽ አካባቢ ሊሆን ይገባል፡፡ የቀበሌ ተመራጮች የሕዝብ ስብሰባ ጥሪን ከበቂ የየሠፈሩ ተወካዮች ጋር መጥራት አለባቸው፡፡ በስብሰባው ጊዜ የቀበሌ ባለሥልጣኑና የመድረክ መሪው ስለጽንሰሐሳቡና ስለአሣታፊ የበጀት ዕቅድ መግለፅና ያለውን የካፒታል በጀትም ማብራራት አለባቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ስብሰባው የሰፈር የልማት ፍላጐት ቅደም ተከተሎችን ይወያያል፡፡ ውይይቶቹ ተጨባጭ ፕሮጀክቶችን አልያም እንደሥራ ፈጠራ ያሉ የፖለቲካ ዓላማዎችን ሊያካትት ይችላል፡፡ የስብሰባው ሐሳቦች በድምጽ ብልጫ መንጠር አለባቸው፡፡ ታዲያ ስብሰባው የመጨረሻ መዋዕለንዋዮች ሁለት የበጀት ልዑካን መምረጥ አለበት፡፡

ሁለተኛ፡- የከተማ አስተዳደሩና የቀበሌ በጀት ልዑካን (በከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ የቴክኒክና የቴክኒክ ባለሙያዎች እየተደገፉ) በበጀት እጥረትና በሠፈር ደረጃ ቀዳሚ ምርጫዎች ላይ የፕሮጀክት ጥናቶችን ለማዘጋጀት በየሣምንቱ ይሰበሰባሉ፡፡ልዑካኑ በዚህ ማኑዋል ክፍል 4 ላይ በተገለፀው መሠረት በደንብ የተጠኑ ፕሮጀክቶችን መርምረው ያቀርባሉ፡፡

ሶስተኛ፡- የአሣታፊ በጀት ዝግጅት ም/ቤቱ በጥናቶቹ ላይ ድምፅ ይሠጣል፡፡ ይህ ም/ቤት ከእያንዳንዱ ቀበሌ 2 የበጀት ልዑካንን፣ የከተማ ም/ቤቱን ቋሚ ኰሚቴና የቀበሌ ም/ቤት አፈ ጉባዔን ያቀፈ ነው፡፡ የበጀት ልዑካን ከተጨባጭ ጥናቱ ጋር ለበጀት ዝግጅት ም/ቤቱ ያቀርባሉ፡፡ እያንዳንዱ ተወካይ የትኛው ፕሮጀክት ላይ መዋዕለንዋይ እንደሚያስፈልግ አንድ አንድ ድምፅ ይኖረዋል፡፡ ድምፅ አሠጣጡን ተከትሎ የመጨረሻው አሣታፊ የበጀት ዕቅድ በመዋዕለንዋይና ባለው ሀብት ላይ ተመሥርቶ ይጠቃለላል፡፡ የበጀት ም/ቤቱ ለሕዝብ ክፍት ነው፡፡

አራተኛ፡- አሣታፊና ልማዳዊ የምክክር በጀትን አቀናጅ፡፡ ከልማዳዊ የምክክር ሂደትና ከአሣታፊ የበጀት ዝግጅት ሂደት የሚመነጩ በጀቶችን ወደማጠቃለያ 'ካመዕ' በጀት አዋህድ፡፡
ይህም ሚያዝያ 15 አካባቢ በሕዝብ ስሚ ጊዜ ይከናወናል፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ የበጀት ም/ቤት ተወካዮች በቀዳሚ መዋዕለንዋዮች ላይ ድምፅ ሊሠጡ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ከዚህ በኋላ ከአሣታፊ የበጀት ሂደት የመነጨው በጀት ለውይይት አይቀርብም (ከላይ ተመልከት)

አምስተኛ፡- " የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ "ን አቀናጅተህ ለከተማ ም/ቤቱ አቅርብ

አሳታፊ በጀት በኢትዮጵያ



ስዕል 20፡- በኢትዮጵያ አሳታፊ የበጀት ዝግጅት ሂደት

ደረጃ 4፡- ሂደቱን መዘገብ

የከተማ አስተዳደሩ ማስታወቂያ ጽ/ቤት ሁለቱንም የአሣታፊ ሂደቶች ለክልሉ ከተማ ልማት ቢሮና በተቀናጀ መልኩ ደግሞ ለፌደራል ቢሮ ሪፖርት የማድረግና የዶኪመንቴሺን ኃላፊነት አለበት፡ ፡ሪፖርቶቹን ደረጃቸውን በጠበቁ ፎርማቶች አዘጋጁ (CD ዕዝል 7) እናም የሚከተሉትን ዶኪመንቶች አካላት፡-

ልማዳዊና የምክክር ሂደት፡-

- የነዋሪዎችን ስሜት ለመፈተሸ መጠይቆች፣ የናሙና አወሣሠድ መጠን፣ የተጠኑ ሰዎች ያታዊ ምጣኔ እና የጥናት ውጤቶች፣
- ከእያንዳንዱ አጋር የትኩረት ቡድን ጋር ቃለምልልስ (ውይይት) መጠይቆችና ሪፖርቶች፣

አሣታፊ የበጀት ዝግጅት ሂደት

- የጥሪ ደብዳቤ፣ የተሳትፎ ዝርዝር፣ ያታዊ ምጣኔ፣ የዕያንዳንዱ ቀበሌ ስብስብ ፎቶ (ፊልም)፣ የቀዳሚ ፍላጐቶችና የድምፅ ውጤቶች ዝርዝር ፣
- በበጀት ልዑካን የተዘጋጁ የፕሮጀክት ጥናቶቹ ከቀበሌ ቀዳሚ ፍላጐቶች ጋር ስለመጣጣማቸው ማረጋገጫ፣ የጥራት ማረጋገጫና የባለሙያዎች የድጋፍ መጠን ፣
- የጥሪ ደብዳቤ፣ የተሳትፎ ዝርዝር፣ ያታዊ ምጣኔ፣ የአሣታፊ በጀት ም/ቤቱ ጠ/ስብሰባ ፊልም ወይም ፎቶ እና የድምፅ ውጤቶች ፣

የሕዝብ ስሚና ለም/ቤቱ ስለማቅረብ

- የጥሪ ደብዳቤ፣ አቴንዳንስ ዝርዝር፣ ያታዊ ምጣኔ፣ የሕዝብ ስሚ ፎቶ ወይም ፊልምና የድምፅ ውጤቶች፣
- ከሁሉም ዕዝሎች ጋር የ"ካመዕ" የመጨረሻ ጥናት ኮፒ (የ'ULGDP' ከተሞች ከሆኑ የአፈፃፀም ስምምነቱና ተሣትፎው አብሮ ይያያዛል)

ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የካፒታል ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለመለየት የተደረገ የህዝብ ዉይይት ፣ አዳማ

ክፍል 6

የካፒታል መዋዕለንዋል ዕቅድን አቀናጅ

የለፉት ክፍሎች ያለውን የፋይናንስ ሀብት እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻልና የፍላጎት ቅደም ተከተልና አዋጭ የሆኑ ፕሮጀክቶችና ዝርዝር እንዴት እንደሚዘጋጅ ይገልፃሉ፡፡ ይህ ክፍል የታቀዱ መዋዕለንዋዮች ከ3 ዓመታት ተንከባላይ የ" ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ" ወደፊት ገቢዎች ጋር እንዴት ማጣጣም (ማዛመድ) እና ዕቅዱን ማቀናጀት እንደሚቻል ያሣያል፡፡

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ "ተንከባላይ" ዕቅድ ይባላል ምክንያቱም በእያንዳንዱ ዓመት ዕቅዱ ለ3 ቀጣይ ዓመታት ነው የሚዘጋጀው፡፡ ይህ ዘዴ አንዳንድ ፕሮጀክቶች ከአንድ ዓመት በላይ ረጅም ጊዜን እንደሚወስዱና ከተሞች በመጀመሪያው ዓመት ቅድሚያ የተሠጠውን ፕሮጀክት ለመፈፀም በቂ ሀብት እንደማይኖራቸው ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡

” የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ” ን ማን ያቀናጃል?

ካፒታል በጀትን ማቀናጀት በከተማ አስተዳደሩ ስለጉዳዩ በቂ ዕውቅና ያለው ባለሙያን ይፈልጋል፡፡ ባለፉት ክፍሎች እንደተገለፀው”የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ”ን በፋይናንስ ጽ/ቤት በማዘጋጃ ቤት ታግዞ ማዘጋጀት ያለበት የከንቲባ ጽ/ቤት ነው፡፡ በከንቲባ ጽ/ቤት የ’ULGDP’ መሠረተልማት አስተባባሪ ዕቅዱን የማቀናጀት ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ ስለሆነም በ’MS Excel እና ‘MS Word’ በሚገባ ሊቆጣጠረው ይገባል፡፡

አስተባባሪው በልምድ የዳበሩ ኢንጅነሮች ድጋፍ ያስፈልገዋል፡፡ ምክንያቱም አብዛኛው የከተማ መዋዕለንዋይ በፊስካል መሠረተልማት ላይ ስለሚውል ነው፡፡ ከዝርዝር የፕሮጀክቱ የቴክኒክ ዕውቀት በተጨማሪ የፕሮጀክቱ ኢንጅነር የመለኪያ አሐሃዶችን (ሜ2 ወይም ኪ.ሜ እና ተዛማጅ የነጠላ ዋጋዎችን) የመወሰን ኃላፊነት አለበት፡፡ የትግበራ ዓመቱና የእያንዳንዱ ፕሮጀክት የፋይናንስ ሀብቶችም መወሰን አለባቸው፡፡ የኋላኛው (የፋይናንስ ሀብት) ሁልጊዜ በመጀመሪያ ቅኝት በደንብ የማይታዩ አንድምታዎች (ውጤቶች) አሉት (በተዛማጅ ፈንድ ሁኔታዎች የጐን ዓምድን ተመልከት)፡፡ ስለሆነም የፋይናንስ ጽ/ቤት ባለሙያ በ”ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ” ዝግጅትና ቅንብር ጊዜ መደገፍ ይኖርበታል፡፡

ደረጃ 1 - የከተማዋ ገላጭ ቅኝት

የከተማዋ ዳሰሳ ግብ የ”ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ”ን ሰፋ ባለ ግንዛቤ (ማዕቀፍ) ለመደልደል ማገዝ ነው፡፡ የ’MS Word’ ቴምፕሌት የ”ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ” የመጀመሪያ ክፍል (ደረጃ 3 ተመልከት) ስለከተማዋ ስም፣ ሕዝብ፣ የዕድገት ምጣኔ፣ የዓየርፀባይ --- ወዘተ ያሉትን ጠቃሚ መሠረታዊ መረጃዎች ያቀርባል፡፡ ይህ መረጃ ሁልጊዜ ከከተማዋ ማስታወቂያ ጽ/ቤት ይገኛል፡፡ አብዛኛውም ከሕዝብ ቆጠራ ይገኛል (ሲዲ ዕዝል 2.5)፡፡ በተጨማሪም በዚህ ክፍል የተገለፁት የከተማዋ ግቦችና ዓላማዎች ናቸው፡፡ ይህ መረጃ በአመልካቾች መልክ ብቻ መቅረብ ይገባዋል፡፡ (ለምሣሌ የወጣት ሥራ አጥነት በ2015 ሊወሰን ይገባዋል)፡፡ ግቦችና ዓላማዎች አስቀድሞ ከከተማዋ የዕድገት ወይም የመዋቅራዊ ፕላን ሊቀዱ ይገባዋል፡፡

ቀጥሎ የአሣታፊ ሂደትና ‘የካፒታልመዋዕለንዋይ ዕቅድ’ ለግቡ የሚሠጣቸው ምላሾች፣ ዓላማዎችና የማህበረሰቡ ፍላጐቶች መገለፅ አለባቸው፡፡ ይህም ደግሞ የዜጐችን ቀዳሚ ፍላጐቶችና ከተማው ለነዚህ ፍላጐቶች የሚሠጠውን ምላሽ ጨምሮ አጭር ቅኝት ይሁን፡፡ ዝርዝር መግለጫዎችና ማስረጃዎች ለአሣታፊ ሂደቱ አፈፃፀም በ” ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ” ዕዝል መቅረብ አለባቸው፡፡ (ዶኪመንቴሺን ሲዲው የ”ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ”ምሳሌዎችን ለ’ ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ’ ዝግጅት እንደሞዴል ከሚያገለግሉ በርካታ ከተሞች ተሞክሮ ቀምሮ ያቀርባል)፡፡

በ’ULGDP’ አዲሱ የተዛማጅ ፈንድ ሁኔታዎች የዓለምባንክ ለለውጥ ከተሞች በጋራ ፈንድ ሥርዓት ገንዘብ ይሰጣል፡፡
ምሳሌ፡- የዓለምብንክ 100ሚ ኢትዮ/ብር በአጠቃላይ ሰጠ፡፡ የብድሩ ተዛማጅ ፈንድ በእያንዳንዱ ክልልና ተጓዳኝ ከተማ የሚሸፈን ተጨማሪ 25% በማዋጣት በጠቅላላ 150 ሚ. የኢት/ብር ይሆናል፡፡

በመቶኛ ሲገለፅ የዓለም ባንክ (IDA) 66.67% ሲሰጥ ክልሉና ከተማዋ 16.67% እያንዳንቸው ይሸፍናሉ፡፡ ስለሆነም ፕሮጀክቶቹ በዚሁ መሠረት ይሠላሉ፡፡ ሠነጥረዥ 5 “የፕሮጀክት ዝርዝር” በ’MS Excel’ ቴምፕሌት ይህንን ማንፀባረቅ አለባቸው፡፡ ሠንጠረዡ በቀጥታ ወዲያውኑ ተጓዳኝ መቶኛ ስሌቶችን ያሠላል፡፡



ስዕል 21፡- በ’ULGDP’ የተዛማጅ ፈንድ ሁኔታዎች

የተደጋጋሚ 'ካመዕ' ፕሮጀክቶች መዋዕለንዋይ ወጭዎች ግምቶች

የአስፓልት መንገድ፣ ድልድይ ብቻ፣ ስፋት 10 ሜ	1 ኪ.ሜ	4.0 - 8.5 ሚ የኢ.ት/ብር
የኮብልስቶን መንገድ፣ ድልድይ ብቻ፣ ስፋት 10ሜ	1 ኪ.ሜ	2.2 - 3.1 ሚ"
የጠጠር መንገድ፣ የላይኛው ብቻ ስፋት 10ሜ	1 ኪ.ሜ	2.5 - 3.0 ሚ"
የአፈር መንገድ ስፋት 10ሜ	1 ኪ.ሜ	0.5 - 1.0 ሚ"
ለሁሉም መንገዶች የታችኛው ስፋት 10ሜ ጥልቀት 1ሜ	1 ኪ.ሜ	1 - 1.7 ሚ"
የኮንክሪት ቱቦ ያለብረት ከ60-100	1 ሊ.ሜ	150 - 300 ሚ"
ኮንክሪት ቱቦ በብረት ከ100 - 150	1 ሊ.ሜ	300 - 500 ሚ"
ኮንክሪት ቱቦ በብረት> 150	1 ሊ.ሜ	500 - 700 ሚ"
የግንብ ተፋሰስ፣ የመከላከያ ግንቦች	1 ሜ3	700 - 1000 ሚ"
ስላቦች ያለብረት ኮንክሪት ግንቦች	1 ሜ3	2500 - 3000 ሚ"
የግንባታ ብረት	1 ኪ.ግ	20 - 30"
የገበያ ሸዶች፣ አነስተኛ ቤት	1 ሜ2	2500 - 4500 ሚ"
የደረቅ ቆሻሻ መሰብሰቢያ መኪና ለ1 ሜ3	በነጠላ	3000 - 3500 ሚ"

ቁልፍ:- • ካመዕ ማለት የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ነው፡፡
• ሊ.ሜ = ሊኒየር ሜትር ማለት ነው

ደረጃ 2 - የፋይናንስ ድርጅታዊ መረጃ

የ' የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ዶክመንት ሁለተኛ ክፍል ቁልፍ መረጃ የያዘ የሠንጠረዦችን ስብስብ የያዘ ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ ያለፊው ጊዜ የካፒታል መዋዕለንዋይ የተጠቃለሉ መግለጫዎች፣ ገቢዎች፣ የካፒታልና መደበኛ ወጭዎች እንዲሁም ሁል አቀፍ የበጀት ትንበያና የመሠረተልማት ጥገና በጀት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ሠንጠረዦች ከሲዲው ጋር ተያይዘው ከቀረበው MS Excel ቴምፕሌት የወጡ ናቸው፡፡

በዚህ ጊዜ ከተማዋ በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ላይ ዝርዝር መረጃ ሊኖራት ይገባል፡፡ በተለይም የተገመተ የመዋዕለንዋይ ወጭ፡፡ ይህ መረጃ ወደ ዝርዝር ፕሮጀክት መግለጫዎች መግባት አለበት (ሠንጠረዥ 5 MS Excel ቴምፕሌት) ከቴምፕሌቱ የሚፈለግ መረጃ የፕሮጀክት ዓይነት፣ አሐድና ተያያዥ የነጠላ ዋጋዎችና መጠን ናቸው፡፡ ሠንጠረዡ በራሱ ጊዜ የገባውን መረጃ በማስላት ከጠቅላላ ዋጋው ላይ ይደርሣል፡፡

ቀጥሎም ከተማዋ በየትኛው ዓመት ፕሮጀክቱ እንደሚተገበርና የትኛውን የፋይናንስ ምንጭ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል ማመላከት ይጠበቅበታል፡፡ የExcel ሠንጠረዥ የካፒታል ገቢዎችን ከታቀዱ መዋዕለንዋዮች ጋር ያወዳድራል (MS Excel ቴምፕሌት ሠንጠረዥ 3)፡፡ ገቢዎችን ከወጭዎች ጋር የማዛመድ ጉዳይ የከተማው ሥራ ነው፡፡ ግዙፍ ተራፊ ወይም እጥረት መኖር የለበትም፡፡ MS Excel ወርክሺት ሠንጠረዥ የ'ካመዕ' ማጠቃለያ ሠንጠረዥ 6 ጋር የተሣሠረ ነው፡፡ የ MS Excel ሺት በራሱ ጊዜ ሥዕላዊ መግለጫዎችን እንደሚያዘጋጅ አስታወስ፡፡ ይህም በክፍል 8 የተገለፀው የቁጥጥር ቴምፕሌት አካል ነው፡፡

አሐዶች (ክፍሎች)፣ ዋጋዎችና ስሌት

ከተሞች በሠንጠረዥ 5 ችግራቸውን የሚሞሉበት እንዳላቸው ልምድ ያስረዳል፡፡ ከዚህ በታች ያለው ዝርዝር ችግሩን የሚያቃልል መረጃ ይሠጣል፡፡

1. በትክክል ሲታይ ሁሉም መንገዶች ከስፋታቸው ጋር በኪ/ሜ ይሰላሉ፡፡ በኮብልስቶን መንገዶች በኩል ሜ2 መለኪያ ሆኖ ይወሰዳል፡፡ ተፋሰስና የአገልግሎት መስመሮች (ውሀ፣ መብራት፣ ስልክ) በቀጥታ መስመር ሜትር ይለካሉ፤ ቀሪዎቹ ጉዳዮችም በቀጥታ አሐዛዊ አሐዶች ይለካሉ፡፡
2. የነጠላ ዋጋዎች በእጅጉ ይለያያሉ፡፡ ይህም በከተሞቹ አቀማመጥና በመሠረተልማቱ ዲዛይን ልዩነቶች ምክንያት ነው፡፡ ስለዚህ ለትክክለኛ የወጭ ስሌት ከተሞች ከራሳቸው ወይም ከአጐራባች ከተማ ተመሣሣይ ፕሮጀክቶች ልምድ መቅሠም አለባቸው፡፡
3. ፕሮጀክቶች ለዝግጅትና ትግበራ በሚወስዱት ጊዜ ይለያያሉ፡፡ በዓለም አቀፍ ጨረታ አማካኝነት የከባድ ማሺነሪ ግዢና ከባቢያዊ የተፅዕኖ ዳሰሳ የሚፈልጉ ፕሮጀክቶች ትግበራን ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያዘጋጃሉ፡፡ ስለዚህ ትግበራው በተለይ በዕቅዱ 1ኛና 2ኛ ዓመት መከናወን ያለባቸው ፕሮጀክቶች ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ማረጋገጥ ጠቃሚ ነው፡፡
4. እርዳታ ሰጭዎች ከዘርፉ ወይም ከፕሮጀክት ጋር የተገናኘ አቀራረብ (ዘዴ) አላቸው፡፡

ይህም ማለት የገንዘብ አስተዋፅኦዎቻቸውን በተለዩ ፕሮጀክቶች ላይ ያውላሉ (ተገቢ በማለት የሚታወቁ ፕሮጀክቶች)፡፡ ለምሳሌ የዓለም ባንክ ጉልበትን መሠረት ያደረጉ መሠረተልማቶችን ይደግፋል እንጅ በዓለም ባንክ ገንዘብ መኪና ሊገዛ አይችልም፡፡

የውጭ ሀብት አጠቃቀም ሁልጊዜ ከተማዋ ተዛማጅ ፈንድ ማቅረብ መቻሏን ያመላክታል፡፡ የከተማዋ የራስ ሀብቶች እርዳታ ሰጪ ፈንድ ተዛማጅ ፍላጐቶችን ለማሟላት የግድ ነው፡፡

በተጨማሪም አብዛኛው የረጅ ፈንድ አሠጣጥ ለረጅ ተኮር የግዥ ሥርዓት ቅድመ ሁኔታዎችን ይዞ ይመጣል፡፡ ስለዚህ በMS Excel ቴምፕሌት ሠንጠረዥ 3 የተዘረዘሩ ሁሉንም የውጭ ሀብቶች ከነዚህ ውስንነቶች አንፃር መከለስና በውጭ ሀብቶች የሚገዙ ፕሮጀክቶችም ተለይተው መዘጋጀት (መዘርዘር) ይኖርባቸዋል፡፡

የሰው ኃይል ሠንጠረዥ

የሰለጠነና በቂ የሰው ኃይል እጥረት ለ'ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' ጤናማ ትግበራ ትልቅ ዕንቅፋት ነው፡፡ የMS Excel ቴምፕሌት ሠንጠረዥ 7 ሁሉንም ፕሮጀክቶችና አጠቃላይ የግምት ዋጋቸውን እንዲሁም ተጓዳኝ የትግበራ ሂደትና የትግበራ ክትትል ባለሙያ በዝርዝር ያስቀምጣሉ (በአብዛኛው ሂደቱ የመሠረተልማት ቁልፍ ሂደትና ተቆጣጣሪውም የከተማ ኢንጅነሩ ነው)፡፡ የዲዛይን፣ ኮንትራት አስተዳደር እና ግዥ ባለሙያ በጥንቃቄ መመረጥ አለበት (እንደፕሮጀክቱ ስፋት)፡፡ እንደሀገሩ 1 ኢንጅነር 10 ሚሊዮን የኢት/ብር ያህል ሊተገብር ይችላል፡፡ የሚፈለግና አሁን በትክክል ያለ የባለሙያዎች ቁጥር በእጅጉ ልዩነት ቢያሣይ የሰው ኃይል ልማት መምሪያው በፍጥነት ባለሙያዎችን መቅጠርና የመነሻ ሥልጠና መስጠት አለበት፡፡

ደረጃ 3 - የ 'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' ዕዝሎች

ሶስተኛው የ 'ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' ክፍል ዕዝሎችን የያዘ ነው:: በዚህ ማኑዋል የተመለከተውን ሂደት ከተከተልን አብዛኞቹ ዕዝሎች ተዘጋጅተዋል:: ቀጥሎ ያለው በእያንዳንዱ ዕዝል ያለውን መረጃ ይዘረዝራል:-

ዕዝል 1:- አጭር ማብራሪያን ጨምሮ የከተማዋ ዝርዝር መረጃ

- ዕውነታዎችና አኃዞች:- ሕዝብና የዕድገት ምጣኔ፣ የመሬት መጠንና መስፋፊያ፣ ሥራ አጥነትና ድህነት፣ የጐሣና የሃይማኖት ስርጭት (ስብጥር)፣
- ታሪክ:- ከተማዋ የተመሠረተችበት ቀን፣ ታሪካዊ ዕድገት፣ ውጤቶችና የዕድገት ምክንያቶች
- የቦታ መገኛ:- መልክአምድራዊ፣ ፖለቲካዊና የአየር ፀባይ ቀጠናዎችና ተዛማጅ አንድምታዎች፣
- የኢኮኖሚ መሠረቶች:- እርሻ፣ አገልግሎት፣ ኢንዱስትሪ፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ንግድ፣ ማዕድንና ወታደር ፣
- አካባቢ:- አፈርና ክለት፣ የገፀ-ምድርና ከርሠምድር ውሀ፣ ዕፅዋትና እንሰሳት፣

ዕዝል 2:- የልማት ግቦችና ዓላማዎች ዝርዝር ነጥቦች

- ያሉ ፕላኖች:- ለምሣሌ መዋቅራዊ ፕላን፣ የከባቢያዊ ልማት ፕላን፣ የመሀል ከተማ ዕድሳት፣ የተፋሰስ መረብ ፕላን (የማፅደቅና የመጨረሻ ቀንን ጨምሮ)፣
- ራዕይና ግቦች:- አጠቃላይና ልዩ -ልዩ ዓላማዎች በተለይም እንደመስፋፊያ አካባቢ ያሉ ስፓሻል ፍላጐቶች፣
- ስኬቶች:- ያለፈ ጊዜ ዓላማን ለማሣካት የተደረገ መሻሻል ዘገባ፣

ዕዝል 3:- የመሠረተልማት ሁኔታና ደረጃ (ከተገኘ ከመሠረ/ልማት አስተዳደር ዕቅድ)

- መንገድና የተፋሰስ መረብ:- መጠን፣ አሁን ያለው መሠረተልማት የመሬት ገፅታና ሁኔታ፣
- ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ:- የቆሻሻ መመረትና አሰባሰብ፣ ነባራዊ መሠረተልማት፣ መኪኖች፣ የአሰባሰብ ሥርዓት፣ የማስፈፀሚያ ወጭና ወጭን የመመለስ መረጃዎች (በአኃዝ)
- የማህበረ-ኢኮኖሚ መሠረተልማትና አረንጓዴ ልማት:- ጤናና ትምህርት፣ ፓርክና አረንጓዴ፣ ገበያዎች፣ የኢንዱስትሪ ቀጠናዎች ቀሪዎች፣
- አገልግሎቶች:- የውሀ፣ ኤሌክትሪሲቲ፣ የመንገድ መብራትና የቴሌኮሙኒኬሽን አቅርቦት
- የሕዝብ ሕንፃዎች:- ዕውነታዎች አኃዛዊ መረጃዎችና ሁኔታዎች

ዕዝል 4:- ዝርዝር የገቢና ወጭ ዳሰሳ (ቅኝት) (ከገቢ ማሣደግ ዕቅድ)

- ያለፈ አፈፃፀም:- ገቢዎች፣ መደበኛና ካፒታል ወጭዎችና ተዛማጅ አዝማሚያዎች
- የራስ ገቢዎች:- የታቀደው መጠንና ምንጮች፣ እንዲሁም ዕድገትና አዝማሚያዎች
- መደበኛ ወጭዎች:- የታቀዱ መጠኖችና ዓላማ፣ እንዲሁም ተጓዳኝ አዝማሚያዎች፣
- የካፒታል ገቢዎች:- የታቀዱ መጠኖች፣ ምንጮች፣ ሁኔታዎች፣ ተዛማጅ ፈንድና የግዥ ፍላጐቶችና አዝማሚያዎች
- መዋዕለንዋይን መልሶ መተካት:- አጠቃላይ ነባራዊ የወጭ ማስመለስ (ወይም መጋራት) ስልቶች

ዕዝል 5፡- የአማታፊ ሂደት ዝርዝር ሐሳቦች

- የአጋር መረጃ፡- ነባራዊ የአጋር ቡድኖችና ፍላጐቶቻቸው
- የትኩረት ቡድን ውይይት፡- ገለፃ፣ ዘገባና፣ ውጤቶች
- የመጀመሪያ የሕዝብ ስሚ፡- ገለፃ፣ ዘገባ (ጥሪ፣ ፎቶ፣ ፊልም) እና የቀዳሚ ፍላጐቶች የተቀመረ ዝርዝር
- ሁለተኛ የሕዝብ ስሚ፡- ገለፃ፣ ዘገባና የቀዳሚ ፍላጐቶች/ፕሮጀክቶች ዝርዝር
- ፎቶዎች፣ ፊልም፣ ጥሪ፣ የድምፅ አሠጣጥ ዘገባ ወዘተ

ዕዝል 6፡- የእያንዳንዱ ፕሮጀክት ክፍሎች፡-

- የፕሮጀክት መግለጫ
- " ምጣኔ ሀብታዊ ጥናትና ፋይናንስ
- " አስፈላጊነትና ውጤት

ዕዝል 7፡- የጥገና ዕቅድ ከተጓዳኝ የሰው ኃይል ዕቅድ ጋር

- በጀት፡- ለጥገና የተመደበ በጀት ዝርዝር ክፍሎች
- ድርጅት፡- ሴክተር-ተኮር ጥገናን ማመቻቸት (ለምሣሌ የመንገድ ጽዳትና አረንጓዴ ልማትና ሥራን ለሌላ ፈፃሚ መስጠት)
- መልሶ ማደስ፡- ዋና - ዋና የጥገናና ዕድሳት ሥራ

ዕዝል 8 እና 9 በቀጣዩ ክፍል ይገለፃሉ

ክፍል 7

የግዥና የገንዘብ ፍሰት ዕቅድ

የዚህ ክፍል ዋና ዓላማ የ ‘ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ’የግዥና ዓመታዊ የገንዘብ ፍሰት ዕቅድን ማዘጋጀት ነው፡፡ እነዚህ ዕቅዶች መዋዕለንዋይ እንዴት እና መቼ እንደሚገዛና የገንዘብ ፍሰት ፍላጐት እንደሚፈጠር መሠረት ይጥላሉ፡፡
የግዥ አስተዳደር 6 መሠረታዊ ደረጃዎች ያቅፋል፡-

1. የግዥ ዕቅድ
2. ማስተዋወቅና አቅራቢውን ማግኘት
3. መክፈት
4. መገምገም
5. ድርድርና ኮንትራት መስጠት
6. ኮንትራት አስተዳደር፡፡ የግዥ ዕቅድ ማለት እያንዳንዱን ደረጃ በቅደም ተከተል በጊዜ ሰሌዳ ማቀድ ማለት ነው፡፡

እነዚህን ዕቅዶች ማዘጋጀት መሠረታዊ የግዥና የገበያ ስልቶች ዕውቀትን ይጠይቃል፡፡ ከተገቢ የቴክኒክ መምሪያዎች ጋር የገንዘብና ኢ.ኮ/ል/ጽ/ቤት በቅንጅት የግዢና የገንዘብ ፍሰት ዕቅድን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፡፡ የግዥና የገንዘብ ፍሰት ዕቅዶች ከዋና የ’ካመዕ’ ዶኪመንት ዕዝል 8 ና 9 ጋር በቅደም ተከተላቸው ይቀርባሉ፡፡

ደረጃ 1 - የግዥ ሁኔታዎችን መወሰን

የግዢ ሂደት ግብ ግልፅ፣ ተጠያቂነት ባለውና ተገቢ በሆነ የጨረታ ሂደት የደንበኛውን ፍላጐት የሚያሟላ የተሻለ አቅራቢ መለየት ነው፡፡ ስለሆነም ሁሉም መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጫራቾች ተመሣሣይ መረጃ ይሠጣቸዋል፡፡ ለመወዳደርም ዕኩል ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ ምንም እንኳ በሕዝብ ግዥ ዝቅተኛው ዋጋ ብቻ ተቀባይነት ቢኖረውምአነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ሁሉ የተሻለ አቅራቢ ሊሆን እንደማይችል ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ የተሻለ አቅራቢውን መለየት ማለት ግልፅና የማያምታታ የተጫራች መምረጫ መሥፈርት ማቅረብና በጨረታ ዶኪመንቱ የሥራውን ስፋትና ውስብስብነት በግልፅ ማስረዳት ነው፡፡ ከተሞች ግዢን ለማስተዳደር ብቻ ሳይሆን ገበያን ለማጥናትና የሥራ ሕጉንም ለመወሰን ጭምር ክህሎት ያለውን ሠራተኛ መመደብ (መምረጥ) አለባቸው፡፡ የMS Excel ሠንጠረዥ 5 የፕሮጀክት ዝርዝሮች የታቀዱ ፕሮጀክቶችን ግምት ዋጋቸውንና የፋይናንስ ምንጫቸውን ይዘረዝራል፡፡ እነዚህ ሶስት ጉዳዮች በግዥ ላይ ወሳኝ ተፅዕኖ አላቸው፡፡

- **የፕሮጀክቱ አድማስ፡-** ፕሮጀክቱ በጣም ውስብስብ በሆነ ቁጥር ግዢውም በጣም ዘርዘር እንዲል ይፈለጋል፤ እናም ለዕቅድ ዝግጅት ሂደት ሠፊ ጊዜ ይመደብለታል፡፡ ለምሳሌ የቆሻሻ መጣያ ቦታ ዲዛይን፣ የኮንትራት ቁጥጥርና ለግንባታው ግዥ የአማካሪ ሥራን ይጠይቃል፡፡ ሌሎች ፕሮጀክቶች (አነስተኛ ደረጃ የጐርፍ ማፋሳሻ ---) ቀላል የግዥ ሥርዓትን ይጠይቃሉ፡፡ ውስብስብነት በቀነሠ ቁጥር ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ መለስተኛ ልምድ ላላቸው ዝቅተኛ ኮንትራክተሮች የኮንትራት ተደራሽነትን ይጨምራል፡፡ አነስተኛ ኮንትራክተሮች የከተማ አስተዳደሩን ድጋፍ ይሻሉ፡፡ ለምሣሌ ከተማ አስተዳደሩ ማሺነሪ ሊያቀርብ ጥሪ ቢያደርግ፡፡

- **ዋጋ፡-** የፕሮጀክት ግምት ዋጋ ከፍተኛ ከሆነ ግዥው ውስብስብ ይሆናል፡፡ ለምሣሌ የኢትዮጵያ የግዥ ደንብ (ሲዲ ዕዝል 4) ፕሮጀክቱ ከ250, 000 የኢትዮጵያ ብር በታች ከሆነ ብቻ ግዥው በአካባቢ ገበያ እንዲፈፀም ይፈቅዳል (‘ULGDP’ን) በሚመለከት ግን ከ500, 000 የኢት/ብር በታች ነው፡፡ ስለዚህ ለአነስተኛ ተቋማት ዕድል ይሠጣል፡፡ ከዚህ ወለል በላይ ከተማዋ የሀገር ውስጥ ጨረታንና አንዳንዴም አለምአቀፍ ጨረታን ልትጠቀም ይገባል፡፡

- **ምንጭ፡-** የውጭ ሀብት (በተለይ የረጂ ድርጅቶች) ከተሞች የተለየ የግዥ ሥርዓት እንዲከተሉ ያስገድዳል፡፡’KFW’ ለምሣሌ የአካባቢ ገበያ ግዥን አይፈቅድም በተጨማሪም የቀጥታ ኮንትራትንና በራስ ግዥን የማካሄድ ዘዴ (ቀጥሎ ደረጃ 2 ተመልከት) በጥብቅ ገደቦች ከሆነ ብቻ እንዲከናወን ይፈቅዳል፡፡

የጨረታ ሂደቱን በርካታ ሌሎች ምክንያቶች ይወስኑታል፡፡

- **የግዥ ፈርጆች፡-** የግዥ ፈርጆች ሥራዎች፣ የምክር አገልግሎቶች፣ ሸቀጣሸቀጦችና ሌሎች ናቸው፡፡ትልቁና አብዛኛው የከተማ አስተዳደሮች የ’ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ’ የመሠረተልማት

ፕሮጀክቶችን ያቀፈ በመሆኑ ይህ ክፍል የሥራዎች ግገርን ብቻ እንደሚያካትት አስታ ወስ፡፡ የግገር ፈርጆችና ወለሎች የትኛውን የግዥ ዘዴ መጠቀም እንደሚገባ ይወስናሉ፡፡ ስለሆነም የፈርጁ ምርጫ ለጨረታ ሂደቱ በሚያስፈልገው የጊዜ መጠን ላይ ወሳኝነት አለው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ኮንትራቶች በነጠላ ፈርጅ ውስጥ ይሰጣሉ፤ (በተለይም በ' ካፒታል መዋዕለንዋይ' ጊዜ አብዛኛውን ለሥራዎች) ምንምእንኳ አንዳንድ ጊዜ የተለዩ ሁኔታዎች ቢኖሩም፡፡ የተለዩ ዓይነት የማሽን መሣሪያዎች ለምሣሌ እንደቁፋሮ ግንባታ ያሉት በአቅርቦትና ተከላ ሥምምነት መሠረት ግዢቸው ይፈፀማል፡፡ ይህም የዕቃ አቅርቦቱና የኢንስታሌሽን አገልግሎቱ በነጠላ በኮንትራቱ ስለሚካተት ነው፡፡

- **የስምምነት ማዕቀፍ** ኢኮኖሚንና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ለጨረታ ሂደት ፓኬጆችና ጠቅላላ አቅርቦቶች እንዴት እንደሚያደራጁ ይገልፃል፡፡ ለምሣሌ መጠለያ ያለው የገበያ ግንባታ፣ የሕዝብ ሽንት ቤቶች፣ የቆሻሻ አወጋገድና የተፋሰስ መስመሮች በአንድ ጥቅል ወይም በበርካታ ነጠላ ኮንትራቶች ሊገዙ ይችላሉ፡፡

  ጥቅሉን በመወሰን የከተማ አስተዳደሩ የእንደዚህ ዓይነት ውስብስብ ኮንትራቶችን ዕቅድ አስተዳደርና የማጣጣም ሥራ ላይ ጫና ያሣድራል፡፡

- **የግዥ ጊዜ፡-** በተወሰኑ ሁኔታዎች ምን ዓይነት የግዥ ዘዴ መከተል እንደሚገባ ጊዜ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ለምሣሌ ለብዙ ዓይነት ግንባታ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ትራክተሮችን እንውሰድ፡፡ እነዚህ ዓይነት መኪኖች በዓለም አቀፍ ጨረታ ወይም በሀገር ውስጥ ጨረታ ቢገዙ ሂደቱ ለአንድ ዓመት የተቃረበ ጊዜ ይወስዳል፡፡ ስለሆነም ከተማው ጊዜን ለመቆጠብ ሌሎች ሁኔታዎች ዕቃውን የማግኘት ማረጋገጫ እስካለ ድረስ ቀጥታ ግገርን (ብቸኛ አቅራቢ) ሊወስን ይችላል፡፡

ደረጃ 2 - የግዥ ዘዴዎች (ሥራዎች)

የኢትዮጵያ የግዥ ደንብ (ሲዲ ዕዝል 4) የተደራጁ ግገሮችን ማለትም የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ግገሮችን፣ የአካባቢ ግገርንና ቀጥታ ግገርን ዕውቅና ይሰጣል፡፡ ረጅዎች እንደ 'ULGDP' ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ የአካባቢ ጨረታና የኅብረተሰብ ተሣትፎ ያለበት ተጨማሪ የግዥ ዘዴን ሊያስተዋውቁ ይችላሉ፡፡ የግዥ ዘዴው ለአንድ ጨረታ ውጤት ትልቅ አንድምታ አለው፡፡ በተጨማሪም የግዥ ዘዴዎች ረጅዎች የጨረታ ዶኪመንቱን አስቀድመው ወይ በኋላ የጨረታ ዶኪመንቱንና የጨረታ ግምገማ ሪፖርቶችን ለመፈተሽ ይጠይቁ እንደሆን ይወስናል፡፡ ተቀባይነት ያላቸው የግዥ ዘዴዎች ባጭሩ ቀጥሎ ተመልክተዋል፡፡

ዓለምአቀፍ ጨረታ ውስብስብና ማሺንን መሠረት ያደረጉየሕዝብ መዋዕለንዋዮችን (ግድቦች) እንዲሁም ውስብስብ ማሺነሪን (ምሣሌ ቫክዩም-ትራክ) ለማግኘት ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡ የረጅዎች የገንዘብ ድጋፍ ካለበት ከ500,000 የአሜሪካ ዶላር ለሚበልጡ ሥራዎችና በ'ULGDP' ዕቃዎች ሁኔታ ደግሞ ከ500,000 ዩኤስ ዶላር በላይ ለሆኑት አለምአቀፍ ግልፅ ጨረታ ይፈልጋል፡፡

የሀገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ የውጭ ተወዳዳሪዎችን የማይጠይቁ ሥራዎችን ወይም ዕቃዎችን ለመግዛት አዋጭና ቆጣቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ዓለምአቀፍ ግልፅ ጨረታው በአስተዳደራዊ ወይም በፋይናንስ ጫናው አላስፈላጊነቱ በግልፅ ተተንትኖና ተፎካካሪዎች በአካባቢ በበቂ ሁኔታ መኖራቸውን ገልፆ ሊሆን ይገባል፡፡ የሀገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያው በይፋ ለሆኑ ዕቃዎችና ከ5,000,000 የአሜሪካ ዶላር በታች ለሆኑ ግንባታዎች ሊሠራ ይችላል፡፡

ለአካባቢው ግዥ ከ250,000 በታች የኢት.ብር ላነሡ ሥራዎች (ለ'ULGDP' ከ50,000 ዩኤስዶላር በታች)፣ ለዕቃዎች ከ100,000 የኢትዮጵያ ብርና ለምክር አገልግሎት ከ60,000 የኢትዮጵያ ብር በታች ቢያንስ መሥፈርቱን የሚያሟሉ 3 የአካባቢ ኮንትራክተሮች ወይም የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ሊጫረቱ ይችላሉ፡፡ ኮንትራቱ ለኮንትራክተር ወይም አነስተኛ ወጭን ለቀነሱ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለኮቴሽኑ በቀረበው ጥያቄ በተገለፀውና ለተጫራቾቹ ሁሉ በተላከው መሥፈርት መሠረት ይሠጣል፡፡ ይህም ቢያንስ 3 አቅራቢዎች እንደቀረቡና እንደተወዳደሩ ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ ሁሉም አቅራቢዎች ከከተማው ማጣቀሻ ዋጋዎች የነጠላ ዋጋ መረጃ ከበለጡ ከተማው በዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበውና መሥፈርቱን ካሟላው ተጫራች ጋር ሊደራደር ይችላል፡፡ ድርድሩ በዝቅተኛ ዋጋው ካላስማማ የከተማ አስተዳደሩ የሥራውን ስፋት እንደገና ሊፈትሽና የነጠላ ማጣቀሻ ዋጋዎችን ሊከልስ ወይም አማራጭ ሊያፈላልግ ይችላል፡፡

የራስ ግዥ፡- በኢትዮጵያ የራስ ገዥን ለመጠቀም የተለየ የአሠራር ሂደት አልተቀመጠም፡፡ስለዚህ ከዚህ መንገድ መውጣት እጅግ የተሻለ ነው፡፡ በ'ULGDP' የራስ ግዥን ዘዴን ለመጠቀም ከተሞች የሚከተለውን መረጃ መሰብሰብ እና ከከተማ ም/ቤቱ ይሁንታ ማግኘት አለባቸው፡-

- የተለዬ ሥራን በራስ ግዢ ለመፈፀም ግምታዊ ዋጋና አጥጋቢ ምክንያት፣
- የራስ ግዥ ክፍሉ አቅምና ከከተማ አስተዳደሩ ጋር ያለው ግንኙነት ዝርዝር መረጃ፣
- የነጠላ ዝርዝር ዋጋዎች አወሳሰን ስልቶችና የአሠራር ሥርዓቶች ፣
- ለሥራው ጥራት ቁጥጥር የተጠቆመ አደረጃጀት ፡፡
- ለተጠቀሰው ልዩ ሥራ ተዛማጅ የሚባል ሌላ መረጃ ፣

ይህም ሆኖ የራስ ግዢ ዘዴ ብዙ ክፍተቶችን እንደሚያሣይ አስተውል፡፡ ረጅዎች ይህ ዓይነቱን የግዥ ዘዴ በተለዬ አስገዳጅ ሁኔታዎች ብቻ ይፈቅዳሉ፡፡

ቀጥታ ግዥ/ኮንትራት፡- የኢትዮጵያ የግዥ አዋጅ ቀጥታ ግዥ የሚከተሉት እስከተሟሉ ድረስ ብቻ ተገቢ እንደሆነ ያትታል፡፡ እነሱም፡-

- ዕቃዎች ወይም ሥራዎች በአንዱ እጩ ብቻ ከቀረቡ፣
- ለመተካትም ይሁን ያሉትን አቅራቢዎች ለማስቀጠል ተጨማሪ የዕቃ አቅርቦቶች በመጀመሪያ አቅራቢው እንዲቀርቡ ከተፈለገ ፣
- የሚመለከተው የመንግስት ኃላፊ አስቸኳይ ፍላጐት እንዳለ ከወሰነ፣
- የመንግስት አካላትን የተለየ የግዥ ፍላጐት ለማሟላት ግዢው አስፈላጊ ከሆነ፣

የአካባቢ ግልፅ ጨረታ (አግጨ)፡-

የዓለም ባንክ የ'አግጨ' ግዥ ዘዴን በአይዲኤ ፋይናንስ ለሚደገፉ ፕሮጀክቶች እስከ 100,000 የአሜሪካ ዶላር በከተማ አስተደደሮች ሥራ ላይ እንዲውል አስተዋውቋል፡፡ በዚህ ሂደት የአካባቢ አነስተኛ ኮንትራክተሮችና ጥቃቅን አነስተኛ ተቋማት እንዲወዳደሩ ይጋበዛሉ፡፡ የማስተዋወቅ ሥራውም በአካባቢ ጋዜጦች፣ ሬዲዮ ጣቢያዎችና የከተማ አስተዳደር የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ቢያንስ ለ15 ቀናት መካሄድ ይኖርበታል፡፡ ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢው በከተማ አስተዳደሩ የዋጋ ግምት ወለል ውስጥ ከሆነ ድርድር አይፈቀድም፡፡ አንድ ተጫራች ብቻ እንኳ ምክንያታዊ የሆነ ዋጋ ቢያቀርብ ኮንትራቱ ሊሰጠው እንደሚገባ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

የማህበረሰብ የግዥ ተሣትፎ፡-

በ'ULGDP' ግዥ አንድ ፕሮጀክት በቀበሌ ወይም በማህበረሰብ የከተማ አስተዳደሩ ክትትል/ቁጥጥር የሚተገበሩ አነስተኛ ደረጃ ጉልበት ተኮር የፕሮጀክት ክፍሎችን (ሥራዎችን) ሊያቅፍ ይችላል፡፡ የፕሮጀክቱ ክፍሎች ቀላል ጨረታ ሰነድን በመጠቀም ለኮንትራት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በኅብረተሰብ ተሣትፎ የሚከናወኑ ተግባራት ኮንትራቶችን ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር የተለዩ የአመራር ሥርዓቶችን መከተል አለባቸው፡፡ የፕሮጀክት ክፍሎችንና ኮንትራቶችን (ሲዲ ዕዝል 4.2) አሠጣጥ የሚገልፁ የናሙና ጨረታ ሰነዶች መመሣከር (መጣቀስ) አለባቸው፡፡

- በአጭር ጊዜ ውስጥ ብቻ በተፈጠሩ ልዩ ጠቃሚ ሁኔታዎች የሚገኙ ዕቃዎች ጥያቄ ሲኖር፣
- በመጀመሪያው ኮንትራት ያልተካተቱ ተጨማሪ ሥራዎች ባልተጠበቁ ሁኔታዎች አስፈላጊ ከሆኑ፣
- የተመሣሣይ ሥራዎች ድግግምን ያካተቱ አዳዲስ ሥራዎች ሲኖሩና ሆኖም ግን የመጀመሪያው ኮንትራት በውስን ወይም በግልፅ ጨረታ መሠረት የተሠጠ ከሆነ፣
- ቀጣይ የአማካሪ አገልግሎት ፍላጐት ሲኖር ማለት የመጀመሪያው ኮንትራት በአጥጋቢ ሁኔታ ከተፈፀመና በጋራ አስተዋፅኦ አዋጭና ቆጣቢ ሆኖ ሲገኝ፣
- ቀጥተኛ ግዥ ስለሚከናወንበት ሁኔታ ዝርዝር መረጃ ሲዲ ዕዝል 4 ተመልከት

ደረጃ 3 - የግዥ ዕቅድን ተመልከት

እያንዳንዱ የ' ካፒታል መዋዕለንዋይ' ዝርዝር በራሱ ገንዘብም ተገዛ በረጅ የሀብት ምንጭ በግዥ ዕቅዱ ላይ መንፀባረቅ አለበት፡፡ የግዥ ቴምፕሌቱ የቴክኒክ መረጃ ሀብትን ይፈልጋል፡፡ ቴምፕሌቱ የፕሮጀክት ጥናቱ በሚገባ ከተዘጋጀ ብቻ ይጠናቀቃል፡፡

ስለዚህ ቴምፕሌቶቹን ከመሙላት በፊት የግዥ ኦፊሰር የዲዛይን፣ ዝርዝር የዋጋ መግለጫ፣ የዕቃ ዓይነትና ልዩ ወይም መደበኛ የግዥ ማስታወቂያን ጨምሮ የእንዳንዱን ፕሮጀክት የጨረታ ሰነድ አጠቃላይ ፍተሻ ያደርጋል፡፡ የተረሱ ጉዳዮች ካሉም የግዥ ኦፊሰሩ ሂደቱን ለመከታተልና ዋና ዶኪመንቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ጊዜ ያሰላል፡፡ የግዥ ቴምፕሌቱን ለማሟላት (ለማጠናቀቅ) የሚከተለው መሠረታዊ መረጃ ያስፈልጋል፡፡

(ይህን ክፍል ስታነብ የቴምፕሌት ፋይሉን ማጣቀስና ክፍት አድርጎ መተው ጠቃሚ ነው)፡-

- **የፕሮጀክቱ መግለጫና ተራ ቁጥር፡-** ተራ ቁጥሮች የተለዩና አጭርና ገላጭ የፕሮጀክት ስያሜን የተከተሉ መሆን አለባቸው፡፡

- **ውስብስብነት፡-** የጨረታ ዶኪመንቶች ዝግጅት እንደፕሮጀክቱ ውስብስብነት ይለያያሉ፡፡ በተጨማሪም ውስብስብነት ከጨረታ ቀኖች ጋር ተያያዥነት አለው፡፡ እዚህ ላይ 'በውስብስብ' ወይም 'ቀላል' አቀራረብ መካከል ተጠቃሚው ሊመርጥ ይችላል፡፡ በ'ULGDP' ለሚገዙ ፕሮጀክቶች በግዢ ሥርዓቱ ላይ ይህ ልዩነት የሚፈጥረው ጫና የለም፡፡

- **ጥቅልና ጠቅላላ ቁጥር፡-** የጥቅል ቁጥሮች ከሚከተለው የተግባር ዕቅድ (የከተማ ስም፣ የሀብት ምንጭ፣ የግዥ ምድብ ቁጥር፣ የግዥ ዓመት) ጋር መጣጣም አለበት፡፡ ለምሣሌ የሆሣዕና ከተማ በ2003 ዓመተ ምህረት በራሷ ሀብት የኮብልስቶን መንገድ መገንባት ትፈልጋለች እንበል፡፡ ተዛማጅ ኮዱም፡- ሆሳ/መንግ/ሥ-001/2003 ይሆናል፡፡ 'መንግ' የሚለው መንግስትንና 'ሥ' የሚለው ደግሞ ሥራዎችን ይወክላል፡፡ ይህን ፕሮጀክት አስመልክቶ በሚደረግ ማናቸውም ግንኙነት የጥቅል (Package) ቁጥሩ እንደማጣቀሻ ሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡ የአጠቃላይ (Lot) ቁጥሩ ግን የኮንትራት ፖኬጁ በጣም ውስብስብ ከሆነ ብቻ ነው ሥራ ላይ የሚውለው፡፡

- **የዋጋ ዝርዝር ድምር፡-** ብዙ ፕሮጀክቶች ዘርዘር ያለ እና የሥራውን እያንዳንዱን ደረጃና ለእያንዳንዱ ደረጃ የሚያስፈልገውን የፋይናንስ ጨረታ የሚገልፅ የዋጋ ዝርዝር አላቸው፡፡ በትክክል ሲታይ የዋጋ ዝርዝር የመለኪያ አሐድን እና ተጓዳኝ መጠኖችን ያስቀምጣል፣ የተፈላጊ ዕቃ ዓይነት ዝርዝርንም ይተነትናል፡፡ ይሁን እንጅ አንዳንድ ፕሮጀክቶች ጥቅል መጠንን ይፈልጋሉ፡ - ለምሣሌ የዕቃዎች ግዥ፣

- **የግዥ ደንብና ዘዴ፡-** የጨረታ መክፈቻ ጊዜዎች እንደግዥ ዘዴው ይለያያሉ፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ነገሮች የተለያየ ግዥ ደንቦች አሏቸው በተለይም ጊዜንና የዋጋ ወለልን አስመልክቶ፡፡ ስለዚህ የግዥ ዘዴ ውሳኔ ለባለሙያው ቢተው የተሻለ ነው፡፡ የግዥ ቴምፕሌት በባለሙያው የግዥ ዘዴ ምርጫ ላይ ተመሥርቶ የጊዜ አንድምታን በራሱ ያሰላል፡፡

- **ግምታዊ መጠኖች** • እያንዳንዱ ፕሮጀክት ባለፉት ክፍሎች እንደተገለፀው ባለው የፕሮጀክት ዲዛይንና ቴክኒካዊ ዝርዝር የዕቃ ዓይነት መለያ ጥናት ላይ ተመሥርቶ የዋጋ ግመታን ያከናውናል፡፡ የግዥ ሠንጠረዥ ባለው ወቅታዊ የምንዛሬ ልውውጥ ምጣኔ መሠረት የኢትዮጵያ ብርን በዶላር መጠን ያሰላል፡፡ ይህም መጠን ወደተዛማጅ መስክ ሊገባ ይገባል፡፡

- **የጨረታ ሪፖርቶች ዶኪመንቶች ቅድመና ድህረ-ቅኝት፡-** የግዥ ዕቅዱ ቅድመጥናት ለውጭ ፈንድ ብቻ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህም በአብዛኛው ከተሞች የአካባቢ ግዥን ወይም ቀጥታ ግዥን ሲፈልጉ ወይም የኮንትራት መጠኑ የተወሰነውን ወለል ሲያልፍ (በ'ULGDP' ሁኔታ 5 ሚሊዮን



ስዕል 22፡- በራስ ኃይል ከመሥራት ወደ ግልፅ ጨረታ

የኰብልስቶን ግዥ

ከተሞች መጀመሪያ የኰብልስቶን ዘርፉን ሲያንቀሳቅሱ ተፈላጊ ሥራዎችን ለመግዛት ሁልጊዜ የራሳቸውን ኃይል ይጠቀማሉ፡፡ ይሁን እንጅ ይህ ዘዴ አይመከርም፡፡ ምክንያቱም ከተሞች በአጠቃላይ የግንባታ ሂደት ውስጥ ሰምጠው ገብተው አስተዳደራዊና የማቴሪያል አቅርቦት አቅማቸውን ማዳከም የለባቸውም፡፡

የመጀመሪያው አስተሳሰብ (ከላይ የተጠቀሰው) ምን ያህል የራስን ኃይል የመጠቀም ዘዴ በኮብልስቶኑ ድርጅታዊ ሂደት ከተማዋን አጣብቂኝ ውስጥ ማለትም እንደድልድይ ሥራ፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ የሠራተኛ ደሞዝ ክፍያ፣ የሥራ ጥራትና የሠራተኛ ምርታማነት ቁጥጥር ያሉ ውስብስብ ተግባራትን ከማቀናጀት እንደሚያስገባት ያሣያል፡፡ አንድምታው ከተማዋ አንዴ የነዚህን የመንገድ ግንባታዎች እንደጨረሰች አጠቃላይ ዘርፉ ይወድቃል፡፡

ሁለተኛው አመለካከት በግንባታ ውስጥ አጠቃላይ የግንባታ ዑደቱን የሚመራ መቋቋም ያለበት ጠንካራ ኢንተርፕራይዝን ያሣያል፡፡ ይህም የጽ/ቤት፣ የግንባታና የኮንትራት አስተዳደሩን ማከናወን የሚችል የግንባታ ኮንትራክተር ወይም የጥ/አ/ኢንተርፕራይዝ ሚና ነው፡፡ በዚህ አመለካከት ከተሞች እንደደንበኛ ይሆኑና ሥራዎችን በጨረታና ልዩ- ልዩ ዘዴ ሊገዙ ይችላሉ፡፡ የነፃ ገበያ አሠራር አስተሳሰብ ከአቅርቦትና ፍላጐት ስልቶች ጋር ዋጋን በእጅጉ ይቀንሳል፡፡ በመጨረሻም በደንበኛና በኮንትራክተር መካከል ያለው ግልፅ ልዩነት ደንበኛው ከኮንትራክተሩ የተሻለ አፈፃፀምን ስለሚፈልግበት ወደ ጥራት መሻሻል ያደርሣል፡፡ የኮንስትራክሽን ከተማ ልማት ሚ/ር ከተሞች ሥራውን ለኮንትራት እንዲሰጡ የሚረዳ የኮብልስቶን ግዥ ማኑዋልን አቅርቧል፡፡ አልፎም ስታንዳርድ የጨረታ ሰነዶችን (ኮንትራቶችን የዋጋ ዝርዝርን፣ የቴክኒክ ዝርዝር ጥናቶችን የኮብልስቶን ሥራዎችን ግዥ ለማመቻቸት) አዘጋጅቷል (አቅርቧል)፡፡ (ሲዲ ዕዝል 4.3)

አውቶማቲክ ቴምፕሌቶች

የከተማ ልማት ሚ/ር ደረጃቸውን የጠበቁና አውቶማቲክ ቴምፕሌቶችን የምክር አገልግሎት፣ የዕቃና ሥራዎች ግዥን ለማስላት እንዲቻል አዘጋጅቷል፡፡ የ'MS Excel' ቴምፕሌት (የሰነድ ሲዲ ተመልከት)፡፡ አስቀድሞ ፕሮግራም የተደረጉ የግዥን ዕቅዶች 3 ጉዳዮች ያሚያል፡፡ ማለትም አንድ ለግንባታ ሥራዎች፣ አንድ ለዕቃዎችና አንድ ለአማካሪ አገልግሎቶች፡፡ እያንዳንዱ ታብ ሁለት ሠንጠረዦችን ይዟል፡፡ በቴምፕሌቱ ግራ ጐን ያለው ሠንጠረዥ (ሠንጠረዥ 23) መረጃ ለማስገባት ነው፡፡ ሌላው (ሠንጠረዥ 24) በደንብ የተዘጋጀ የግዥ ዕቅድን ይመልሳል፡፡ ሠንጠረዥ 23 የግዥ ሥርዓቱን ለመወሰን የሚያስፈልጉ መሠረታዊ መረጃዎችን ይይዛል፡፡ ተጠቃሚው የግዥ ሥርዓቱን ሊመርጥና ቅድመ ወይም ድኅረ ፍተሻ ያስፈልግ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ይህ መረጃ 'MS Excel' በግዥ ዕቅዱ ውስጥ ወዲያውኑ እንዲያካትት ያስችለዋል፡፡ የግዥ ቴምፕሌቱ ሠንጠረዥ 2 (ቁ. 24) የግዥ ዕቅዱ ራሱ ነው፡፡ በመጀመሪያው ክፍል በገባው መረጃ መሠረት ዕቅዱ በፕሮጀክቱ አመራር ዑደት ጊዜ መሟላት ያለባቸው የተለያዩ የጊዜ ገቦችን ያስቀምጣል፡፡ የ3ቱ የግዥ ዕቅድ 'ታቦች' መረጃ ወደ ገንዘብ ፍሰት ዕቅድ 'ታብ' ወዲያውኑ ይተላለፋል፡፡ ይህም በተራው ወዲውኑ ይሞላል፡፡ የ'MS Excel' ሠንጠረዥ ወደ ትክክለኛው የ'ካመዕ' ሰነድ 'ካመዕ' ዕዝል 8 እና 9 ወዲውኑ በቀጥታ ይገናኛል፡፡ እናም ኮፒ ይሰጣል አላስፈላጊ መረጃንም ያሽጋግራል፡፡

	ሀ	ለ
8	መሠረታዊ መረጃ ዝርዝር 2	
9	ተራ ቁጥር (ተ/ቁ)	1
10	የፕሮጀክቱ መግለጫ	1.1.1 የአስፋልት መንገድ ቁ. 1
11	የፕሮጀክቱ ውስብስብነት	ዉስብስብ
12	የፓኬጅ ቁጥር	1
13	ጥቅል ቁጥር	1
14	ድምር ወይም የዋጋ መጠን	የዋጋና የመጠን መግለጫ ዝርዝር
15	ሥራ ላይ የዋለ የግዥ ደንብ	የኢትዮጵያ
16	የግዥ ዘዴ	አገር ዓቀፍ ገልፅ ጨረታ
17	የተገመተው መጠን በኢትዮጵያ	
18	የተገመተው መጠን በአሜሪካ	
19	የጨረታ ሰነዶችና ቅድመና ድ	
20	የጨረታ ሪፖርት ቅድመና ድኅረ ቅኝ	የጨረታ ሪፖርት ቅድመ ምልከታ
21	ዕቅድ	ዕቅድ
22	የተከለሠ	
23	የ'SPN, BI/CA' የታቀደ ቀን	10/10/2012
24	የ'SPN, BI/CA' የተከለሠበት ቀን	
25	የኮንትራት አፈፃፀም (ሣምንታት)	20

ዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ
አገር አቀፍ ግልፅ ጨረታ
የአካባቢ ግብይት
የቀጥታ ግዢ
በራስ ኃይል መስራት

ስዕል 23፡- የግዥ ዕቅድ ቴምፕሌት ሠንጠረዥ 1 የመረጃ ግብዓት ሠንጠረዥ

የግዥ ደንቦችን ታሣቢ ያደረገ የጨረታ ጊዜ (በቀናት)				0	የዝግጅትና ማቅረቢያ ጊዜ ውስብስብነትን ግምት ውስጥ አስገብቶ (በቀናት)				0				
	የዋጋ ዝርዝርና የዕቃ ዓይነትን ያካተተ የጨረታ ሰነድ ረቂቅ		ልዩ የግዥ ማስታወቂያ	የጨረታ ጊዜ		የጨረታ ግምገማ ሪፖርት ማቅረብ	የኮንትራት ማጠናቀቂያ			የመልካም አፈፃፀም ማቅረቢያ	የኮንትራት ማጠናቀቂያ		
ዕቅድ	ዝግጅትና ማቅረቢያ	ተቃውሞ የማይቀርብበት		የጨረታ ጥሪ	የመዝጊያ (የመክፈቻ)		ተቃውሞ የማይቀርብበት	ኮንትራት የሚሠጥበት	ፊርማ		ንቅናቄ	መጀመሪያ	ማጠናቀቂያ
የተከለሠ													
ትክክለኛ													

ስዕል 24፡- የግዥ ዕቅድ ቴምፕሌት ሠንጠረዥ 2 በራሱ የተዘጋጀ የግዥ ዕቅድ

የአሜሪካ ዶላር) ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አብዛኛዎቹ የሥራ ግዢዎች የጨረታ ሪፖርቶችን ወይም ዶኪመንቶችን ቅድመ ቅኝት አይጠይቁም፡፡ ይሁንና በውስብስብ የአማካሪ ግዢዎች ጊዜ ሥራውን የመሥራት ብቃት ያላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች በገበያ ላይ ጥቂት ከሆኑ ብቻ የቅድሚያ መስፈርቶችን ማስቀመጥ ይጠይቃል፡፡

- **የታቀደና የተከለሰ፡-** እነዚህ የጐን መስመሮች የግዥ ባለሙያው የታቀደ ወይም የተከለሰ የግዥ ዕቅድ ሰነድ ሊያዘጋጅ ይፈልግ ከሆነ የግዥ ትግበራ ደረጃን ያመላክታሉ፡፡ የግዥ ባለሙያው የትግበራውን ትክክለኛ ደረጃ ለማመልከት ሲፈልግ ይህን መረጃ ወደሠንጠረዥ በራሱ ማስገባት አለበት፡፡
- **የታቀዱና የተከለሱ ቀናት፡-** ቀን ሁሉንም ሌሎች ቀኖች (dates) በራሱና ወዲያውኑ ለማስላት የሚረዳ ቁልፍ ቀን ነው፡፡ ቀኑ በግዥ ሥርዓት ላይ ተመሥርቶ ሊለያይ ይችላል፡፡ በዓለምአቀፍ ጨረታ ሁኔታ ይህ የልዩ ግዥ ማስታወቂያ ማቅረቢያ ቀን ነው አሊያም የግዥ ማስታወቂያ ለፕረስ (ለጋዜጣ) የሚቀርብበት ቀን ነው፡፡ የአካባቢ ግዥ ከሆነ ደግሞ ቀኑ የጨረታ ጥሪ ቀንን ያመላክታል፡፡ በቀጥታ ግዥ ጊዜ ኮንትራቱ የተሠጠበት ቀን ይሆናል፡፡ በራስ ግዥ ጊዜ ሥራ ላይ የዋለው ቀን የንቅናቄ ቀን ይሆናል፡፡
- **የኮንትራት አፈፃፀም ጊዜ፡-** በመጨረሻም የኮንትራት አፈፃፀም ጊዜ በሣምንታት መመላከት አለበት፡፡ ይህን ማድረግ የግዥ ዕቅዱንና የገንዘብ ፍሰት ዕቅዱን ይወስነዋል፡፡

ወዲያውኑ (በራሱ) ማስላት፡-
ከዚህ መነሻ የ'Excel' ግዥ ሠንጠረዥ ወዲያውኑ በራሱ ያሰላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ለሥራዎች የግዥ ዕቅድ የተለያዩ ደረጃዎችን ቴምፕሌቱ እንዴት እንደሚያሰላ መረጃው ያሣያል፡፡

- **ጨረታ በዓየር ላይ የሚውልበትና የሚዘጋጅበት ጊዜ፡-** ይህ ቁልፍ መረጃ በግዥው ዘዴና እንደተመረጠው ደንብ መሠረት በሥፋት ይለያያል፡፡ በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለው ሠንጠረዥ ለልዩ ልዩ ሁኔታዎች የተሰጠውን የጊዜ ርቀት ያመላክታል፡፡
- **ተቃውሞ የማይቀርብባቸው ቀናት፡-** በጨረታ ሪፖርቶችና ዶኪመንቶች ቅድመ-ቅኝት ጊዜ ዶኪመንቱን ለመመለስና ተቃውሞ እንደሌለው ለመግለፅ እንዲችል የግዥ ሠንጠረዥ ለረጅ ኤጀንሲው ሁለት ሣምንታትን (14 ቀናት) ይሰጣል፡፡ ረጅው ተቃውሞውን ቢያሰማ በዚያው መሠረት የግዥ ዕቅዱ መከለስ ይኖርበታል፡፡
- **የጨረታ ጥሪ ቀን፡-** ጨረታው በይፋ የሚከፈትበት ቀን ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም የግዥ ማስታወቂያዎች መታተምና በጋዜጣና በኢንተርኔት በሣምንት ውስጥ (7 ቀናት) መሠራጨት አለባቸው፡፡ ይህም የግዥ ማስታወቂያው ለሚመለከተው ኤጀንሲ ከቀረበ በኋላ (በ'ULGDP' ሁኔታ በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮገራም ወይም' Business website' አማካኝነት)፡፡
- **የጨረታ ግምገማ ሪፖርት አቀራረብ፡-** የጨረታ ግምገማ ሪፖርት የቴክኒክና የፋይናንስ ባለሙያዎችን በያዘ ግምገማ ኮሚቴ

ይከናወናል፡፡ ሪፖርቱም ለፋይናንስ ግዥ ጽ/ቤት ወይም የጨረታ ሪፖርት ቅድመ-ቅኝት ጊዜ ከሆነ ኮንትራቱን ለመሥጠት ሥልጣን ላለው ለረጅው ይቀርባል፡፡ ከዚህ ላይ ለጨረታ ግምገማ የ14 ቀናት ጊዜ ይሰጣል፡፡

- **የኮንትራት ማጠናቀቂያ፡-** ኮንትራት ማጠናቀቂያ የጨረታ አሸናፊው መታወጅና የኮንትራቱ መስጠት ነው፡፡ አሸናፊውና ተሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ሪፖርቱ ከቀረበበት 14 ቀናት በኋላ ወይም ተቃውሞ በማይቀርብበት ጊዜ በቅደም ተከተል ይሆናል፡፡ አዋጁ በአካባቢ ጋዜጦች መታተምና በከተማ አስተዳደሩ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ መውጣት አለበት፡፡ የኮንትራት ፊርማው ከአንድ ሳምንት በኋላ ይሆናል፡፡

- **የአፈፃፀም ደህንነት አቀራረብ፡-** ይህ ለከተማ አስተዳደሩ ኮንትራክተሩ የሚሠራው ነው እናም ለባንክ ማመልከትን ይጠይቃል፡፡ ኮንትራክተሩ ፊርማውን ለማስረከብ ሁለት ሣምንት ይቀረዋል፡፡

- **የኮንትራት አፈፃፀም፡-** የንቅናቄ ቀን የኮንትራት አፈፃፀም ይፋ መጀመሪያን ያሣያል፡፡ ይህም ለፋይናንስ ጽ/ቤትና ለረጅዎች የካሽ ፍሰት ፍላጐቶችን ለመወሰን ጠቃሚ ቀን ነው፡፡ የአፈፃፀም ድህነት ከቀረበ በኋላ በ14 ቀናት ውስጥ የሰው ኃይልና የማሽነሪ ንቅናቄ ይከናወናል፡፡ የሥራ ጅማሮ ከ1 ሣምንት በኋላ ይሆናል፡፡ የኮንትራት አፈፃፀም ጊዜ በፕሮጀክቱ ስፋትና ውስብስብነት ይወሰናል፡፡ አፈፃፀሙ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ መገመቱ በኮንትራክተሩና በደንበኛው መካከል በሚካሄድ ድርድር ጊዜ ይፈፀማል፡፡ ለዚህ ድርድር በልምድ የተካነ ኢንጂነር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በታች የሚገለፀው የግዥ ዕቅድና የገንዘብ ፍሰቱ ዕቅድ በ' ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ' 8ኛና 9ኛ ዕዝሎች ላይ ተካቷል፡፡

	ጨረታው ዓየር ላይ የሚቆይባቸው ቀናት		Preparation period in days	
ሥራ ላይ የዋለ የግዥ ህግና ዘዴ	ውስብስብ	ቀላል	ውስብስብ	ቀላል
የኢትዮጵያ አግጨ	45	35	140	70
የኢትዮጵያ ሀግጨ	30	21	112	56
የኢትዮጵያ አአ	15	15	42	21
የኢትዮጵያ DP		NA	112	56
ዓለምባንክ አግጨ		45	168	84
ዓለምባንክ ሀግጨ		30	112	56
ዓለምባንክ አአ		15	42	21
ሌሎች ረጅዎች አግጨ		45	168	84
ሌሎች ረጅዎች አግጨ		30	112	56

Table 4: Sample of the amount of time required for varioous procurement options

ደረጃ 4 - የገንዘብ ፍሰት ዕቅድ

የገንዘብ ፍሰት ዕቅዱ (የድርጊት መርሀግብር ይባል የነበረው) በቀጥታ ከግዥ ዕቅዱ ይነሣል፡፡ ሁሉም ዕቅዶች እርስበርስ የተሣሠሩ ናቸው፡፡ የገንዘብ ፍሰት ዕቅዱ የሚፈለገውን የገንዘብ መጠንና መቼ እንደሚፈለግ ይዘረዝራል፡፡

ይህ ፕላን በአብዛኛው ለረጅ ድርጅቶች (የውጭ ፈንድ) ነው የሚያስፈልገው፡፡ ይሁንና ለከተማው ገቢዎች ባለሥልጣንም ያስፈልጋል ማለትም ኮንትራት አንዴ ከተሠጠ የቅድሚያ ክፍያ ፍላጎቶችን ለመፈፀም ገንዘብ መኖሩን እንዲያረጋግጥ ነው፡፡ ይህም ወዲያውኑ በግዥ ዕቅዱ በተመለከቱት ቀናት መሠረት ይሟላል፡፡ የአንድ ፕሮጀክት አጠቃላይ የገንዘብ ፍሰት ፍላጎቶች ሥርጭት ልምድ ባለው ባለሙያ በዓመቱ 4 ክፍሎች (ሩብ ዓመታት) ይከለሣል፡፡

ክፍል 8

ማፀደቅ፣ ሥርጭትና ግምገማ

እንደ’ ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ’ ያለ በጀትን ማፀደቅ የከተማውን የስምምነት ውሳኔ ይመለከታል፡፡ ስለሆነም የካፒታል መዋዕለንዋዮች በጀት በሁሉም የ’ ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ’ ዝግጅት ተሣታፊ አጋር አካላት መፅደቅ አለበት፡፡

ይህን ብለን የከተማው ትልቅ የሥልጣን አካል የሆነው የከተማ ም/ቤት ነው ዕቅድን የማፅደቅ ኃላፊነት ያለው የመጨረሻ አካል፡፡ በጀት ማፅደቅ ማለት በይፋ ዕውቅናን ከመስጠት በላይ ነው፡፡ አንዴ ከፀደቀ የበጀት ዕቅድ በከተማ ም/ቤቱ ባለቤትነት ይያዛል፡፡ ስለሆነም በዕቅድ ይዘቱ ላይ የከተማ ም/ቤቱ ኃላፊነት አለበት (ተጠያቂ ነው)፡፡ ይህ ክፍል ‘ካመዕ’ እንዴት እንደሚፀድቅና ገዢ ህግ እንደሚሆን ይገልፃል፡፡

ደረጃ 1 - የካፒታል መዋዕለንዋይን እቅድ

የ'ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' ሰነድ አንዴ ከፀደቀ ገዥ ሕግ ይሆናል፡፡ የዕቅዱ ባለቤትነት ከከተማ አስተዳደሩ አፈፃፀሙን ወደሚከታተሉት የከተማ ም/ቤት አባላት ይተላለፋል፡፡

ምክንያቱም ማፅደቅ የከተማ አስተዳደሩና የነዋሪዎች (በም/ቤቶቻቸው የተወከሉ) የስምምነት ውሳኔን ያመላክታል፡፡ 'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' በተጨማሪ ዜጎች ድርሻቸውን በባለቤትነት እንዲወጡ ለማስቻል ለሕዝብ መቅረብና ስምምነት ላይ መደረስ አለበት፡፡ መደበኛ የማፅደቅ ሥራው ለከተማ አስተዳደሩ የ' ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ' የትግበራ መጀመሪያ ምዕራፍ ይሆናል፡- አንዴ ከፀደቀ ይፋ የሥራ መመሪያ ይሆናል፡፡

የከተማ አዋጅ ሁሉም የከተማ በጀት በከተማ ም/ቤቱ እንዲፀድቅ ያትታል፡፡ ሆኖም ም/ቤት ማለት ምንም እንኳ ዋናው ቢሆንም 'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ 'ን ለማፅደቅ አንድ አሐድ ብቻ ነው፡፡ በአስተሳሰብ ደረጃ ሰነዱ የተዋረድ መሰላሉን መሠረት አድርጎ መጽደቅ አለበት፡፡

- ካቢኔ የከተማ አስተዳደሩ ዋና ፈፃሚ አካል ነው፡፡ 'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ'ን ያዘጋጀል እናም የመጨረሻ ንድፉን ሊያፀድቅ ይገባል፡፡
- ዜጎች (ነዋሪዎች) በውሳኔ አሠጣጥ ሂደት ተሣታፊ ስለሆኑ ፍላጐታቸው የተካተቱ ስለመሆናቸው ስምምነታቸውን እንዲገልፁ የመጨረሻውን ሰነድ ማፅደቅ አለባቸው፡፡
- የከተማዋ የቀበሌ ም/ቤቶች በተለይም የታላላቅ ከተሞች ከየቀበሌያቸው በተያያዙ መዋዕለንዋዮች የበጀት አቋምን ማፅደቅ አለባቸው፡፡
- የከተማው ከፍተኛ ሕግ አውጭ አካል የሆነው የከተማ ም/ቤት ካመዕን ያፀድቃል፡፡ ረቂቁንም ወደ ገዥ የሕግ ሰነድነት ይቀይረዋል፡፡

(በ'ULGDP' አንዳንድ የገንዘብ ሀብቶች ከውጭ ረጅዎች ይመጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የፋይናንስ ተቋማት አብዛኛውን ጊዜ ባንኮች ከረጂዎች ደንቦች ጋር መጣጣምን አስመልክቶ ካመዕን ማፅደቅ አለባቸው፡፡

ይህም የኢትዮጵያን የበጀት ዓመት ተክትሎ በየዓመቱ ሰኔ 30 በም/ቤቱ መፅደቅ አለበት)፡፡ ለመፈተሽና ለማፅደቅ የጊዜ ገደቡ በትግበራ ማኑዋሉ መሠረት ሁልጊዜ ከጥር እስከ መጋቢት ይሆናል (ሲዲ ዕዝል 8.2)፡፡

ምክንያቱም የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ለክልልና የፌደራል ባለሥልጣናት ከዚያም ለዓለምባንክ ለመፅደቅ መቅረብ ስላለበት ነው፡፡ ይሁንና ከልምድ እንደምንግረው የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ በየግማሽ ዓመቱ ም/ቤቱ ማረጋገጫ እንዲሠዋ ሆኖ መከለስ አለበት፡፡

ስዕል 25: የማፀደቅ ሂደት

ደረጃ 2 - ሰነድ ዝግጅትና ሪፖርት አቀራረብ

ሪፖርት ማቅረብ ከአስተዳደራዊ ሥራ በላይ ነው፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ለበላይ ባለሥልጣናት፣ ለም/ቤቱና ለነዋሪዎች ተጠያቂ የሚሆንበት አሠራር (ዘዴ) ነው፡፡ በካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ዝግጅት ጊዜ ሪፖርት ማቅረብ ለካፒታል መዋዕለ ንዋይ ዕቅድ አፈፃፀም መረጃ ለመስጠት ያገለግላል፡፡ ለዚህ ሲባል ሂደቱን የሚገልፅ ሰነድ በሚገባ መቅረፅ ጠቃሚ ነው፡፡

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት ሪፖርት ለክልል ባለሥልጣናትና ለከተማ ም/ቤት መቅረብ አለበት፡፡ ሪፖርቱም ተግትፎንና የአፈፃፀም ስምምነትን ማካተት አለበት (ሲዲ ዕዝል 8.1)፡፡ ይህንን ስምምነት በመፈረም የከተማው ከፍተኛ ተወካይ (ከንቲባው) አፈፃፀምን መሠረት ላደረገው ለእያንዳንዱ ድጐማ ሕጐች ተገዢ መሆንና ለካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ አተገባበር ስኬትም ኃላፊነትን መውሰድ አለበት፡፡

ሰነድ ዝግጅት ሪፖርት የማቅረብ ያህል ተፈላጊ ነው፡፡ ይህ ማለት አጠቃላይ በሆነ መልኩ ሁሉንም ሰነዶች በማዕከላዊ ቦታ መሙላት ማለት ነው፡፡ ለሪፖርቶች መሟላትና ሥርጭት ኃላፊነት ያለበት ጽ/ቤት ከከንቲባ ጽ/ቤት፣ ከማዘጋጃ ቤቱ፣ ከፋይናንስና ከገቢዎች ጽ/ቤት ጋር በመሆን የከተማው ማስታወቂያ ጽ/ቤት ነው፡፡ የሰነድ ዝግጅት በካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ሂደት የሚዘጋጁትን ሁሉንም ሰነዶች ከሁሉም ዕዝሎቹ ጋር ትክክለኛ የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድንና ከክፍል 5 የተግትፎ መረጃን ጨምሮ ያቀፈ ነው፡፡ በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት እንደጨረታ ሰነድና ተጓዳኝ የጨረታ ሪፖርቶች እንዲሁም የፋይናንስና የፊስካል የሂደት ሪፖርቶች ያሉት በርካታ ሰነዶች ሊመነጩ ይችላሉ፡፡

ደረጃ 3 - የመረጃ ሥርጭት

የመረጃ ሥርጭት በተለይም ከበጀት ውሳኔዎችና ከጨረታ ውጤት ሪፖርቶች ጋር በተያያዘ የከተሞችን ግልፅነትና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሪፖርት ማቅረብና ሰነድ ዝግጅት ጋር የከተማ ማስታወቂያ ጽ/ቤቱ የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድን ከሚተገብሩ መምሪያዎች ጋር በመተባበር የመረጃ ሥርጭት ኃላፊነት የከተማው የማስታወቂያ ጽ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የዜጐችን ዕውቅና መፍጠር ዋና ዓላማ በከተማው ልማት ላይ እንዲሣተፉ ለማስቻል ነው፡፡ ስለሆነም ለዜጐች የመረጃ ሥርጭት ለአስተዳደሩ ግዴታ ነው፡፡ ይኸውም የአንድ ጊዜ ሥራ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው፡፡

የሚከተሉት መረጃዎች ለሕዝብ ሊገለፁ የሚገቡ ጠቃሚ ነገሮች ናቸው፡፡ (ለእያንዳንዱ መረጃ ደረጃቸውን የጠበቁ ቴምፕሌቶች ተዘጋጅተዋል፣ ባለፉት ክፍሎችም ተመላክተዋል፡፡ እናም በሰነድ ሲዲው በዕዝልነት ተያይዘዋል)፡-

- የሕዝብ ስሚው ውጤቶች (የተለያዩ ቡድኖችና ነዋሪዎችን ቀዳሚ ፍላጐቶች አካቶ)
- በጀቶች እንደካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ፣ የጥገና በጀትና መደበኛ ወጭዎች ፣
- የጨረታ ግምገማ ውጤቶችና የኮንትራት አሠጣጡ መጠንንና ምክንያታዊ ማብራሪያዎችን ጨምሮ፣
- የማህበራዊና አካባቢ ጥበቃ ዳሰሳና ፍተሻ ውጤቶች (የአካባቢ ጥበቃና የመልሶ ማቋቋም ማዕቀፎችንና የኢትዮጵያን የአካባቢ ደህንነት መመሪያ ተከትሎ)

ለሕዝብ መረጃን ግልፅ የማድረጊያ መንገዶች በአጠቃላይ አስተደደራዊ ብቃትና በከባቢያዊ ሁኔታ ይወሰናል፡፡

በአብዛኛው ከተሞች ለመረጃ ሥርጭት የማስታወቂያ ሰሌዳዎች አሏቸው፡፡ የአካባቢ ጋዜጦች፣ ሬዲዮ ጣቢያዎችና የመረጃ በራሪዎች የም/ቤት ስብሰባዎችን የሬዲዮ ስርጭት ጨምሮ በኢትዮጵያ ሁኔታ በበቂ ስኬት ለተለያዩ ዓላማዎች ያገለግላሉ፡፡ የቀበሌ ደረጃ የሕዝብ ሰሚዎች ሕዝቡን ለማድረስ ጠቃሚ መሣሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመጨረሻም መረጃን ሁልአቀፍ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ይህም ማለት የአካባቢ ቋንቋን በመጠቀም፣ ቴክኒካዊ ቃላትን በማስወገድና በተቻለ መጠን በሚታይ መረጃ አስደግፎ በመሥራት ነው፡፡



ስዕል 27፡- ገቢዎችን ለመቆጣጠር በራሱ ጊዜ የሚሠራ ግራፊክ ምሣሌ



ስዕል 28፡- የካፒታል መዋዕለንዋይ መቆጣጠሪያ ግራፊክ ምሣሌ



ስዕል 29፡- የከተማዋን የ'ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ' አስተዋጽኦ የሚቆጣጠር ግራፊክ ምሣሌ.

ደረጃ 4 - ቁጥጥር

የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ዝግጅት ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾችን ለመወሰን የሚረዱ መሠረታዊ መረጃዎችን ይጠይቃል፡፡ ይህም ጠቃሚ መረጃ ለውሳኔ ሰጭዎች የከተማዋን የልማት አቅጣጫ ለመወሰን ይረዳል፡፡ ደረጃቸውን የጠበቁ የቁልፍ አፈፃፀም አመልካቾች (ቁአአ) ሪፖርት አቀራረብ ከጊዜ ጋር ለመጓዝና በከተሞች መካከል ውድድርን ለመምራት እነዚህን አመልካቾች ይፈቅዳል (ለምሣሌ ስዕል 26ን ተመልከት)፡፡

የ'MS-Excel' ቴምፕሌት የመረጃ ግብዓትን በቀጥታ ያሰላል፣ በዲያግራም መልክም ያሣያል፡፡ እነዚህ ምስሎችም ወደ ወርድ ቴምፕሌት ይተላለፋሉ (ለቴምፕሌቱ የሰነድ ሲዲውን ተመልከት)፡፡ ዲያግራሞቹ ተጨባጭ ያለፈ መረጃን ከመጭው የታቀደ መረጃ ጋር በማዋሀድ የግሽበት ምጣኔንና የሕዝብ ዕድገትን በአንድ ጊዜ ታሳቢ ያደርጋል (ሠንጠረዥ 27፣ 28ና 29 ምሣሌዎች ናቸው)፡፡

ለ'ULGDP' ሥርዓት የግምገማና ቁጥጥር ሠንጠረዥ አለ (ሲዲ ዕዝል 8.4)፡፡ ሪፖርቶች ደረጃውን በጠበቀ የሪፖርት ቴምፕሌት መሠረት ይቀርባሉ (ዕዝል 5)፡፡ የቁጥጥር ዑደት (ሠንጠረዥ 30) ምን መረጃ፣ በምን ፎርማትና ሪፖርቶች መቼ መቅረብ እንዳለባቸው፣ በምን ያህል ድግግሞሽና ለማን ...ወዘተ.የተሟላ ሂደቱን በሚገባ ይገልፃል፡፡ ቁልፍ ሪፖርቶች የኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ከተጀመረ ጀምሮ የሩብ ዓመት የሂደት ሪፖርቶችና ዓመታዊ ሪፖርቶች ናቸው፡፡

የቁጥጥር ሪፖርት በከተማው 'የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ' የእያንዳንዱን ፕሮጀክት ትክክለኛ አፈፃፀም ከዕቅዱ ጋር አነፃፅሮ ያቀርባል፡፡ ዋና የመረጃ ምንጮች የግዥ ዕቅዶችና የገንዘብ ፍሰት ዕቅዶች ናቸው፡፡ የሁሉም ፕሮጀክቶች የተጠቃለለ ሂደት በካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ የክንውን ሂደት ጠቅላላ አፈፃፀምን ያመላክታል፡፡

የቁጥጥር ሪፖርቱም በገቢ አሰባሰብ ሂደትና መደበኛ ወጭዎች ላይ የጥገና በጀት አፈፃፀምን ግምት ውስጥ አስገብቶ መረጃን ይፈልጋል፡፡

ስለከተማው ጠቅላላ መረጃ							
ዓመት		2001	2002	2003	2004	2005	2006
1	የተገመተ የሕዝብ ዕድገት በ%	4.00 %	5.00 %	4.00 %	5.00 %	4.00 %	4.00 %
2	የግሽበት ምጣኔ በ%	5.00%	6.00 %	5.00 %	6.00 %	7.00 %	5.00 %
የሕዝብ ዕድገትና ግሽበት		9.00 %	11.00 %	9.00 %	11.00 %	11.00 %	9.00 %
የትክክለኛ ቁጥር ማጠቃለያ							
ዓመት							
1	የራስ ገቢዎች	የኢ.ት/ብር 130000	የኢ.ት/ብር 175000	የኢ.ት/ብር 195000	የኢ.ት/ብር 215000	የኢ.ት/ብር 270000	የኢ.ት/ብር 318000
2	መደበኛ ወጭዎች	የኢ.ት/ብር 110000	የኢ.ት/ብር 125000	የኢ.ት/ብር 140000	የኢ.ት/ብር 10000	የኢ.ት/ብር 15000	የኢ.ት/ብር 20000
3	ትርፍ (1-2)	የኢ.ት/ብር 20000	የኢ.ት/ብር 50000	የኢ.ት/ብር 55000	የኢ.ት/ብር 205000	የኢ.ት/ብር 255000	የኢ.ት/ብር 298000
4	መዋዕለንዋዮች	የኢ.ት/ብር 125000	የኢ.ት/ብር 100000	የኢ.ት/ብር 75000	የኢ.ት/ብር 340000	የኢ.ት/ብር 435000	የኢ.ት/ብር 460000
5	ትርፍ/መዋዕለንዋዮች (3 4)	0.16	0.50	0.73	0.60	0.59	0.65

ስዕል 26፡- ዋናካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ስዕሎች የሠንጠረዢ ማጠቃለያ ምሣሌ



ስዕል 30፡- ዓመታዊ የሪፖርትና ቁጥጥር ዑደት

የ'ULGDP' የቁጥጥርና ግምገማ ሥርዓት፡-

'ULGDP' በ19 ፓይለት የኢትዮጵያ ከተሞች ተተግብሯል፡፡ በአሣታፊ ምክክር ሂደት በከተማ ም/ቤቱ ከፀደቀ ዓመታዊ የድርጊት መርሀግብር ጋር የ3 ዓመታት የካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድን ጨምሮ ለተሣትፎ 4 ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ለከተሞች መሠረተልማት ፕሮጀክቶች የሚመደብ የውጭ ፈንድ ሥርዓት በአፈፃፀማቸው ተመሥርቶ ነው፡፡

ስለሆነም ሁሉም ከተሞች በአፈፃፀም መሥፈርቶች መሠረት ይገመገማሉ፡፡ ዋናው መለኪያ የትግበራ አቅም ሆኖ ይህም በየዓመቱ መዝጊያ ላይ የታቀዱ መዋዕለንዋዮችን ከተተገበሩ መዋዕለንዋዮች ጋር በማነፃፀር ነው፡፡ (አብዛኛውን ጊዜ ከተሞች ከውጭ ፈንድ ድጎማ ጋር ለመቀጠል የ'ካመዕ' ዕቅዳቸውን ቢያንስ 80% ማከናወናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

ከአዲሱ የ'ULGDP' ምዕራፍ ጋር (2011 - 2014) አዳዲስ ተጨማሪ ውጤት አመልካቾች ተቀምረዋል፡፡ እነዚህም፡-

- በከተማ ከባቢያዊ አስተዳደሮች (ከከአ) ደረጃ በ'ከከአ' የተለዩ የገቢ አሰባሰብ ዕቅዶች ግቦችን (በበጀት ዓመት 2007 መጨረሻ ላይ 85% ግቡን የመታ አኃዝ)
- ከአነስተኛ አስተያየት ጋር የሚያሟሉ ወይም የማያሟሉ ወቅታዊ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶችን ያዘጋጀ የከተማ አካባቢያዊ አስተዳደሮች (ከአአ) በቁጥር፡፡
- በ' ካፒታል መዋዕለንዋይ ዕቅድ ' በተገለፀው መሠረት ዓመታዊ የጥገና የማስፈፀሚያ በጀትን 75% የተጠቀሙ ከከተማ ከባቢያዊ አስተዳደሮች ('ከከአ) (ቁጥር)
- ቀጥተኛ የፕሮጀክት ተጠቃሚዎች (ቁጥር)፣ የሴት ተጠቃሚዎች መቶኛ (%)
- በ'ከከአ' በመሣተፍ በ500 ሜትር ርቀት ውስጥ የሚካለሉ ዓመት ሙሉ ሊያገለግሉ የሚችሉ መንገዶችን በ'ULGDP' ያገኙ ሕዝቦች (ቁጥር)፡

ይህ ህትመት በጀርመን መንግስት በኩል በጂ. አይ. ዜድ. ድጋፍ ሰጪነት ታትሟል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

Deutsche Gesellschaft
für Internationale
Zusammenarbeit GmbH

COOPERATION
ETHIOPIA
GERMANY